‹‹የዚህ ሀገር የኢኮኖሚ ችግር የሚፈታው በመስራትና በመስራት ብቻ ነው ››

አቶ ሃይሉ ገብረህይወት
የኢኮኖሚ ባለሙያ



ገጽ 6

ድምጹን አጥፍቶ የዓይን ብርሃንን የሚሰርቀው ግላኮማ

ገጽ 8

አዲስ ዘመን
ኢፕድ
81ኛ ዓመት ቁጥር 316 ሐምሌ 16 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# ክልሉ በበጀት ዓመቱ፡-

- ከ300 ሺህ በላይ የሥራ እድል መፍጠሩን አስታወቀ
- 100 ሚሊዮን ኩንታል የሚጠጋ ምርት ሰብስቧል



አቶ ርስቱ ይርዳ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የደቡብ ብሔር ፤ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በ2014 በጀት ዓመት ከ300 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ሥራ አጥ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠሩን አስታወቀ፡፡ በበጀት ዓመቱ በግብርና ዘርፍ አንድ መቶ ሚሊዮን ኩንታል የሚጠጋ ምርት መሰብሰቡንም ገልጿል፡፡

የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ምክር ቤት 6ኛ ዙር 1ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 2ኛ መደበኛ ጉባዔው በትላንትናው ዕለት ሲከፈት የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ርስቱ ይርዳ እንደገለጹት፤ በክልሉ በሁሉም አካባቢዎች 504 ሺህ 894 ሥራ አጥ ዜጎች ተለይተው በቋሚና በጊዜያዊ ለ306 ሺህ 51 ዜጎች የሥራ እድል ተፈጥሮላቸዋል።

ለተደራጁ ሥራ አጥ ዜጎች መነሻ የሚሆን እና በፍጥነት ሥራ እንዲጀምሩ ለማድረግ ከ929 ሺህ ብር በላይ እንደተሰራጨም ጠቅሰዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ 21 ሺህ 333 ኢንተርፕራይዞች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት እንዲያገኙ መደረጉን እና ከ126 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ኢንተርፕራይዞች ስልጠና መሰጠቱንም ነው ርዕሰ መስተዳድሩ የገለፁት።

በሥራ ላይ የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች 544 ሚሊዮን

ክልሉ በበጀት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






ፎቶ፡- አዩብ ተፈሪ

ሼህ ሐጂ ኢብራሂም ቱፋ

## ሕዝበ ሙስሊሙ ለሰላም በአንድነት እንዲቆም ጥሪ ቀረበ

**አስመረት ብስራት**

አዲስ አበባ፤ ሙስሊሙ ኅብረተሰብ ከአንድነት ውጪ የሚያዋጣው ነገር አለመኖሩን ተረድቶ ሀዲስና ቁርኣንን መሠረት በማድረግ ለሰላም በአንድነት እንዲቆም የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ጥሪ አቀረበ።

ሕዝበ ሙስሊሙ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የኢኮኖሚ ጫናዎችን መቋቋም የሚያስችሉና ለፖሊሲ ግብዓት የሚሆኑ ሀሳቦችን ማመንጨት እንደሚገባ ተገለጸ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ጫናዎችን መቋቋም የሚያስችሉ መረጃ ላይ የተመሠረቱና የተጠኑ ለኢኮኖሚ ፖሊሲው ግብዓት የሚሆኑ ሀሳቦችን ማመንጨት እንደሚገባ ተጠቆመ። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማኅበር ትኩረቱን የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ በማተኮር 19ኛውን ዓለም አቀፍ ኮንፈረንሱን አካሂዷል።

ማኅበሩ ትናንት ኮንፈረሱን ሲያካሂድ የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አሕመድ ሽዴ እንደገለጹት፤ ድርቅ፣ ኮሮና፣ ጦርነት፣ የሩሲያና ዩክሬን ግጭት በኢኮኖሚው ላይ ትልቅ ጫና አሳድሯል። ይህን ጫና ለመቅረፍ የሚያስችል ማስረጃና መረጃ ላይ የተመሠረቱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ግብዓት የሚሆኑ ጥናቶች አስፈላጊ ናቸው።

ሳይንሳዊ ትንታኔዎችን የተከተለ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ለማሻሻል ግብዓት የሚሆኑ ጥናቶችን ማሻሻያዎችን ለመቀበል መንግሥት ቁርጠኛ መሆኑን የገለጹት አቶ አሕመድ ሽዴ፤ ማኅበሩ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የዓለም ገበያ አለመረጋጋትና የዋጋ ግሽበት ትልቅ ፈተና ሆኗል። የሀገር ውስጥ ምርት ግሽበት በተመሳሳይ እያደገ ነው።



ፎቶ፡- አዩብ ተፈሪ

አቶ አሕመድ ሽዴ

ይህም የመንግሥት ትልቅ ትኩረት በመሆኑ ችግሮችን ሊቀርፉ የሚችሉ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የማሻሻያ ሥራዎች እየተሠሩ ነው።

በሀገርና ዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰቱ የኢኮኖሚ ጫናዎችን በውጭ ምንዛሪና በኢኮኖሚው ላይ ከፍተኛ

የኢኮኖሚ ጫናዎችን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## "ሩሲያ ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔዎች መርሕን በቁርጠኝነት ትደግፋለች"

-ሰርጌ ላቭሮቭ
የሩሲያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ሩሲያ"ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔዎች" የሚለውን መርሕ በቁርጠኝነት እንደምትደግፍ የሩሲያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰርጌ ላቭሮቭ አስታወቁ፡፡ የሩሲያና የአፍሪካ ግንኙነት በወዳጅነትና ትብብር ላይ የተመሠረተ ነው ብለዋል፡፡

የሩሲያው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰርጌ ላቭሮቭ ሰሞኑን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላኩት ጽሑፍ፤ ሞስኮ ሠላም ወዳድ የውጭ ፖሊሲን በመከተል በዓለም አቀፍ ጉዳዮች ውስጥ ሚዛናዊ ሚናን እየተጫወተች ትገኛለች ብለዋል፡፡ ከአፍሪካ አገራት ጋር ያላት ሁሉን

"ሩሲያ ለአፍሪካዊ ችግሮች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








ዶክተር መሐመድ ኢድሪስ

# ከዲያስፖራው ከአራት ቢሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ተገኝቷል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በተጠናቀቀው የ2014 በጀት ዓመት ከዲያስፖራው 4 ነጥብ 2 ቢሊዮን ዶላር ወደ አገር ቤት መላኩን የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዶክተር መሐመድ ኢድሪስ፣ በ2014 በጀት ዓመት የዲያስፖራው ተሳትፎ በሁሉም ዘርፎች ከፍተኛ ዕድገት የታየበት መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ያለፈችባቸው የተለያዩ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ዲያስፖራው በሀገሩ ጉዳይ ያለው ተሳትፎ እንዲጨምር ዋነኛ ምክንያት መሆኑንም ጠቅሰዋል።

በኢንቨስትመንት፣ በንግድ፣ በሀገራዊ ጉዳዮች እና በፕሮጀክቶች ክንውን ላይ ዲያስፖራው ከቀደሙት ዓመታት በተሻለ ተንቀሳቅሷል ሲሉ ተናግረዋል።

በበጀት ዓመቱ ከዲያስፖራው 4 ቢሊዮን ዶላር (ሪሚታንስ) ይገኛል ተብሎ ታቅዶ 4 ነጥብ 2 ቢሊዮን ዶላር ማሳካት ተችሏል ብለዋል።

ሀገራዊ ፕሮጀክቶችን እና የተጎዱ አካባቢዎችን ከመደገፍ አኳያ በዲያስፖራው ከ1 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር በላይ ድጋፍ መደረጉንም ገልጸዋል።

በበጀት ዓመቱ ከ1 ሺህ በላይ የዲያስፖራ አባላት በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች እንዲሳተፉ ለማድረግ ታቅዶ ከ1 ሺህ 800 በላይ በሂደት ላይ ናቸው ብለዋል።

በፐብሊክ ዲፕሎማሲ በተለያዩ የዓለም አገሮች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን የሀገራቸውን ነባራዊ ሁኔታ በማሳወቅ ላቅ ያለ የዲፕሎማት ሚና የተወጡበት ዓመት እንደነበርም አስታውሰዋል።

እንደ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፣ በታላቁ የሀገር ቤት ጥሪ ዲያስፖራው ከሀገሩ ጎን በመቆም ያሳየው ድጋፍም ከፍተኛ ነው።

በቀጣይም ከሀገር የገጽታ ግንባታ ባለፈ በኢንቨስትመንት፣ በንግድና ቱሪዝም እንዲሁም ሌሎች ሀገራዊ ጥሪዎች የተሻለ ተሳትፎ እንዲደረግ ይሠራል ሲሉ አረጋግጠዋል።

በተለያዩ የዓለም ሀገራት የሚኖሩ ዲያስፖራዎች ኢትዮጵያን በተለያዩ ነገሮች በመደገፍ ያሳዩትን ተሳትፎ እንዲያጠናክሩም ጥሪ ማቅረባቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

# በቶሌ ቀበሌ በንጹሓን ላይ ጭፍጨፋ የፈጸሙት የሸኔ ታጣቂዎች ናቸው ሲል አምነስቲ ኢንተርናሽናል ገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የሸኔ ታጣቂዎች በቶሌ ቀበሌ በንጹሓን ዜጎች ላይ ጥቃት መፈጸማቸውን ከጥቃቱ የተረፉ ሰዎች ነግረውኛል ሲል አምነስቲ ኢንተርናሽናል ባወጣው መግለጫ አስታወቀ፡፡

በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ወለጋ ዞን ጊምቢ ወረዳ ቶሌ ቀበሌ ታጣቂዎች በንጹሓን ላይ የፈጸሙትን ጭፍጨፋ አስመልክቶ የአምነስቲ ኢንተርናሽናል የምስራቅ እና ደቡብ አፍሪካ ዳይሬክተር ዴፕሮዝ ሙቼና ፤ የጥቃቱ ፈጻሚዎች የሸኔ ታጣቂዎች መሆናቸውን ከጥቃት የተረፉ ሰዎች ነግረውኛል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በቶሌ የተፈፀመው ዘግናኝ ግድያ ሴቶችና ሕጻናት ሕይወታቸውን ያጡበትና የተሰቃዩበት ግድያ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ገዳዮቹ ለሰው ልጅ ሕይወት ምንም ደንታ እንደሌላቸው ያሳዩበት ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡ በጥቃቱ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች እንደተገደሉ ከዓይን ምስክሮችና በሕይወት ከተረፉ ሰዎች መስማታቸውንም ገልጸዋል፡፡

እንደ አምነስቲ ገለጻ፤ በቶሌ ቀበሌ የተፈፀመው ዘግናኝ ግድያ በኦሮሞ ነፃ አውጪ ጦር እጅ የተፈጸመ መሆኑን የአይን እማኞች አረጋግጠውልኛል፡፡ ጥቃቱ እንደተጀመረ የአካባቢው አስተዳደር መረጃው ቢደርሰውም፣ መንገዱ ተዘግቷል በማለት ጸጥታ ኃይል ሳይልክ እንደቀረ አምነስቲ አረጋግጫለሁ ብሏል፡፡ ሴቶች እና ሕጻናት ሕይወታቸውን ያጡበት ይህ አሰቃቂ ግድያ ራሱን የቻለ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ መመርመር አለበት ሲሉ የአምነስቲ ኢንተርናሽናል የምስራቅ እና ደቡብ አፍሪካ ዳይሬክተር ዴፕሮዝ ሙቼና ተናግረዋል።

በጭፍጨፋው በብዛት የተገደሉት ሕጻናትና ሴቶች እንደሆኑና አዲስ የተወለዱ ሕጻናት ጭምር እደተገደሉ ማረጋገጡን አስታውቋል፡፡ በቃለ መጠይቁ የተሳተፉ ሰዎች እንደገለጹት ያለማቋረጥ ግድያ፣ ቤት ማቃጠል እና ዘረፋ መኖሩን ተናግረዋል፡፡ የሳተላይት ምስል ትንተና ሰኔ 18 ቀን በቶሌ ቀበሌ በሚገኙ መንደሮች ውስጥ የእሳት ቃጠሎ ተነስቷል የሚለውን አባባል ያረጋግጣል ብሏል አምነስቲ በመግለጫው፡፡

በጥቃቱ ወቅት ጎልማሶች ሥራ ለመሥራት ከቤት ከወጡ በኋላ ነው ያለው የአምነስቲ ገለጻ፤ ከጥቃቱ በፊት የሸኔ አባላት በአካባቢው እንዳሉ የአይን እማኞች ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም ከጥቃቱ በፊት በአካባቢው የሚገኙ መንደሮችን ከበው ነበር ብለዋል፡፡ በወቅቱ በመንደሮቹ ውስጥ በብዛት የነበሩት ከአጥቂዎች መሸሽ ያልቻሉ እናቶችና ሕጻናት ናቸው ብሏል፡፡

የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዶክተር ለገሰ ቱሉ ሰኔ ወር ላይ በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ወለጋ ዞን ጊምቢ ወረዳ ቶሌ ቀበሌ በንጹሓን ላይ ጭፍጨፋ ያካሄዱ የሸብር ቡድኖች በተቀናጀ የጸጥታ አካላት በተወሰደ እርምጃ አብዛኞቹን የሸብር ቡድን ተሳታፊዎች መደምሰስ ተችሏል፡፡ ወደ ጫካ የተበታተኑ የሽብር ቡድኑ አባላትም በጸጥታ ኃይሎችና በኅብረተሰቡ ትብብር እየታደኑ ይገኛሉ። በአካባቢው ጉዳት የደረሰባቸውን ቤተሰቦች የማረጋጋትና ከአካባቢው የተፈናቀሉ ዜጎችን ወደ መንደራቸው እንዲመለሱ፣ የቆሰሉ እንዲታከሙ፣ ንብረታቸው የወደመባቸው የዕለት ደራሽ ምግብና ቁሳቁስ እርዳታ እንዲያገኙ መደረጉንም ሚኒስትሩ አስረድተዋል።

የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም ይህንን ጭፍጨፋ የሚያጣራ ቡድን ማዋቀሩ የሚታወስ ነው፡፡

# ባለሥልጣኑ በከተማዋ የሚስተዋሉ ሕገወጥ ድርጊቶችን በጋራ ለመከላከል ጥሪ አቀረበ

**በኃይሉ አበራ**




አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደምብ ማስከበር ባለሥልጣን ሕገወጥ የመሬት ወረራን ጨምሮ በከተማዋ የሚስተዋሉ የተለያዩ የደምብ ጥሰቶችን አስቀድሞ ለመከላከል የማኅበረሰብ ግንዛቤ ላይ በትኩረት የሚሠራ መሆኑን አስታወቀ።

ባለሥልጣኑ ለብሔራዊ የእግር ኳስ ቡድን ተጫዋቾችና አባላት ስለተግባሩና ራዕዩ ግንዛቤ ሰጥቷል።

የባለሥልጣኑ የቅድመ መከላከል የኅብረተሰብ ተሳትፎ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወይዘሮ ሀኒ ዓለሙ የደምብ መተላለፎችን በጋራ በመቆጣጠርና በመከላከል ረገድ የማኅበረሰብ ተሳትፎ ያስፈልጋል ብለዋል።

የመጫወቻ ሜዳ የሌላቸው የየአካባቢው ልጆች በሕገወጥ ግንባታዎች ሳቢያ አለእቅድ በሚያዙ የመጫወቻ ስፍራዎች መቸገራቸውንም ገልጸዋል።

ብሔራዊ የእግር ኳስ ቡድን አባላት አዲስ አበባ ንፁሕ እና ፅዱ መሆኗንና ጫት ሺሻና ሌሎች አዋኪ ድርጊቶችን ለመከላከል በሄዱበት ሀገር ሁሉ በአርአያነት ግንዛቤ እንዲሰጡም ጥሪ አቅርበዋል።

ተጨዋቾች ጫት ሺሻ እና ሌሎች ሕገወጥ እና አዋኪ ድርጊቶች ዙሪያ ለወጣቶች ሞዴል በመሆን ተፅዕኖ የማሳደርና ግንዛቤ የመፍጠር አቅም እንዳላቸው ገልጸዋል።

የባለሥልጣኑ ተልዕኮ በኅብረተሰብ ሁሉን አቀፍ ተሳትፎ የደምብ መተላለፎችን እና ተያያዥ ሕገወጥ ተግባራትን በመከታተልና በመቆጣጠር አዲስ አበባ ከተማን ለነዋሪዎቿ ማራኪ፣ ሰላማዊና ምቹ ማድረግ መሆኑን አስገንዝበዋል። አዲስ አበባ ከተማ ፅዱ ለነዋሪዎቿ ምቹ እና ለአፍሪካ ተምሳሌት እንድትሆን የተቋሙ ራዕይ ቢሆንም የብሔራዊ ተጫዋቾችና ሁሉም የጋራ ኃላፊነት ነው ብለዋል።

ባለሥልጣኑ በዋነኛነት የሚከላከላቸው የሚቆጣጠራቸውና እርምጃ የሚወስድባቸው በኅብረተሰብ ጤና ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ሕገወጥ እርዶች፣ ሕገወጥ የመሬት ወረራ፣ አዋኪ ድርጊቶችን ጨምሮ በከተማዋ ዘጠኝ ዐብይ የደምብ መተላለፎችን ቀድሞ መከላከል እንዲቻል የማኅበረሰቡ አጋዥነት ያስፈልገናል ብለዋል።

የባለሥልጣኑ የሚዲያና የተቋማት ገፅታ ግንባታ ተወካይ አስተባባሪ አቶ ኤርሚያስ ጋዲሣ በበኩላቸው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደምብ ማስከበር ባለሥልጣን በ11 ወራቱ በሕገወጥ ደምብ ጥሰቶች ቁጥጥር 32 ሚሊዮን ብር መሰብሰቡን አስታውሰው ግንዛቤ መፍጠር ላይ በትኩረት ለመሥራት የሁሉም ትብብር አስፈላጊ መሆኑን አመላከተዋል።

ማኅበረሰቡ ሕገወጥ ድርጊቶችን ቀድሞ ካወቀ ይጠነቀቃል ያሉት አቶ ኤርሚያስ፤ ደምብና መመሪያዎችን አለማወቅ ከተጠያቂነት የማያድን በመሆኑ በጋራ ግንዛቤ መፍጠር እንደሚገባ አመላክተዋል።

# የመንገድ ፖሊሲ አለመኖር ዘርፉን እንደጎዳው ተገለጸ

## -ችግሩን ለመቅረፍ ረቂቅ ፖሊሲ ተዘጋጅቷል

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የመንገድ ፖሊሲ አለመኖሩ የመንገድ ዘርፉን እንደጎዳው የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ አሁን ላይ ችግሩን ለመቅረፍ የሚረዳ የመንገድ ፖሊሲ ረቂቅ መዘጋጀቱም ተጠቁሟል፡፡

የመንገድ ፖሊሲ ረቂቅና ተያያዥ አዋጆች ላይ ያተኮረ ውይይት በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣንና በከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር አስተናጋጅነት ትናንት ሲካሄድ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትሯ ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ እንዳስታወቁት፤ በእስከሁኑ አካሄድ የመንገድ ግንባታውን የሚመራ ፖሊሲ ባለመኖሩ ዘርፉን ወጥነት የሌለው አሠራር እንዲከተል አስገድዶታል፡፡

የመንገድ ዘርፉ የሚመራበትን ግልፅ አቅጣጫ የሚያስቀምጥ ፖሊሲ ማዘጋጀት በማስፈለጉ ላለፉት ሁለት ዓመታት ጥናትና ዝግጅት ሲደረግበት የቆየው የመንገድ ፖሊሲ ረቂቅ የመጨረሻው የዝግጅት ምዕራፍ ላይ መድረሱንም ሚኒስትሯ ገልጸዋል።

በረቂቅ ደረጃ በተዘጋጀው የመንገድ ፖሊሲ ለችግሮቻችን መፍትሔ ሊያመጡ የሚችል አማራጮች ታይተዋል ያሉት ሚኒስትሯ፤ በተለይ ከፍትሐዊነት፣ ከዘለቄታዊ የፋይናንስ አቅም፣ ከመንገድ ልየታ እንዲሁም ግንባታና ጥራት አኳያ ወጥ አካሄድ እንዲኖር የሚያስችል ሰነድ መዘጋጀቱን ጠቁመዋል።

የመንገድ ፖሊሲ ረቂቅ የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ግብዓት የማሰባሰብ የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ እንገኛለን ያሉት ሚኒስትሯ፤ ፖሊሲዎቹን ማስፈጸም የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችንና አዋጆች በተመለከተ ውይይት ተደርጓል ብለዋል።

በቀጣይም ተጨማሪ ግብዓቶችን በማከል



ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ

የመንገድ ፖሊሲ ረቂቁ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እንደሚቀርብ አስታውቀዋል።

ቀደም ባሉ ጊዜያት የመንገድ ልማት ትርጉም በተደራሽነት ላይ ብቻ ትኩረቱን አድርጎ ነበር ያሉት ሚኒስትሯ፤ ሁሉም አካባቢዎች ላይ የፌዴራል መንግሥት መንገድ ልማት እንዲያደርስ ጥረት ሲደረግ መቆየቱን አስታውሰዋል።

ይህም ዋና ዋና የአገሪቷን ልማት ኮሪደሮችን ከግምት ያላስገባ ግንባታ እንዲከናወንና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታችንም በሚፈለገው ልክ እንዳያድግ አንድ ምክንያት መሆኑን ገልጸዋል።

በተጨማሪ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ ዘጠኝ ስር ከመንገድ ግንባታ አኳያ የፌዴራል መንግሥት የሚያከናውናቸው መንገዶች ዋና ዋና የሚባሉና ክልልና ክልልን እንዲሁም ጎረቤት ሀገርን የሚያገናኙትን መሆን እንዳለባቸው ተቀምጧል። ይሁንና ይህን ማስፈጸም የሚያስችል አንድም ሕግ እስከዛሬ አልነበረንም ብለዋል።

በመሆኑም ግልጽ የሆነ የፌዴራል መንግሥትና የክልል መንግሥታት የመንገድ ልማት ሥራ ባለመኖሩ የሚና መደበላለቅ ያጋጥማል። እኛ ግን 70 ዓመት የሞላው የመንገድ አስተዳደር ተቋም ቢኖረንም በቂ ሕጎችን ግን አዘጋጅተን አልተጓዝንም ሲሉ ተናግረዋል።

በተዘጋጀው ረቂቅ ፖሊሲ መሠረት ግን ዋነኛ የመንገድ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎችን በማመላከት ለክልልና ለፌዴራል ተቋማት ተብለው የሚለዩ ሚናዎች መኖራቸውን ሚኒስትሯ ጠቁመዋል።

ወይዘሮ ጫልቱ እንደገለጹት፤ በዘርፉ የሚስተዋሉ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ለመፍታት በፖሊሲ የተደገፈ አካሄድ ያስፈልገናል፤ ረቂቅ የመንገድ ፖሊሲው ፀድቆ ወደሥራ ሲገባ በፌዴራልና በክልል ያለውን የተደበላለቀ ሚና ለማስተካከል፣ የተሳለጠ የመንገድ ግንባታዎች ደረጃ ምደባ ለማቅረብ እና የተሻለ የመሠረተ ልማት ግንባታ አፈጻጸም እንዲኖር ያግዛል።

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ሃብታሙ ተገኘ በበኩላቸው፤ በቀጣይ በረቂቅ ፖሊሲው ላይ ከጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አመራርና ባለሙያዎች ጋር ውይይት እንደሚደረግ አስታውቀዋል።

የመንገድ መሠረተ ልማት ሥራዎችንና የአገሪቷን የሎጂስቲክስ እንቅስቃሴዎች ለማሳለጥ ይረዳል ያሉት ኢንጂነር ሃብታሙ ፤ ፖሊሲው ጸድቆ ወደ ሥራ በሚገባበት ወቅት በ10 ዓመት የመንገድ ልማት ዕቅዱ እንዲሳካ አዎንታዊ ውጤት እንደሚያመጣ ይታመናል ብለዋል።



አቶ ያሬድ መስፍን

# ባንኩ ለአራት ሀገር በቀል ምግባረ-ሰናይ ድርጅቶች ድጋፍ በማድረግ ሥራ ሊጀመር ነው

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- ፀሐይ ባንክ ኢ.ማ ለአራት ሀገር በቀል ምግባረ ሰናይ ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ዛሬ ሥራ ሊጀምር መሆኑን አስታወቀ፡፡

የባንኩ ቦርድ ሊቀመንበርና ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ያሬድ መስፍን እንደተናገሩት፣ ባንኩ በዛሬው እለት በ30 ቅርንጫፎች በይፋ ሥራ ይጀምራል፡፡ በመርሐ-ግብሩም ለአራት አገር በቀል ምግባረ ሰናይ ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

በሥራ ማስጀመሪያ መርሐ-ግብሩም ባንኩ ለአራት አገር በቀል ምግባረ-ሰናይ ድርጅቶች ድጋፍ በማድረግ ነው ያሉት አቶ ያሬድ ፣ ባንኩ ማኅበራዊ ኃላፊነቱን በተግባር በመወጣት ሥራ እንደሚጀምር ጠቅሰዋል፡፡

አራቱ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ሀገር በቀል ምግባረ-ሰናይ ድርጅቶችም የኢትዮጵያ የልብ ሕሙማን ሕጻናት መርጃ ማኅበር፤ የኩላሊት ሕመምተኞች እጥበት በጎ አድራጎት ድርጅት፤ የጌርጌሶን የአዕምሮ ሕሙማን መርጃ እና ኒያ ፋውንዴሽንና ማገገሚያ ማዕከል መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

የባንኩ ዓላማ የባንክ ኢንዱስትሪውን መቀላቀል ብቻ ያሉት አቶ ያሬድ፤ በፋይናንስ ዘርፉ በቂ ትኩረት ያላገኙትን በሀገሪቱ የሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ፤ የግብርናውን ዘርፍ፤ የአምራች ኢንዱስትሪዎችንና አዋጪ ለሆኑ የፈጠራ ሥራዎችና ሥራ ፈጣሪዎች ተደራሽ በመሆን « ለሁሉም የሆነ ባንክ » እንዲሆን የአገልጋይነት ዕሴትን የተላበሰ አገልግሎት መስጠት ነው፣ መድረሻውን ያወቀ ነው፡፡ አዳዲስ ስልቶችን በንድፈ፤ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ታግዞ ቀልጣፋና ደንበኛ ተኮር የሆነ አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ ነው ብለዋል፡፡

ባንኩ የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራቱን በማዘመን ዘመኑን የዋጀ ቴሚኖስ ትራንዛክት አር 21 የለቀቀውን የኮር ባንኪንግ ሲስተምን የባንክ አገልግሎችን እና የቢፒሲ ካምፓኒ ምርት የሆነውን ስማርት ቪስታ በመጠቀም አጠቃላይ የዲጂታል ባንክ አገልግሎት ይዞ ይቀርባል፡፡

በአገልግሎት አይነት፣ ጥራትና ተደራሽነት አንጻር በሁሉም መስክ ዓለም አቀፍ ባንኮች ከደረሱበት ደረጃ ጋር አብሮ ለመጓዝና ተወዳዳሪ ለመሆን መሠረቱን አጠናክሮ ገበያውን የሚቀላቀል ነው ሲሉም ጠቀሰዋል።

ባንኩ የአገልግሎት ተደራሽነትን ለማስፋት በቅርቡ ከ50 በላይ ቅርንጫፎቸን እንደሚከፍት ያወሱት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፣ በአንድ ዓመት ውስጥ ከ100 በላይ ቅርንጫፎችን በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ለመክፈት እንደሚሠራም ተናግረዋል።

ባንኩ የባንክ ኢንዱስትሪው ውስጥ የሚስተዋለውን የፍላጎትና አቅርቦት ያለመጣጣን ክፍተት መኖሩን በተረዱና ለትውልድ የሚሸጋገር ተቋም በመመሥረት የኅብረተሰብ ክፍል ሊያገለግል በሚያስችል አደደረጃጀት ዝግጅቱን አጠናቆ ወደ በይፋ ይገባልም ብለዋል።

# በክልሉ የባህላዊ ፍርድ ቤቶች መመሥረት ከ78 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ማዳኑ ተነገረ

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዳማ፡- የባህላዊ ፍርድ ቤቶች መመሥረት ከ78 ሚሊዮን ብር በላይ የማኅበረሰቡ ገንዘብ ከተለያየ ወጪ ማዳኑን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አስታወቀ።

የጨፌ ኦሮሚያ ስድስተኛ ዙር አንደኛ የሥራ ዘመን 3ኛ መደበኛ ጉባኤ በክልሉ የ2014 ዓ.ም ጠቅላይ ፍርድ ቤት እቅድ አፈፃፀም ላይ ውይይት ባካሄደበት ወቅት የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት አቶ ጋዛሊ አባሲመል እንደተናሩት፤ ማኅበረሰቡ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች በመዳኘት ወጪና ልፋት እንዳለው በመታመኑ ማኅበረሰቡ ወደ ቀደመው ማንነቱ በመመለስ ግጭቶችን በባህላዊ መንገድ እንዲፈታና በዚህ መንገድ የሚወሰን ውሳኔም እንደ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲወስድ ሕጋዊ ማዕቀፍ እንዲኖረው ተደርጓል ብለዋል።

በዓመቱ ከታቀደው የዳኝነት ጥራት 90 በመቶ መድረሱ ለጨፌው አባላት የቀረበ ሲሆን ይህም ከባለፈው ተመሳሳይ ዓመት ጋር ሲተያይ ብልጫ የሚያሳይ ቢሆንም አሁንም ጥራት ያለው የዳኝነት ተግባር ግን ከዚህ በላይ መጨመር እንዳለበትና የሁሉም ባለድርሻ አካላት ርብርብ እንደሚያስፈልግ አቶ ጋዛሊ ተናግረዋል።

በመሆኑም ከ6326 የመጀመሪያ ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ተመሥርተው ከ53 ሺህ በላይ ጉዳዮች ቀርበው ከ39ሺህ በላይ መፍትሔ ማግኘታቸውን አስረድተዋል።

በተለይም በደን ምንጣሮ፣ የወላጆች ማንነት፣ በገጠርና በከተማ መሬት ላይ የሚነሱ ክርክሮች ፣ በጎሳዎች መካከል በሚነሱ ጉዳዮች በተመለከተ እንዲሁም ሌሎች ለበርካታ ዘመናት በመደበኛ ፍርድ ቤቶች መፍትሔ ያላገኙ ጉዳዮች በአጭር ጊዜ በባህላዊ ፍርድ ቤቶች መፍትሔ ማግኘታቸውን ፕሬዚዳንቱ ተናግረዋል።

በተለይም ከሀሰተኛ ማስረጃ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ችግር አሁንም መፍትሔ ያልተገኘለትና ችግሩ ተሻግሮ የመጣ በመሆኑ ተገቢው የአሠራር ማስተካከያ ተደርጎ በዚህ ረገድ የሚስተዋለውን ችግርና የማኅበረሰቡን እሮሮ መመለስ እንደሚገባ ከጨፌ አባላት በትኩረት የተነሳ ነው።

የዳኞች ስነ-ምግባር፣ የመልካም አስተዳደር ችግሮችንና ቀልጣፋ አገልግሎት ከመስጠት አንፃርም ክፍተቶች እንደሚስተዋሉ ተነስቷል።

ፕሬዚዳንቱ ከጨፌ አባላቱ ሐሰተኛ መረጃን በተመለከተ በተነሳው ሀሳብ ላይ በሰጡት ሃሳብ ጉዳዩ ትክክል መሆኑን ጠቁመው፤ ተገቢው የአሠራር ማስተካከያ በማድረግ ከሐሰተኛ ማስረጃ የፀዳ አገልግሎት መስጠት እንደሚያስፈልግና በዚህ ረገድ የሚነሱ ቅሬታዎች ላይ ሁሉም ርብርብ ማድረግ እንደሚጠበቅበት ተናግረዋል።

ከፍርድ ቤቶች ነፃነት፣ ኃላፊነትና ግልፅኝነት ጋር ተያይዞ የሚነሱ የማኅበረሰቡ ቅሬታዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻሎች የታዩ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣



አቶ ጋዛሊ አባሲመል

የዳኝነት ስነ-ምግባርና የዳኝነት ሥነ ሥርዓት በመጣስ 341 የሚደርሱ ሠራተኞች ላይ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ እርምጃ የተወሰደባቸው መሆኑንም ገልፀዋል።

በተለይም ከተወሰደባቸው እርምጃ መካከልም ከፍተኛ የስነ ምግባር ጉድለት ያሳዩ አራት ዳኞች፣ ያለ በቂ ምክንያት ከሥራ ገበታቸው የቀሩና ማኅበረሰቡን ለእንግልት የዳረጉ አስራ ሁለት ዳኞች በጥቅሉ 16 የሚደርሱ ዳኞች ከስነ ምግባር ጋር ተያይዞ ከሥራ የተሰናበቱ መሆኑን ፕሬዚዳንቱ ተናግረዋል።

ዜና

# የኢኮኖሚ ጫናዎችን መቋቋም...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ጫና የሚያሳድሩ መሆናቸው የገለጹት አቶ አሕመድ ሽዴ፤ በመንግሥት እየተሠሩ ካሉ ሥራዎች የእዳ ጫናውን ወደ መካከለኛ ደረጃ ለማውረድ ከዓለም ባንክ፣ ከቡድን 20 ሀገራት፣ አይኤምኤፍ ጋር ድርድር ተጀምሯል። ይህም ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሪ ችግርን የሚፈታ ነው። የልማት ግቦችን ለማሳካት የእዳ ጫናዎችን ለመቀነስ የብድር ሽግሽግ ለማድረግ እየተሠራ በመሆኑ የፊሲካል አቅም እንደሚያሳድግ ገልጸዋል።

የብሔራዊ ባንክ ገዥ ዶክተር ይናገር ደሴ በበኩላቸው፤ የፋይናንስ ዘርፍ ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ ነው። የኢንቨስትመንት፣ የግብርና፣ የአምራች ዘርፉ፣ በሚገባ እንዲያመርት ማድረግ ያስፈልጋል፤ ለዚህ ደግሞ የባንኮች ሚና ከፍተኛ ነው። ንግድን ማሳደግ፤ ምርታማነትን መጨመር፣ በፋይናንሱ ዘርፍ የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር ማድረግ በብሔራዊ ባንክ በኩል እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችና ሊሰሩ የታሰቡ እቅዶች ናቸው። የኢትዮጵያ ዶክተር ይናገር፤ ኢኮኖሚውን ለማሳደግ ከአስር ዓመቱ የልማት ግቦች አንዱ ሲሆን በዚህም የግብርናውን ዘርፍ ማዘመን፣ የማዕድን፣ የኢንቨስትመንቱንና ቱሪዝምን ዘርፍ በመጠቀም ኢኮኖሚውን ማሳደግ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል።

የምንዛሪ እጥረት፣ አገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች ያሉ ሰላምና አለመረጋጋቶች፣ ቀጣይነት ያለው ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ተግዳሮቶች መሆናቸው የገለጹት የብሔራዊ ባንክ ገዥ፤ ባንኩ ችግሮችን በመለየት እልባት እንዲገኙ ተግዳሮቶቹን ወደ መልካም አጋጣሚ ለመቀየር እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

በባንክ ሲስተም በፋይናንስ ተቋማት ተቀማጭ የሆነው ገንዘብ መጠን አንድ ነጥብ ሰባት ትሪሊየን ብር መድረሱን ገልጸው፤በዘርፉ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት



በማኅበሩ የሚደረጉ የፋይናንስ ተኮር ጥናቶችን እንደ ግብዓት ይጠቀማል ብለዋል።

ላለፉት ሦስት ዓመታት ብሔራዊ ባንክ በርካታ የሪፎርም ሥራዎችን መሥራቱን የገለጹት ዶክተር ይናገር፤ የፋይናንስ ዘርፉን በማዘመንና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ፤ ከ10 ዓመቱ መሪ የልማት እቅድ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ ነው። የካፒታል ገቢያችን እንዲሻሻል፣ የቁጠባ ባህል እንዲዳብር፣ የባንክ ተደራሽነት እንዲስፋፋ ሰፊ ሥራዎች ተሠርተዋል። ሀገሪቱ ከፍተኛ የመልማት እምቅ አቅም ያላት በመሆኑ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው በትኩረት እየተሠራበት ነው። የኢንቨስትመንት፣ የግብርና፣ የአምራች ዘርፉ፣ በሚገባ እንዲያመርት ማድረግ ያስፈልጋል፥ ለዚህ ደግሞ የባንኮች ሚና ከፍተኛ ነው ብለዋል።

# ሕዝበ ሙስሊሙ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ ሐጂ ኢብራሂም ቱፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት ቃለ ምልልስ ላይ እንደተናገሩት የነብዩ መሐመድን እና የሱሀቦችን ፈለግ በመከተል ሀገሪቱን ወደ ሰላም ማምጣት ተገቢ ነው።

"ሀገራችን ኢትዮጵያ በኡለማ የበለፀገች ሀገር ነችና ኡለማዎቻችን የሚሉትን በመስማት መተግበር አስፈላጊ ነው" ያሉት ፕሬዚዳንቱ ከምን ጊዜውም በላይ አሁን ለሰላም ቅድሚያ የሚሰጥበት ወቅት ላይ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የሌሎች እምነት ተከታዮችም የራሳችሁን እምነት እንደምታከብሩ ሁሉ የሌላውን እምነት ማክበር ተገቢ ነው ሲሉም ተናግረዋል፡፡ መጀመሪያ ከራስ እምነት እኩል የሌሎችን ማክበር የሚገባ መሆኑን የጠቀሱት ሀጂ ኢብራሂም፤ የሌላውን እምነት ሳያከብሩ ግን እምነቴን አከብራለሁ ማለት ትክክል አለመሆኑን አስረድተዋል።

ቤተክርስቲያን እየተቃጠለ መስጊድ አይነካም ማለት ዘበት፤ መስጊድ እየተቃጠለ ቤተክርስቲያን አይነካም ማለትም አይቻልም ያሉት ፕሬዚዳንቱ ሁሉም ተከባብሮ ተባብሮ ተቻችሎ መኖር ይገባዋል ብለዋል።

አንድ ሀገር ውስጥ አንዱ ጎጂ አንዱ ተጎጂ ሆኖ አሸናፊ ይኖራል ማለት እንደማይቻል ተናግረው ደም እየፈሰሰ ባለበት ሀገር ሰላም ይኖራል ማለት ስህተት መሆኑን አስረድተዋል።

ሰው የሰው ልጅ በመሆኑ ብቻ ክቡር መሆኑን በእስልምና አስተምህሮት ውስጥ መኖርን ጠቅሰው ሰው በሃይማኖቱ ሳይሆን ሰው በመሆኑ ብቻ ተከብሮ መኖር ይገባዋል ብለዋል። በሃይማኖት መነጣጠል፤ በማንነት ደም መፋሰስ ይበቃል ፤ በሰላም ተከባብረን ተፈቃቅረን እንደተለመደው እንኑር በማለትም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# ክልሉ በበጀት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

445 ሺህ ብር በበጀት ዓመቱ እንዲቆጥቡ መደረጉንም አቶ ርስቱ ተናግረዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ በኢንተርፕራይዞች ዘርፍ ውዝፍ ሆኖ ያለውን 1 ቢሊዮን 113 ሚሊዮን 107 ሺህ ብር ለማስመለስ ታቅዶ 772 ሚሊዮን 281 ሺህ ብር ማስመለስ መቻሉንም ገልፀዋል።

ለኢንተርፕራይዞች፣ ለጥቃቅንና አነስተኛና ማኅበራት ማምረቻና መሸጫ ቦታ የሚሆን 5 ሺህ 222 ሄክታር መሬት መተላለፉንም አቶ ርስቱ ይርዳ ተናግረዋል፡፡

ርዕሰ መስተዳድሩ ግብርናን በተመለከተ ባቀረቡት ሪፖርት÷ በ2013/2014 በጀት ዓመት መኸር እርሻ በአዝርዕት እንዲሁም በአበባና አትክልት 1 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሔክታር በመሸፈን ከ99 ነጥብ 4 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት መሰብሰቡን አመላክተዋል፡፡

በበጋ የስንዴ ምርት 6 ሺህ ሔክታር በስንዴ ለመሸፈን ታቅዶ 5 ሺህ 109 ሄክታር መሬት መሸፈን መቻሉን ጠቁመው÷ ከዚህም 152 ሺህ ኩንታል ምርት ተገኝቷል ብለዋል።

ከወጪ ምርት እና ከቁም እንስሳት ግብይት 48 ሚሊዮን 262 ሺህ 953 ዶላር ገቢ መገኘቱን ተናግረዋል።

ርዕሰ መስተዳድሩ ለምክር ቤቱ ባቀረቡት የ2015 ጠቋሚ ዕቅድ ላይም አባላቱ ላነሷቸው ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል።

ከነዚህም ውስጥ አንዳንድ አካባቢዎች የመንገድ፣ ውሃ፣ የጤናና የመስኖ ተቋማት ግንባታ አለመኖር በሕዝብ ዘንድ የመልካም አስተዳደር ጥያቄ እያስነሳ መሆኑን የምክር ቤት አባላት አንስተዋል።

በ2015 በጀት ዓመት የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሠራ ለጥያቄው ምላሽ የሰጡት ርዕሰ መስተዳድር አቶ ርስቱ ይርዳ አቅም ሲፈቅድ አዳዲስ ፕሮጀክቶች እንደሚጀመሩ ገልጸዋል።

በአርብቶ አደር አካባቢዎች የውሃ ችግር አለ በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ በአሁኑ ሰዓት በክልሉ አጠቃላይ የንፁሕ መጠጥ ውሃ ሽፋን 48 በመቶ ላይ የሚገኝ በመሆኑ ይህን ለማሻሻል እንሠራለን ብለዋል።

በጉራጌ ዞን ከአጣጥ ማዞሪያ እስከ ሌራ የተጀመረው የአስፋልት መንገድ በተቋራጭ ችግር ምክንያት መጓተቱን ያስረዱት አቶ ርስቱ ጨረታ መውጣቱንና በቀጣይ በተጠናከረ መልኩ ግንባታው እንዲከናወን ክትትል እየተደረገ መሆኑን ለምክር ቤቱ ገልጸዋል።

የማዳበሪያ እጥረት ለመቅረፍ ጥረቶች መደረጋቸውን ያነሱት ርዕሰ መስተዳድሩ በቀጣይም እየተሻሻለ ይሔዳል ብለዋል።

በአማሮ ወረዳ የመሠረተ ልማት ሥራዎችን ለማከናወን የፀጥታ ችግር ተግዳሮት ሆኖ መቆየቱን ገልጸዋል። በተያዘው በጀት ዓመት ፀጥታን ለማስጠበቅ የተጠናከረ ሥራ እንደሚከናወንም ነው የተናገሩት።

የምክር ቤት አባላት እና ሕዝቡ ከመንግሥት ጋር በመሆን ለሰላም ዘብ እንዲቆሙም ርዕሰ መስተዳድሩ ጥሪ አቅርበዋል።

ርዕሰ መስተዳድሩ ባቀረቡት የ2015 በጀት ዓመት ጠቋሚ ዕቅድ ላይ ውይይት ተደርጎበት በሙሉ ድምፅ ፀድቋል።

# "ሩሲያ ለአፍሪካዊ ችግሮች...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

አቀፍ ትብብርም የዚሁ አንድ አካል መሆኑን ጠቅሰዋል። በዚህም ሩሲያ "ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔዎች" የሚለውን መርሕ በቁርጠኝነት እንደምትደግፍ አስታውቀዋል።

የሩሲያና የአፍሪካ ግንኙነት በወዳጅነትና በትብብር የተሳሰረ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ አፍሪካውያን ከቅኝ ግዛት ጭቆና ነጻ ለመውጣት የሚያደርጉትን ትግል ሩሲያ ሁልጊዜም በቅንነት ስትደግፍ መቆየቷን ገልጸዋል። ከቅኝ ግዛት የመውረዱን ሂደት ለማጠናቀቅ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ላይ አፍሪካ የምታነሳቸውን ጥያቄዎች ሩሲያ እንደምትደግፍም ተናግረዋል።

አፍሪካ በዓለም አቀፍ ፖለቲካና ኢኮኖሚ ውስጥ ወሳኝ ሚና እንዳላት ጠቅሰው፤ የዘመኑን ቁልፍ ችግሮች ለመፍታት ንቁ ተሳትፎ እንዳላትም አስታውቀዋል። አፍሪካውያን የአብሮነት ድምጻቸው በዓለም ጉዳዮች ላይ ይበልጥ የሚስማማ እንደሆነም የገለጹት ሚኒስትሩ፤ ሩሲያ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር መርሆዎች ላይ የተመሠረተና የዓለምን የባህልና የሥልጣኔ ብዝኃነት ከግምት ውስጥ በማስገባት የአፍሪካን የተጠናከረ አቋም ትደግፋለች ብለዋል።

ሚኒስትሩ፤ "አገራችን በማንም ላይ ምንም ነገር አትጫንም። ሌሎች እንዴት መኖር እንዳለባቸውም ጫና አታሳድርም። እኛ የአፍሪካ መንግሥታትን ሉዓላዊነትና የእድገታቸውን መንገድ በራሳቸው የመወሰን የማይገረሰስ መብታቸውን እናከብራለን። "ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔዎች" የሚለውን መርህ በቁርጠኝነት እንደግፋለን" ሲሉ ተናግረዋል።

አሜሪካና አውሮፓ የበላይነት ለመያዝና አንድ ወጥ የሆነ የዓለም ሥርዓት በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ላይ ለመጫን የሚያደርጉትን ሙከራ አፍሪካውያን እንደማይቀበሉ እናምናለን ሲሉም ገልጸዋል።

ሰርጌ ላቭሮቭ አክለውም፤ የአፍሪካን ነጻ የንግድ ቀጣና ለአህጉሪቷ እውነተኛ የኢኮኖሚ ነጻነት እርምጃ መሆኑን አመላክተዋል። የሩሲያና የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኦፕሬተሮችን ወደ አንድ ገበያ የማምጣትና በትላልቅ የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች እንዲሳተፉ የማበረታቻ ተግባራት እንደሚኖሩም ጠቅሰዋል።

ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ ሩሲያ ለአፍሪካ ጠቃሚ የሆኑ የምግብ፣ የማዳበሪያ፣ የኢነርጂና ሌሎች ሸቀጦችን መላክን በተመለከተ በዓለም አቀፍ ኮንትራቶች ውስጥ ያለባትን ግዴታ በቅን ልቦና መወጣቷን ትቀጥላለች። ለዚህም ሁሉንም እርምጃዎች እየወሰደች ትገኛለች። በፖለቲካ፣ በሰብዓዊነት፣ በንግድና ኢንቨስትመንት መካከል ያለው የሩሲያና የአፍሪካ ግንኙነት ጠቀሜታ ያለው እንደመሆኑ በዓለም አቀፍ የአካባቢ መዋዠቅ ላይ የተመሠረተ አይደለም።

የቀዳሚ መጽሄት

# አገልግል



የጉጂ ቡና አልሚና ላኪ ሶስተኛው ትውልድ

ገጽ 13

## ‹‹የዚህ ሀገር የኢኮኖሚ ችግር የሚፈታው በመስራትና በመስራት ብቻ ነው ››

አቶ ሃይሉ ገብረህይወት
የኢኮኖሚ ባለሙያ



ገጽ 6



በሠርግ ዋዜማ የመጣው ዱብዕዳ

ገጽ 16

የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን
HOUSING DEVELOPMENT CORPORATION

ከአ.አ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዕጣ መጭበርበርና የመንግሥት እርምጃ

በ20/80 እና 40/60 የቤቶች ልማት ፕሮግራም ተመዝግበው በመጠባበቅ ላይ ለሚገኙ ነዋሪዎች የዕጣ ማውጣት ሥነ ሥርዓት መካሄዱ ይታወሳል።የዕጣ አወጣጥ ሥነሥርዓቱ የተካሄደበት ሶፍትዌር በተጭበረበረ መልኩ ቁጠባ ያላከናወኑ ሰዎች እንዲገቡ ተደርጓል በሚል ዕጣው እንዲሰረዝ ተደርጓል።በዕጣው አወጣጥና መሰረዝ ዙሪያ ማጣራቶች ተደርገው ለሕዝብ ይፋ መደረጋቸው ይታወሳል።

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሐምሌ 01 ቀን 2014 የወጣውን የ20/80 እና 40/60 የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዕጣ አስመልክቶ ማብራሪያ ሰጥቷል። በዚህ መግለጫ የከተማ አስተዳደሩ ከኢንሳ፤ ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፤ እንዲሁም ከብሔራዊ መረጃና ደህንነት አጣሪ ቡድን እንዲቋቋም ተደርጎ ወደ ማጣራት ሥራ የተገባ ሲሆን የነበሩ ጉዳዮች ለሕዝብ ይፋ ተደርጓል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ በወቅቱ እንዳሉት፤ የጋራ መኖሪያ ቤት ዕጣ በማውጣት ሂደት ባጋጠመን ችግር ሕዝቡንም ከተማ አስተዳደሩንም ያሳዘነ ድርጊት ተፈፅሟል።በዚህ አንገብጋቢ ጉዳይ ላይ ኅብረተሰቡ በትእግስት በመጠበቅ እንዲሁም የጀመርነውን ጥረት ከጎናችን በመቆም ላሳየው ጥረት ከልብ አመስግነዋል።ችግር ቢያጋጥም እንኳን በቀጥታ ኦዲት እናደርጋለን ብለን በገለፅነው መሠረት ጥቆማ ስለደረሰ ጊዜ ሳንሰጥ በሚመለከታቸው አካላት የማጣራት ሥራ እንዲጀመር አስደርገናል።የቴክኖሎጂ ውንብድና አጋጥሞናል።አመራር የመራው ውንብድና ነው።በዚህ ሂደት የቤት ስርቆት ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ፍላጎት ጭምር ተገልፆበታል።

‹‹የዚህ ሥራ ሌላው አላማ መንግሥት ሕዝብን ማገልገል ብቃት የለውም የሚል ገፅታ ለመፍጠርና ኅብረተሰቡ በመንግሥት ላይ እንዲያምፅ ለማድረግ በማሰብ ነው›› በማለት ከንቲባ አዳነች ገልፀዋል።በዚህ ሂደት ችግር እንዳጋጠመን ማጣራት መጀመራችን የሕዝብን ሀብት መታደግ እንድንችል አድርጎናል።ሕዝቡን መታደግ ችለናል።ኅብረተሰቡም መብቱን ለማስጠበቅ ያደረግነውን ጥረት ተረድቶናል።እኛም ድሃውን ማህበረሰብ መታደግ በመቻላችን ያስደስተናል፡፡



የቀረበልን ሪፖርት በሚገባ ሲስተሙ ተቆጣጣሪ ጭምር እንዳለውና አስተማማኝ እንደነበረ ነበር።ይህንንም ለማመን ምክንያቶች ነበሩ።ምክንያቱም ከዚህ በፊት በዚህ ቡድን የለሙና ጥቅም ላይ የዋሉ ሲስተሞች ነበሩ።ማረጋገጫ ለማግኘት የተሄደበትና ተቋም ለተቋም የተደረጉ ግንኙነቶችም ችግር ነበረባቸው።ሰዎች ለሰዎች የተደረጉ ግንኙነቶች ዓይነት መመልከት ተችሏል።ኢንሳ ማረጋገጫ ሰጥቶ እንደነበርም በወቅቱ ተገልፆ ነበር ነገር ግን ሕጋዊ በሆነ ደብዳቤ ኢንሳ ያረጋገጠው እንዳልሆነ መታየቱን ያብራራሉ።ባለሙያዎችና አመራሮች በቁጥጥር ስር ውለዋል።እንዲሁም አንድ ኃላፊና አንድ ምክትል ኃላፊ ከኃላፊነታቸው ተነስተዋል።ሌሎች እርምጃዎች እንደ ሚዛኑ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

ከንቲባ አዳነች አቤቤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ጉባኤ ባካሄደበት ወቅት በጉዳዩ ዙሪያ ማብራሪያ ሰጥተዋል።«በኮንዶሚኒየም የገጠመን ነገር አሳፋሪ ነው። ችግሩ የሶፍትዌር ብቻ አይደለም፤ ሶፍትዌር እኮ ከባንክ ቁጠባ ያቋረጠ ሰው በድጋሚ እንዲካተት አያደርግም።ሶፍትዌር 100 ሺህ የሚጠጋ ተጨማሪ ዳታ እንዴት ይዞ ይመጣል?? ከፍተኛ ዳታ መደለዝ መጨመር ነው የተደረገው።አላማው ሰዎቹ ቤት እንዲያገኙ ነው ወይንስ ቁጣ ለመቀስቀስ??

ምክንያቱም ኮንዶሚኒየም አገኘህ የተባለው ሰው ባንክ አዋውሉኝ ብሎ ቢሄድ ባንክ አያዋውለውም፤ ቁጠባ ስላላደረገ ወይም ስላቋረጠ፤ ጥቂት ሰው ቢሆን በግለሰብ መመሳጠር ምናልባት ሊዋዋል ይችላል።ይሄ ሁሉ ሰው ግን ሊዋዋል አይችልም።እና አላማው ቤት መስጠት ብቻ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?? ሃሳቡ በዚህ ሰበብ አመፅ መቀስቀስም ጭምር ነበር። የኮንዶሚኒየም ታሪክ መንግሥትና ሕዝብ እንደማይተማመን የሚያደርግ ብዙ የኋላ ታሪኮች አሉ።ይህንን በኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ አስጠንተን አረጋግጠናል፡፡

አብዛኛው ከሰዎች ጋር የሚያያዝ እንጂ የሙያ ጉዳይ አድርገን ሰበብ የምናደርገው አይደለም።የሚያለማ የነበረው ባለሙያ ዳታውን ቀድሞ እንዳላገኘው ነበር ይሄ አመራር የሚያውቀው ጉዳይ ነው።ያ ሁሉ ታዛቢና ትልልቅ ሰዎች ባሉበት ሙከራ ተደረገ።ለዚህም ነው አሁን ዳታውና ሶፍትዌሩ ስለተገናኘ ይታሸግ ተብሎ የታሸገው።ቀድሞ እንደተገናኘ ቢታወቅ ኖሮ ምን መታሸግ ያስፈልግ ነበር፡፡»

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ሹመቴ ግዛው ሐምሌ 01 ቀን 2014 ዓ.ም የወጣውን የ 20/80 እና 40/60 የጋራ መኖሪያ ቤቶች አስመልክቶ መግለጫ ሰጥተዋል።በመግለጫቸውም እንደተናገሩት፤ ኢንሳ እንዲህ ዓይነት ሥራዎችን እንዲመራ የሕግ ኃላፊነትም ስላለበት ሥራውን መርቶ እዚህ ደረጃ አድርሷል።ሲስተሙ ከኑሮው ቀንሶ ተቸግሮ ሲቆጥብ የኖረውን ማህበረሰብ መብት እንዲያጣ የሚያደርግ በመሆኑ ሲስተሙ ተአማኒነት የሌለው ነው።ሲስተሙ የመልማት ዓለም አቀፍ ስታንዳርዱን ያልጠበቀና ሦስቱን አካላት፤ አልሚውን፤ ተጠቃሚውን እና አረጋጋጩን አካላት የቀላቀለ እንዲሁም ለምዝበራ ያጋለጠ ነው።የዳታው አጠቃቀም ከእጅ ንክኪ ነፃ እንዲሆን የሚፈለግ የነበረ ቢሆንም ነገር ግን እጅ በዝቶበት የነበረ መሆኑ ታይቷል፡፡

ከዚህ የምንማረው ነገር ቢኖር በደረስንበት ደረጃ ተዓማኒ ያልሆኑ ነገር ሲገኝ አቁመን እንዲጣራና እርምጃ እንዲወሰድበት ማድረግ እንደሚገባና ሁልጊዜም ይህንን ማድረጋችንን መቀጠል እንዳለብን በተጨማሪም የአመራር ሥነምግባርን ማሟላት እንደሚያስፈልግ እንዲሁም ሰዎች የተሰጣቸውን የማገልገል ዕድል በአግባቡ መጠቀም እንዳለባቸውም ገልፀዋል፡፡

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹የዚህ ሀገር የኢኮኖሚ ችግር የሚፈታው በመስራትና በመስራት ብቻ ነው ››

### - አቶ ሃይሉ ገብረህይወት የኢኮኖሚ ባለሙያ

ማህሌት አብዱል



ፎቶ፡- እዮብ ተፈራ

አዲስ አለም ከተማ በ1925 ዓ.ም ነው የተወለዱት፤ የገበሬ ልጅ ቢሆኑም ገና በህፃንነታቸው ነጋዴው ታላቅ ወንድማቸው አዲስ አበባ አምጥተዋቸው ቀጨኔ መድሃኒያለም በሚገኘው የቄስ ትምህርት ቤት አስገባቸው፤ ዳዊትም ደገሙ:: ብዙም ሳይቆዩ ግን በአዲስ አለም ከተማ ታዋቂ የሆኑ የዜማ መምህር ጋር እንዲማሩ ዳግም ወደ ትውልድ ቀያቸው ተላኩ:: ሁለት ዓመት ዜማ ከተማሩ በኋላ አዲስ አበባ መጥተው በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ገብተው በስምንት ዓመታት ውስጥ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በከፍተኛ ውጤት አጠናቀቁ::

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በከፈቱትና በቀድሞ ሥያሜው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ገብተው በኢኮኖሚክ አድሚኒስትሬሽን ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል:: ቤስ በተባለ የፈረንሳይ ጅምላ አከፋፋይ ኩባንያ እንደተቀጠሩ ነፃ የትምህርት እድል አግኝተው አሜሪካ ተላኩ:: በካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ ለሁለት ዓመታት ኢኮኖሚክስና አለም አቀፍ ንግድ ላይ ጥናት አድርገው የማስተርስ ዲግሪያቸውን ተቀበሉ:: ወደሃገራቸው ተመልሰውም የላካቸው ድርጅት ውስጥ ዳግም ተቀጥረው በቡና ምርትና ሽያጭ ዘርፍ እንዲሁም የድርጅቱ የወጭ ንግድ ሃላፊ ሆነው ሰሩ::

በመቀጠልም ልማት ባንክ ተቀጥረው የፕሬዚዳንቱ ረዳት ሆነው ለጥቂት ጊዜያት ከሰሩ በኋላ በኢንዱስትሪያል ፋይናንሲንግ ትምህርት ዘርፍ ለስድስት ወራት እንግሊዝ ተልከው ስልጠና ወሰዱ:: ወደ ባንኩ ተመልሰውም በኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን የሚባል አዲስ የስራ ክፍል ሃላፊ ሆነው ለአስር ዓመታት አገለገሉ:: ከልጅነታቸው ጀምሮ ነጋዴ የመሆን ህልም የነበራቸው እኚሁ ሰው የመንግስትን ስራ በመተው ቡና ፤ ቦሎቄና ማሾ የተባሉ የተለያዩ የግብርና ውጤቶችን ወደ ውጭ በመላክ እንዲሁም የተለያዩ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ከውጭ በማስመጣት ሙሉ ለሙሉ ንግድ ውስጥ ገቡ:: ከዚህም ባሻገር በግብርና ኢንቨስትመንት ላይ በመሰማራት ጥጥና ሌሎች ምርቶችን በማምረት ለበርካታ ኢትዮጵያውያን የስራ እድል ፈጥረውም ነበር:: ሆኖም ከደርግ ሥርዓት መምጣት ጋር ተያይዞ የእርሻ መሬታቸውም የንግድ ሱቆቻቸው ተወረሰባቸው፤ የነበረውም የፖለቲካ ስርዓት አልጥም ስላላቸው ሃገር ጥለው ከነቤተሰባቸው አሜሪካ ተሰደዱ:: ሥርዓቱ ከወደቀ በኋላ ደግሞ ወደሚወዷት ሃገራቸው ተመልሰው በንግድ ስራቸው ቀጥለዋል:: ከዚሁ ጎን ለጎን አሁን በህይወት የሌሉት ባለቤታቸው የከፈቱትን ‹‹አማ›› የተባውን የበጎ አድራጎት ድርጅት በማስቀጠል ለሃገራቸው የበኩላቸውን አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ ይገኛሉ:: በዚህም የበጎ አድራጎት ድርጅታቸው የአካባቢውን ህፃናት በስነምግባርና በእውቀት ተገንብተው እንዲያድጉ ብሎም ተፈጥሮ የለገሰቻቸውን ልዩ ልዩ ስጦታ እንዲያሳድጉ በማድረግ በርካታ ሃገር ተረካቢ ትውልድ ማፍራት ችለዋል::

እንግዳችን የይርጋ ጨፌን የተፈጥሮ ቡና ለአለም ህዝብ ለመጀመሪያ ጊዜ በማስተዋወቅ ለኢትዮጵያ ከፍተኛ የገቢ ምንጭ እንዲሆን ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል:: በዚህም በቅርቡ ከዲላ ዩኒቨርሲቲ እውቅና ተበርክቶላቸዋል:: አዲስ ዘመን ጋዜጣም የይርጋ ጨፌ ቡና አባት እየተባሉ የሚጠሩትን አቶ ሃይሉ ገብረህይወትን የዛሬው የዘመን እንግዳ አድርጎ እንደሚከተለው ይዞላችሁ ቀርቧል::

**አዲስ ዘመን፡- የይርጋ ጨፌ ቡናን ያገኙበትና ለአለም ያስተዋወቁበትን አጋጣሚ ያስታውሱንና ውይይታችንን እንጀምር?**

**አቶ ሃይሉ፡-** ትምህርቴን እንዳጠናቀኩኝ መጀመሪያ የተቀጠርኩት ቤስ በተባለ አስመጪና ላኪ ኩባንያ ውስጥ ነው:: ይህ ኩባንያ አንድሬ በተባለ ፈረንሳይ ባላሃብት የተቋቋመ ሲሆን ለኢትዮጵያ ንግድ ዘርፍ ማደግ ትልቅ መሰረት ጥሎ የሄደ ኩባንያ ነው:: በመላ ሃገሪቱ በሚገኙ ከተሞች ላይ ትልልቅ መጋዘኖችን በመገንባት የወጭና ገቢ ንግድ ስራ ይሰራ ነበር:: በጣም ብዙ ሰው ይቀጥር ነበር:: ከየአካባቢው የሚመረተውን ምርት ወደ ውጭ ይልክ ነበር:: ከውጭም ከመኪና ጀምሮ እስከ ተራ የቤት ቁሳቁስ ድረስ እያስመጣ ያከፋፍል ነበር:: ይሄ ብቻ ሳይሆን በወጭ ንግድ በተለይ ጥራጥሬ፣ ቆዳ፣ ቡና ይልክ ነበር:: እኔ እዚያ ድርጅት ውስጥ ተቀጥሬ የቡና ምርትና ንግድ ዘርፉ ላይ ተመድቤ በምሰራበት ጊዜ አሁን ይርጋጨፌ ቀድሞ ደግሞ መልካ ሎሌ እየተባለ የሚጠራውን ቡና ያገኘሁት::

በነገራችን ላይ ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያ ቡና ከዚህ ቀደም ሳይታጠብ ነበር የሚላከው:: ይህ ድርጅት ግን ማጠብና መፈልፈል ጀምሮ ነበር:: ቡናው ታጥቦና ተዘጋጅቶ ነው የሚላከው:: እናም ሲዳሞ ውስጥ ከይርጋለም ጀምሮ እስከ ይርጋጨፌ ድረስ በየቦታው አልፎ አልፎ ስምንት ጣቢያዎች ነበሯቸው:: የእኔ ስራ የነበረው በየጣቢያዎቹ እየዞርኩኝ የሚዘጋጀውን ቡና ጥራት መከታተል ነበር:: ሃገሩ አንድ መንገድ ነው ያለው:: ጣቢያዎቹ ደግሞ ከመንገድ ወጣ ያሉ ስለነበሩና መንገዱ ድጥ ስለነበር ለመመላለስ አስቸጋሪ ነበር:: በተለይ በክረምት በጣም ያስቸግር ነበር:: ያም ቢሆን የቡና ማምረቻ ቦታዎች እየተዟዟርኩኝ ስራውን እከታተል ነበር::

ይህንን በማደርግበት ጊዜ ቡናውን በመጠኑ እንለይ ነበር፤ የሲዳሞ ቡና በፍሬው አነስ ያለ ነበር፤ አንዳንድ ደግሞ ረጃጅምና ወፈር ያለ ቡና ዝርያዎች ስለነበሩ በመጠናቸው ለይተን እናስቀምጥ ነበር:: ከስምንቱ ጣቢያ የተፈለፈለውን ቡና በምንለይበት ጊዜ የአንዱ ጣቢያ ቡና በጣም ተለየብኝ:: መልኩ በጣም ያምራል፤ ፍሬም ከሌሎቹ ተለቅ ያለ ነው:: ይሄ የቡና ዝርያ ለምን ከሌሎቹ ተለየ? የሚለውን ነገር ማጥናት ያዝኩኝ:: ይህንን የተለየ ቡና ለብቻው አንድ ናሙና እንዲሁም ሌላውን እንዲሁ ለብቻው አዘጋጅቼ አዲስ አበባ የሚገኘው አለቃዬ ጋር ላኩት:: ያን ጊዜ ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ የቡና ቀማሽ አልነበረም፤ ይህንን የሚያደርጉት ገዢዎቻችን ናቸው:: የላኩላትን ናሙናዎች ጀርመንና እንግሊዝ ለቅምሻ ላካቸው:: ሁለቱም ኩባንያዎች ተመሳሳይ የሆነ ግብረ መልስ ነበር የሰጡት:: ይህንን በአይነቱ ለየት ያለውንና ‹‹መልካ ሎሌ›› ብዬ በአካቢው ባለ ወንዝ ስም የሰየምኩት ይህንን ቡና ከሲዳሞ ቡና እንዳንቀላቅል፤ በተቻለ መጠን በብዛት እንድናመርት፤ ለዚህ ቡና ብልጫ ያለ ክፍያ እንደሚከፍሉ ነበር ሁለቱ የውጭ ሃገር ኩባንያዎች በደብዳቤ ያስታወቁን:: ይህንን ስሰማ በጣም ነበር የተደሰትኩት፤ ምክንያቱም በአይኔ አይቼ በቅምሻ ባለሙያዎች ለይተው ያረጋገጡልኝ በመሆኑ ነው::

በጣም በመደሰቴ የተመረተችውን ቡና ለሁለቱም ኩባንያ ሰዎች አካፍለን ላክንላቸው:: እናም ከዚያ ጊዜ ወዲህ እነሱ ባሉት መሰረት እዚያ ጣቢያ ላይ ብዙ ማምረት ጀመርን:: ለምን ይሄ ልዩነት እንደመጣ ለማወቅ ጥናት ማድረግ ጀመርኩኝ:: በእርግጥ ከይርጋጨፌ የሚገኙ ሌሎች ሁለት ጣቢያዎች ነበሩን:: ግን መልካ ሎሌ ቡና ለየት ያለ ነበር፤ አንድም የቡናው ዛፎች ገና ወጣት ወይም ብዙ እድሜ ያላስቆጠሩ ነበሩ:: ብዙዎቹ ቡናዎች ግን ሽማግሌ ዛፎች ነበሩ:: የሚገኙትም ቆቄ ተራራ ላይ ነው፤ የሚታጠበውም ከዚያው መልካ ሎሌ ወንዝ ከሚገኘው ንፁህ ውሃ ነው:: ስለዚህ እነኚህን ልዩነቶች ነው ከሌሎቹ ያገኘሁት::

የሆኖ ሆኖ ይሄ ቡና በጣም ከፍ ባለ ዋጋ መሸጡን ቀጠለ:: የምንሸጠው ቡና በብሔራዊ ባንክ ይመዘገባል:: የመልካ ሌሎ ቡና ዋጋ ግን ሁልጊዜ ከፍ ባለ ዋጋ ነው የሚሸጠው:: ይህንን ያዩ የብሔራዊ ባንክና የእርሻ ሚኒስቴር ሰዎች የቡና ባለሙያዎች ያሉበት አንድ ቡድን አቋቋሙ:: ጣቢያው ድረስ በመሄድ አካባቢውን ማጥናት ጀመሩ:: በእርግጥም እዛ አካባቢ የሚመረተው ቡና ከሌላ አካባቢ ከሚመረተው ቡና የተሻለ ነው:: ስለዚህ ይህንን አረጋገጡና ወደ 19ሺ 500 ሄክታር ከይርጋ ጨፌ ከተማ ዙሪያ ያለውን ቡና ይርጋጨፌ ብለው ሰየሙት::

እያንዳንዱ ከዚያ አካባቢ የሚወጣው ቡና ይርጋጨፌ የሚል ስያሜ ባለው መሸኛ እየተሰጠው ነው እንዲወጣ የተደረገው:: ከዚያ ውጪ ሲዳሞ እየተባለ ነው የሚወጣው:: እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የሲዳሞ ቡና ከሚያመጣው ገንዘብ የይርጋ ጨፌ ቡና የሚያመጣው ገንዘብ በሶስት ሚሊዮን ብር ይበልጥ ነበር:: ይሁንና የቡና ሻይ ከመጣ ወዲህ ደግሞ ቡናው ላይ የነበረው የጥራት ልዩነት ተረሳና ለሁሉም አንድ አይነት ዋጋ ሰጡት:: ኢትዮጵያ ከዚያ ከይርጋጨፌ ታገኝ የነበረው ብልጫ ያለው ክፍያ አጣች:: ይህም የሆነው በእውቀት ስላልተመራ ነው:: እንደሚታወቀው በሃገራችን ብዙ ስህተቶች ይሰራሉ፤ አንዱ የሚታየው ግልፅ የሆነው

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

ስህተት ይሄ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የልማት ባንክ ፕሬዚዳንት ረዳት እንደነበሩ ሰምተናል፤ እስቲ ስለዚህም አጋጣሚ ያጫውቱን?**

**አቶ ሃይሉ፡-** ልማት ባንክ የገባሁት አስመጪና ላኪ ድርጅቱ የኤክስፖርት ክፍሉ ሃላፊ ሆኜ ለሁለት ዓመት ተኩል ከሰራሁ በኋላ ነው፡፡ በነገራችን ላይ ልማት ባንክ የገባሁትም በምክንያት ነው፡፡ የባንኩ ፕሬዚዳንት ዶክተር ቡትከስ የተባለ ጀርመናዊ ሰው ጋር እንተዋወቅ ስለነበር ወደዚያ እንድመጣ ጋበዘኝና ነው ወደዚያ የሄድኩት፡፡ እሱ ወደ ሃገሩ ሲሄድ የሚተካው ኢትዮጵያዊ ለማሰልጠን ቃልገብቶ ስለነበር በዚያ መሰረት ከፍ ባለደመወዝ፤ መኪና ተመድቦልኝ እሱ የሚሰራውን ከስር ከስሩ እየተከተልኩኝ እንድሰለጥን ነው የተደረገው፡፡ ከእርሱ ቢሮ ጎን ያለች ክፍል ተሰጥቶኝ ለባንኩ የሚመጣ ነገር በሙሉ መጀመሪያ የማየው እኔ ነበርኩ፡፡ ቀጥሎም ለእርሱ አሳልፋለሁ፡፡ እርሱም የትኛውንም ነገር በመጀመሪያ የሚሰጠው ለእኔ ነው፡፡ ወይ ያስረዳኛል፤ አሊያም ደግሞ የጨረሰውን ይሰጠኛል፡፡ ዓላማው በባንኩ ውስጥ የሚካሄደውን ነገር በሙሉ እንዳውቅ ነበር፡፡ በዚህም አይነት የእርሱ ረዳት ሆኜ እዛ ሰራሁ፡፡

ቃል ከገባልኝ ውስጥ አንዱ ውጭ አገር ልኬ በኢንዱስትሪ ፋይናንሲንግ ትምህርት መስከ አሰለጥንሃለሁ የሚል ነበር፡፡ በቃሉ መሰረትም ለስድስት ወር ኢንዳስትሪያል ፋይናንሲንግ እንዳጠና እንግሊዝ አገር ላከኝ፡፡ በወቅቱ እኔን ሲልከኝ የእርሱ ኮንትራት ሊያልቅ የቀረው ትንሽ ጊዜ ነበር፡፡ እንግሊዝ አገር እያለሁ የኮንትራት ማደሻ ጊዜው ደረሰ፡፡ እርሱ ለባንኩ የቦርድ አባላት አንድ ሐሳብ በጽሁፍ ያቀርባል፡፡ ይኸውም እርሱ ያጠናውን ሶስት ፕሮጀክቶች ነበር፡፡ እንዴት ፋይናንስ ቢደረጉ ከጀርመን አገር ባንኮች ብድር እንደሚሰጡ እና እነዚህን ሶስት ፕሮጀክቶች በስራ ላይ ቢውሉ ይህቺን አገር በአጭር ጊዜ ለመክፈትና ወደኢንዱስትሪ ወደማኑፋክቸሪንግ ስራ ኢኮኖሚዋ እንዲዛወር ማድረግ ይቻላል ብሎ ሃሳብ አቀረበላቸው፡፡ ይሁንና በሚኒስትሮቹ ተቀባይነት አላገኘም ነበር፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በምን ላይ የሚያጠነጥኑ ፕሮጀክቶች ነበሩ?**

**አቶ ሃይሉ፡-** አንዱ ከአሰብ እስከ አዲስ አበባ ዛሬም ድረስ በቦቴ የሚመላለሰው ነዳጅ የቱቦ መስመር ተዘርግቶለት በቀጥታ ማምጣት የሚያስችል ፕሮጀክት ነበር፡፡ ይህም ይባክን የነበረውን ሃብትና ጉልበት በከፍተኛ መጠን ይታደጋል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት ፕሮጀክት ነበር፡ ሁለተኛ ደግሞ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በኤሌክትሪክ የሚሰራ የአውቶብስ መስመር መዘርጋት ሲሆን ሌላኛው መላ ሃገሪቱን የሚያስተሳስር የባቡር ሃዲድ ዝርጋታ የያዘ ትልቅ ፕሮጀክት ነበር፡፡

ለእነዚህ ፕሮጀክቶች የሚሆን ፋይናንስ ከጀርመን ራሱ እንደሚያስመጣ በወቅቱ ለነበሩት የቦርድ አባላት ቢነግራቸውም ሐሳቡን ሊቀበሉት አልፈቀዱም፡፡ ይልቁንም በየቦታው ብዙ ትምህርት ቤቶች፣ ጤና ጣቢያዎች መከፈት እንደሚፈልጉ፤ ለሚቀጥለው ትውልድ አሁን እዳ ማስተላለፍ እንደማይሹ ገለፁለት፡፡ ይገርምሻል! ይህ ሰው በጣም አዝኖ ‹‹እናንተ የተማራችሁ ሚኒስትሮች ናችሁ፤ አገሪቱን የምትመሩ እናንተ ናችሁ፤ እናንተ እንዲህ ካላችሁማ ይህቺ አገር ማደግ አትችልም›› ብሎ ከእነርሱ ጋር ይጣላል፡፡ ኮንትራቴንም አላድስም በሚል አቁሞ ወደካሜሩን በአገሩ ከሚገኘው በሁለት እጥፍ ደመወዝ ተቀጥሮ ነው የሄደው፡፡ እኔም ለስልጠና ከሄድኩበት ሀገር ስመጣ አንድ ሚኒስትር የነበሩ ሰውዬ ተሹመው አገኘኋቸው፡፡ በእኔ ቦታም ሌላ ሰው ተተክቶ ስለነበር ለእኔ ሲባል ኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን የሚባል ዲፓርትመንት ተቋቋመና ያንን ክፍል እንድመራ ተደረኩኝ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ታዲያ እንዴት ነበር የንግዱን አለም የተቀላቀሉት?**

**አቶ ኃይሉ፡-** ልማት ባንክ አስር ዓመት ካገለገልኩኝ በኋላ ድሮም ቢሆን ነጋዴ የመሆን ህልም ስለነበረኝ ጥዬ ወጥቼ የራሴን የንግድ ድርጅት አቋቋምኩኝ፡፡ አፍሪካን ሴልስ ፓወር የተባለው ይሄው ድርጅት የግንባታ እቃዎችን ያስመጣ ነበር፡፡ ህንጻዎች ሲሰሩ ጣሪያውን ወተርፐሩፍ ያደርግም ነበር፡፡ በነገራችን ላይ ይህንን ስራ ለመጀመሪያ ጊዜ በሃገራችን ያስተዋወቀው የእኛ ድርጅት ነው፡፡ ጳውሎስ ሆስፒታል፣ መርካቶ የገበያ አዳራሽና መሰል የወተር ፐሩፍ ስራዎችን ሁሉ የእኛ ድርጅት ነበር የሚሰራው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከቡና ላኪዎች ቡና እየተረከብኩኝ በቀጥታ ለውጭ ሃገር ገዢዎች በመላክ የወጭ ንግዱ በተሳለጠ መንገድ እንዲሄድ የበኩሌን ሚና ተጫውቻለሁ፡፡



**አዲስ ዘመን፡- ከንግዱ ባሻገር ወደ እርሻም የገቡበት አጋጣሚ ነበር፡፡ እስቲ ያስታውሱን?**

**አቶ ኃይሉ፡-** ልክ ነሽ፤ ወደሻሸመኔ ሲኬድ 190 ኪሎ ሜትር ላይ ወደምዕራብ ወደቀኝ ሶስት ኪሎ ሜትር ላይ በምትገኝ ሜቶ በተባለ ስፍራ ላይ ነው የእርሻ ስራ የጀመርኩት፡፡ ያ አካባቢ ሰፊ ጫካ ነበር፡፡ ያ ሰፊ ቦታ የጃንሆይ የወንድም ልጆች ሳምሶን በየነ እና ወንድሙ ያንን መሬት ጃንሆይ ሰጥተዋቸው መሬቱን እነርሱ በጋሻ አሸነሸኑትና ለሚፈልግ ነጋዴ፣ ዳኛ ፣አስተማሪ ሳይቀር ሰጡ፡፡ ይህንን መሬት የሚሸጠው ሰውዬ ወዳጄ ነበር፡፡ እርሱ አንድ ሃያ ጋሻ ያዝ አለኝ፡፡

እኔ በወቅቱ በጣም ትርፋማ ስራ ሆኖ ያገኙሁት ንግዱን ነውና ምንም እንኳን የገበሬ ልጅ ብሆንም እንደገና ግብርና ውስጥ መግባት አይታየኝም አልኩት፡፡ ይሁንና ከአንተ ላለመለየት ትልቅ ወንዝ አለ፤ እዛ ወንዝ ላይ አንድ ሁለት ጋሻ ያዝልኝ አልኩት፡፡ እርሱ ለመስኖ የሚመች ሶስት ጋሻ ያዘልኝ፡፡ ግን ሥራ የጀመርኩት ከሁለት ዓመት በኋላ ነበር፡፡ ባለችኝ ሶስት ጋሻ ላይ እርሻዬን አለማሁ፡፡ በነገራችን ላይ እዛ አካባቢ ያለው ነዋሪ የሚተዳደረው በከብት ርቢ ላይ ነበር፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ትንሽ ትንሽ በቆሎ ያመርታሉ እንጂ እርሻ አያውቁም ነበር፡፡ ስለዚህ ለዚህ ገበሬ ያሳየሁት ነገር ቢኖር ትራክተር እስጣቸውና የእነርሱን መሬት ሄዶ ያርስላቸዋል፡፡ በሰዓት አስር ብር ደግሞ ይታሰባል፡፡ የቦለቄ ዘርና ማዳበሪያም እኔ አቀርብላቸዋለሁ፡፡ ይህን የሚከፍሉት ደግሞ የጉልበት ስራ በመስራት ነው፡፡ በተጨማሪም የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ወሰድኩና እዛ ያሉትን የእነርሱን ልጆች ማስተማር ጀመርኩ፡፡ በአካባቢው ክሊኒክም ሆነ ትምህርት አልነበረም፡፡ በመሆኑም የእነርሱን ልጆች ማስተማር ጀመርኩ፤ እናም ገበሬዎቹ ህይወታቸውን በአንድ ጊዜ ለወጡ፡፡ ይሔ የሚያሳየው የእኛን ገበሬ ኑሮ ወይም ሕይወት ለመቀየር እንዴት እንደሚቻል ነው፡፡ በዚህ መልክ ስንሠራ ደርግ መጣና መሬት ላራሹ አለ፡፡ ያለንን የእርሻ ስፍራና የንግድ ቦታ በሙሉ ወረሰብንና ሥራውን ዘግተን እኛም ወጣን፡፡ የሚያሳዝነው ግን ያ ቦታ ተመልሶ ጫካ መሆኑ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች የኢትዮጵያን ዕድሏን ነው ያኮላሹት፡፡ አሁንም ይህ ምን ምን ዓይነት ዕድል እያመለጠን እንደመጣ ያሳያል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እርሶ መሬት ላራሹ የሚለውን የደርግ አዋጅ አይደግፉትም ማለት ነው?**

**አቶ ሃይሉ፡-** እንደሱ ለማለት ሳይሆን ከእኛ ተቀምቶ ሲያበቃ ገበሬውም የመሬት ባለቤት ያለመሆኑ ነው የሚያሳዝነኝ፡፡ በእርግጥ ደርግ በመምጣቱ ብዙ ነገር መጥቷል፡፡ አንደኛ የከተማን ትርፍ ቤት በመውረሱ ኢትዮጵያኖችን ድሃ አድርጓል፡፡ ሁላችንም መሠረታችን መሬት ነው፡፡ ግብርና ነው፡፡ ከተማም መጥተን አከራይተን የምንኖረው እና የምንሻሻለው በራሳችን ጥረት ነበር፡፡ ነገር ግን መንግስት ድሃ አደረገን፡፡ እርሱ የሶሻሊስትን ስርዓት አምጥቶ የማምረቻውን ሃይል መንግስት ይዞ እያመረተ የህዝቡን ኑሮ ማሻሻል በፅንሰ-ሃሳቡ ውስጥ ወይም በወረቀት ያለ ነበር፡፡ በተግባር ግን አልሆነለትም፡፡

ደርግ ሲወድቅ ወደ ድሮው ቦታ መመለስ ሲገባው አልተመለሰም፡፡

የተወረሰው ቤትም ሆነ መሬት መመለስ ሲኖርበት አልተመለሰም፡፡ ይልቁኑ ለኢህአዴግ መንግስት ያ ለእርሱ ትልቅ ገቢ ሆነ፡፡ ጥንካሬው እርሱ ነው፡፡ ቤት ያከራያል፡፡ የፈለገውን ይጨምራል፡፡ እርሱ ሃብታም ሆነ፡፡ ድሃው ቢሰቃይ የራሱ ጉዳይ ተባለ፡፡ ስለዚህ ያ ስርዓት ለሰፊው ሕዝብ ሳይሆን ለገዢው መደብ ነው የጠቀመው፡፡ የሚገርምሽ በኢህአዴግም ጊዜ ከጓደኛዬ ጋር እርሻ ጀምረን ነበር፡፡ አፋር ገዋኔ ላይ ሰባት ዓመት የጥጥ ሥራ እንሰራ ነበር፡፡ ለመጥረጊያ የሚሆን አገዳም እናመርት ነበር፡፡ እርሱ እዚህ አገር አልተለመደም፡፡ ያንን እያመረትን ወደ ውጪ እንልክ ነበር፡፡ ሁለተኛ ጥጥ እናመርት ነበር፡፡ ሌላም የግብርና ሥራ እንሠራ ነበር፡፡

አንድ ጥሩ ኢትዮጵያን ይጠቅማል ብለን ማሾ ማምረት ጀምረንም ነበር፡፡ ይህች ምስር ማሳይ ዘር በተዘራች በሁለት ወር ውስጥ ትደርሳለች፡፡ በዓመት ሁለት እና ሶስቴ ማምረት ይቻላል፡፡ ወደ ውጪ ስትላክ ዋጋዋ ከሌላው በልጦ ቁጭ አለ፡፡ ከሁመራ ሰሊጥ በላይ የምትሸጠው ማሾ ነበረች፡፡ እርሷን ማምረት ጀምረን ነበር፡፡ የሆነው ሆኖ የአፋር የመሬት አያያዝ አስቸጋሪ ነው፡፡ መሬቱን የሚያኮናትረው የሚመረጥ የሽማግሌ ስብስብ ነው፡፡ እነርሱ ካልፈለጉ ነጥቀው ለሌላ ይሰጣሉ፡፡ እኛ ላይም ይኸው ሆነ፡፡ የምንሰራበትን መሬት ኮንትራት እያለን፤ ሌላ ገንዘብ ለሰጣቸው ሰጡት፡፡ እኛ ከእነርሱ ጋር አንጨቃጨቅም ብለን ወጣን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከሃገር የወጡበት ምክንያት ምን ነበር?**

**አቶ ሃይሉ፡-** እንዳልኩሽ የደርግ አጠቃላይ ሁኔታ ለእኛ ጥሩ አልነበረም፡፡ ለዚህም ነው ግማሹን የደርግ ዘመን የምንኖረው አሜሪካን የኖርነው፡፡ እዚህ ስላልተመቸን ቤተሰቤን ይዤ አሜሪካ እኖር ነበር፡፡ እነመለስ ሲመጡ ወዲያው ሮጠን ተመለስን፡፡ ሥራዬን እንደገና ቀጠልኩ፡፡ ባለቤቴም የበጎ አድራጎት ድርጅት አቋቋመች፡፡ አሁን እርሷ ከሞተች 15 ዓመት ቢሆናትም እኛ ተረክበን እያስቀጠልነው ያለነው፡፡ በነገራችን ላይ ድርጅቱ ከተቋቋመ 29 ዓመቱ ነው፡፡ አሁን ትልቁ ህልማችን ይህንን ሥራ ማስፋፋት ነው፡፡ መንግስት መሬት ሰጥቶናል፡፡ እዛ ላይ ሕንፃ ሰርተን ከፍ ከፍ ያለ ስልጠናን የመስጠት ዕቅድ ይዘናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የተራድኦ ድርጅት ሆና ነገር ግን የስልጠና ተቋም ይሆናል ማለት ነው?**

**አቶ ሃይሉ ፡-** አዎ! እናስከፍልም በነፃ ስልጠና እንሰጣለን፡፡ አሁንም በምግብ ስራና በተለያዩ የሙያ መስኮች የተቸገሩ ዜጎችን እናሰለጥናለን፡፡ ከዚህ ቀደምም ከአረብ ሃገር የተመለሱ በርካታ ሴቶችን አሰልጥነን ሥራ እንዲያገኙ አድርገናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የገቢ ምንጫችሁ ምንድን ነው?**

**አቶ ሃይሉ ፡-** ከድሮ ጀምሮ ግብርና ላይ ነኝ፤ ምርት ወደ ውጪ እልካለሁ፡፡ ከደንበኞቼ መካከል አንዱ የአሜሪካን ኩባንያ ባለስልጣናት ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ የእኛን ድርጅት አሳየናቸው እና ነገርናቸው፡፡ ልጆቹ እናት አባት የሌላቸው እና በጣም ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ቤተሰብ የመጡ መሆናቸውን ነገርናቸው፡፡ እንግዲያው እኛ እንረዳችኋለን፤ የእኛ ሰራተኞችም ይረዱችኋል ብለው የእነርሱ ሰራተኞችም ስፖንሰር ማድረግ ጀመሩ፡፡ ለአንድ ልጅ በዓመት 200 ዶላር ነበር፡፡ አንዱ አንድ እና ሁለት ልጅ እየረዱ ይህንን እያካሔድን ነበር፡፡ ነገር ግን ኮቪድ ከተከሰተ በኋላ ኩባያው ከሶስት ሺ በላይ ሰራተኞችን አስወጣ፤ ስለዚህ እኛም አሁን የምናገኘው ገንዘብ ትንሽ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት የምንረዳቸው ልጆች ብዛት ከ130 ወደ 50 ዝቅ ብሏል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የእርዳታ ተቋሙ የተጀመረው ባለቤትዎ ትውልዱ ላይ ባዩት የሥነምግባር ችግር ምክንያት ያንን ለመቀረፍ ሲባል ታስቦ መሆኑን ሰምቻለሁ፡፡ ይህንን መነሻ በማድረግ አሁን ትውልዱ ላይ የሚታየውን ችግር በምን መልኩ ማረቅ ይቻላል ብለው ያምናሉ?**

**አቶ ሃይሉ ፡-** ይሄ ጉዳይ ሁላችንንም እያሳሰበን ያለ ነገር ነው፡፡ በተለይ በእድሜ ጠና ያልነው ማለትም እንደ እኔ ሶስት አገዛዞችን ያየን ሰዎች ያሳስበናል፡፡ በጣም ቁልጭ ባለ መልክ ኢትዮጵያ ከምን ወደ ምን እየመጣች እንደሆነ እየታዘብን ነው፡፡ በአፄ ሃይለስላሴ ጊዜም ሆነ በደርግ ጊዜ የብሔር ልዩነት ብሎ ነገር የለም፡፡ እኔ ሳገባ ብታምኑም ባታምኑም እኔ አማራ ብሆንም ሚዜዎቼ ግን ሁለቱ ኦሮሞ አንዱ አማራ ነበር፡፡ ይሄ ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡ አሁን ልዩነት ላይ መሰረት ያደረገው ሃገራዊ ችግር ገዝፎ ነው የሚታየው፡፡ ፅንፍ የያዙ ሃሳቦች ናቸው ወጣቱ እያራመደ የሚታየው፡፡ በእኛ ጊዜ ዘር ቆጠራ የሚባል ነገር አልነበረም፡፡ ይሄ አይነቱ ልዩነት ወደ ጫፍ በመድረሱም ነው በምዕራብ ወለጋም ሆነ በተለያዩ የሃገሪቱ አካባቢዎች ጭፍጨፋና ግድያ እየሰፋ የመጣው፡፡ ይህ አይነቱ ጭካኔ በፊት ለነበረው ለእኔ አይነቱ ትውልድ በጭራሽ የማይገባው ነገር ነው።

ይህ አይነቱ ጎሳ እየቆጠሩ የሚደረግ ጭፍጨፋ በየትም የአለም ሃገር ላይ የሚታይ አይደለም፡፡ አሜሪካ ከአለም የተፈጠረ ህዝብ ሁሉ የሚኖርባት ሃገር ናት ፡፡ እዚያም በመኖሬ አውቃለሁ፡፡ እዚያ ሃገር ትልቁ ቁም ነገር በዘር መለያየት ሳይሆን በስራና በእውቀት በልጦ መገኘት ነው፡፡ ይሄ ነው ቁም ነገሩ እንጂ አንተ መጥፋት አለብህ ፣ አንተ መስራት የለብህም የሚባል አመለካከት የለም ፡፡ ስለዚህ አሁን በእኛ ሃገር ላይ እየሆነ ያለው ነገር ለቀደምነው ትውልዶች ግራ የሚያገባ ነው። ይህንን ልዩነትም አናውቀውም ፡፡ እንዲህ አይነቱነ ችግር ጊዜ ነው የሚያስተካክለው። አስተሳሰቡ ጉዜያዊ ነው። በጣም መርዛማ የሆኑ አስተሳሰቦች አሁንም አለ፤ እኛ ከዩኒቨርሲቲ ከወጣን በኋላ ነው መሬት ላራሹ የሚለው አስተሳሰብ የመጣው። እኛ ባለን ጊዜ አልነበረም መሬት ላራሹ። አሁን ቁም ነገሩ ተመርን የሚሉት እሳቱን እፍ እፍ የሚሉት ትንሽ ሰዎች ናቸው፡፡ እነሱ ማስተካከልና ማረቅ ደግሞ ከባድ አይሆንም ብዬ ነው የማስበው፡፡

ይህች ሀገር የአማኝ ሀገር ናት ፤ እስልምና ክርስትና ሌላውም የተስፋፋበት ሀገር ነው። የእነዚህ ሁሉ እምነቶች ትምህርት የበጎ ነው እንጂ የክፋት አይደለም።በግብረ ገብ በጎ ትምህርት የተስፋፋበት ነበር። አሁንም ለወጣቱ ትምህርቱን ማስፋፋት ያስፈልጋል። በእርግጥ ይሄ ትውልድ ያለፈውንና አሁን እየሆነ ያለውን እየታዘበ ነው የሚመጣ። ይሄ አፍርጦ ማስረዳት ያስፈልጋል። እየተደረገ ያለው ስህተት ምን እንደሆነ ማወቅ አለበት። በግብረገብ ትምህርት የትውልዱን አስተሳሰብ መቅረጽ ነው። ኢትዮጵያ ፈጣሪዋ አይጥላትም፤ ወድቃም ተንከባላም ቢሆን ትነሳለች።

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት የሃገሪቱ ኢኮኖሚ ካገጠመው ፈተና እንዴት መውጣት ይችላል ብለው ያምናሉ**

**አቶ ኃይሉ ፤** አሁን የተከሰተው ችግር በኢትዮጵያ ብቻ አይደለም ። ቀውስ ሲመጣ ኢኮኖሚ ይዛባል፤ በሚዛባበት ጊዜ የኢኮኖሚው መሰረታዊ አቋሙ ደካማ በሚሆንበት ጊዜ ይበልጥ ይዛባል። በእርግጥ እኛ ብዙ አናመርትም፤ አሁንም አብዛኛው ምርት የሚመጣው በበሬ የታረሰ ነው። በዚህ ዘመን በበሬ ማረስ ሀጥያት ነው። በዚህ ዘመን በዘመናዊ መንገድ በትራክተር፣ በኮምባይነር ነበር ማምረት ያለብን ።ሆኖም አሁን ተጀምሯል። ዶክተር ዐቢይ እንዳለውም በዘመናዊ መንገድ በጣም ብዙ ስንዴ እየታረሰ ነው። ይህን ማድረግ የነበረብን ግን የዛሬ 20 ና 30 ዓመታት ነበር፤ ያኔ አድርገን ቢሆን ኖሮ አሁን እኛ ከሌሎቹ ሀገሮች በላይ ማምረት እንችል ነበር።

ኢኮኖሚው ለምን እንደዚህ ሆነ ከተባለ ስላልሰራን ነው።አመት ሙሉ መስራት አለብን ። ምክንያቱም ይች ሀገር በጣም ትልቅ አቅም አላት። አሁን ያለው ችግር እንዴት ይቀረፋል ለሚለው አላውቅም! ነገር ግን የሚሰራ ሳይሆን የሚበላ እያፈራን ነው። አሁን የምለው የዚህ ሀገር የኢኮኖሚ ችግር የሚፈታው በመስራትና በመስራት ብቻ ነው። ከችግር መውጪያ መድሀኒቱ መስራት ብቻ ነው ።

**አዲስ ዘመን፡- ስነበረን ቆይታ በአንባቢዎቼና በዝግጅት ክፍሉ ሥም ከልብ አመሰግናለሁ**

**አቶ ሃይሉ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# ማህደረ ጤና

## ድምጹን አጥፍቶ የዓይን ብርሃንን የሚሰርቀው ግላኮማ

**እፀገነት አክሊሉ**

ከሰውነት ክፍላችን ትልቁን ቦታ የሚይዘው ብዙዎች እንደሚስማሙበትም የጉልበት ዘርፍ የሆነው አይናችን ከፍ ያለ ጥንቃቄን ይሻል:: በመሆኑም ለአይናችን የምንሰጠው ጥንቃቄና የምናደርግለት ክትትል ከሌሎች የሰውነታችን ክፍሎች ከፍ ያለም ሊሆን ይገባል::

የጤና ባለሙያዎችም እንደሚሉት ሰዎች በተለይም እድሜያቸው ከ 40 ዓመት በላይ ሲሆን በየጊዜው ወደጤና ተቋማት በመሄድ የአይናቸውን ጤንነት ማረጋገጥ ይገባቸዋል:: ይህንን ባደረጉ መጠን ደግሞ ቀስ በቀስ በአይናቸው ላይ ከሚከሰትና ምናልባትም የአይን ብርሃናቸውን ሊያሳጣ ከሚችል ከፍ ያለ ጉዳትም ራሳቸውን ያድናሉ ሲሉም ይመክራሉ::

ድምጽ አጥፍቶ የአይን ብርሃንን ከሚሰርቅ በሽታ አንዱ ደግሞ ግላኮማ ነው:: ግላኮማ ምንም ምልክት ሳያሳይ ቀስ በቀስ እየሄደ የአይን ብርሃንን እስከ ማጥፋት የሚደርስ የአይን እክል ሲሆን አይኑን ቶሎ ቶሎ በህክምና ባለሙያ የሚያሳይ ሰው ግን በዚህ በሽታ የመጠቃት እድሉ ዝቅተኛም ስለመሆኑ ነው ባለሙያዎች የሚናገሩት፤ ምናልባት በጤና ባለሙያ የዓይን ግፊት ህመም (ግላኮማ) እንዳለብዎት ወይም ለዚሁ ችግር ከሌሎች በበለጠ ተጋላጭ እንደሆኑ ተነግሮዎት ይሆናል። አለያም ደግሞ በዓይን ግፊት ህመም የተያዘ (የተጠቃ) ሰው ያውቁ ይሆናል። ስለግላኮማ ምንም ሰምተው ላያውቁም ይችላል። ያም ሆነ ይህ ግን ግላኮማ ምንድን ነው? በሽታው ሲከሰት የሚኖረው ምልክት እንዴት ይገለጻል? በእይታችን፣ በኑሯችን ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖስ ምን ይመስላል? የህክምናው ዓትነት እንዴት ይገለጻል? የመከላከለያ መንገዶቹ ምንድን ናቸው? የሚሉ ነጥቦችን በዚህ ጽሁፍ ለመዳሰስ እንሞክራለን።

### የዓይን ግፊት ህመም (ግላኮማ) ምንድን ነው?

ግላኮማ በብርሃን አማካኝነት ዓይናችን የሚቀበለውን መረጃ ለአንጎላችን የሚያደርሰውን እይታ ነርቭ የሚያጠቃ የዓይን ጤና ችግር ነው።

እይታ ነርቭ ብለን የምንጠራው ልክ እንደ ኤሌክትሪክ ገመድ ጥቃቅን ሽቦ (ክር /ሐረግ/) መሰል ነገሮች የተሠራ በመሆኑ የዓይን ግፊት ከሚፈለገው በላይ ጨምሮ በእነዚህ ጥቃቅን የነርቭ (ገመዶች) ላይ ጉዳት ሲያደርስ ጉዳት የደረሰበት የነርቭ ክፍል መረጃ ለአንጎላችን በበቂ ሁኔታ ማድረስ (ማቀበል) ስለማይችል ጉዳቱ በደረሰበት የዓይን ክፍል የማየት ችሎታ ይቀንሳል። ይሁን እንጅ በእይታ ነርቭ ውስጥ የሚገኙት የነርቭ ሐረጎች የጉዳት መጠን የከፋ ደረጃ እስኪደርስ በግላኮማ የተጠቃ ሰው ችግሩ መከሰቱን ሳያውቅና ህመም ሳይሰማው ለብዙ ጊዜ ሊቆይ ይችላል።

የጉዳቱ መጠን እየጨመረ ሄዶ በከፍተኛ ደረጃ ወይም ሙሉ በሙሉ ነርቩ ሲጎዳ ምንም የብርሃን መረጃ ከዓይን ወደ አንጎል ስለማይደርስ ዓይነ ስውርነት ይከሰታል።

የኤሌክትሪክ ገመድ ጥቃቅን ሽቦዎች ጉዳት ቢደርስባቸው (ቢበጠሱ) ጉዳት የደረሰበትን (የተበጠሰውን) በመጠገን ወይም ገመዱን ሙሉ በሙሉ በመቀየር አገልግሎት ማግኘት የሚቻል ቢሆንም በእይታ ላይ ነርቭ ሐረጎች ላይ ጉዳት ሲደርስ ግን በምንም አይነት መንገድ ጥገና አድርጎ ወይም ቀይሮ የእይታ መቀነስን ወይም ዓይነ ስውርነት ማስተካከል አይቻልም።

በሌላ አነጋገር ግላኮማ ድምጹን አጥፍቶ የዓይን ብርሃንን (እይታን) የሚያጠፋ ወይም የሚሰርቅ አስከፊው የዓይን ህመም ነው። ቀስ በቀስ የእይታ አድማስን እያጠበበና የቀጥታ እይታን እያዳከመ ለዓይነ ስውርነት ይዳርጋል ::

**ለግላኮማ ህመም የሚደረጉ ዋና ዋና የህክምና አይነቶች በሦስት ይከፈላሉ ፤ የመድኃኒት ህክምና፣ የብርሃን ጨረር (ሌዘር) ህክምናና የዓይን ግፊት ቀዶ ህክምና ናቸው:: እነዚህ ህክምናዎች ዋና አላማቸውም የዓይን ግፊትን በመቀነስ ተጨማሪ ጉዳት እንዳይደርስ መከላከልና የጉዳቱ መጠን እንዲቀንስ ማድረግ ብቻ ነው**

ስለሆነም የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ ብቸኛው መፍትሄ ግላኮማው የከፋ ጉዳት ሳያደርስ እንዲታወቅ ወቅታዊና ተገቢ የዓይን ምርመራ ማድረግና ጉዳቱንም ለመቀነስ የሚያስችሉ የተለያዩ የህክምና አማራጮችን መጠቀም ነው።

ግላኮማ በዓለም ላይ ዓይነ ስውርነት በማምጣት ከዓይን ሞራ ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ የሚገኝ ሲሆን በሀገራችንም ከዓይን ሞራና ዓይን ማዝ በመቀጠል በሦስተኛ ደረጃ የሰዎችን ብርሃን በመንጠቅ ይጠቀሳል። በዓይን ሞራ እንዲሁም በዓይን ማዝ የሚመጣን ዓይነ ስውርነት በቀዶ ህክምና ሰዎች ችግሩ ከመከሰቱ በፊት ወደነበራቸው እይታ ወይም ተቀራራቢ የእይታ መጠን መመለስ ሲቻል በግላኮማ ምክንያት የመጣን የእይታ መቀነስ (ዓይነ ስውርነት) ግን መመለስ አይቻልም። ለዚህም ነው የግላኮማ ችግር አሳሳቢና አስጊ የሚሆነው። ስለዚህ የህክምናው ዋና አላማ ህመሙ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ ተጨማሪ ጉዳት እንዳያደርስና የጉዳቱ መጠን እየከፋ እንዳይሄድ ማድረግ ነው። ይህን እውነታ ችግሩ ያለባቸው ወይም ለችግሩ ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች በደንብ ሊገነዘቡት ይገባል።

በተጨማሪም እንደ ዓይን ሞራ በአንድ ጊዜ ህክምና ሊድን የማይችል በመሆኑ ችግሩ ከታወቀ ጊዜ ጀምሮ ያለማቋረጥ በሕይወት ዘመን ሙሉ ክትትል ማድረግን ይጠይቃል።

### ግላኮማ በምን ምክንያት ይመጣል?

እንደማንኛውም የአካል ክፍል ዓይናችንም የሚጠበቅበትን የማየት ሥራ እንዲሠራ (እንዲያከናውን) የተለያዩ ነገሮች ለምሳሌ አየር፣ ውኃ፣ ምግብና ሌሎች ንጥረ ነገሮች ያስፈልጉታል። ዓይናችን የያዘውን የኳስ መሰል ቅርጽ እንዲይዝ ያስቻለው ዓይናችን ውስጥ ያለው ውኃ መሰል ፈሳሽ ሲሆን ይህ ፈሳሽ የዓይንን ቅርጽ ከመጠበቅ በተጨማሪ ለተለያዩ የዓይን ክፍሎች አስፈላጊ ንጥረ ነገሮችን የማድረስና በጊዜ ሂደት የሚፈጠሩ (ጥቅም ላይ የዋሉ) ንጥረ ነገሮችን ከዓይን የማስወገድ ሥራ ይሠራል።

የዓይን ኳስ የሚጠበቅበትን አገልግሎት ለመስጠት ከውስጥ በቂ የሆነ የግፊት ኃይል (አየር) ሊኖረው ይገባል። ኳሱ ውስጥ ያለው የግፊት መጠን ከበዛ ወይም ካነሰ በኳሱ ላይ ጉዳት ይደርሳል። በተመሳሳይም ዓይናችን ውስጥ ያለው ፈሳሽ ሲበዛ ወይም ሲያንስ ዓይን ሥራውን በአግባቡ የማይወጣ ከመሆኑም ባሻገር በዓይናችን ላይ አካላዊ ጉዳት ይደርሳል።

ከላይ እንደተገለጸው ግላኮማ የሚከሰተው በዓይናችን ውስጥ ያለው ዓይነ ውኃ ከሚፈለገው በላይ ተጠራቅሞ (የዓይን ግፊት ጨምሮ) ከዓይን ወደ አንጎል መረጃ በሚያስተላልፈው (በሚያቀብለውዉ) ነርቭ ላይ ጉዳት ሲያደርስ ነው። በደምሳሳው ግላኮማ የሚከሰተው በዓይን ውስጥ የሚገኘው የፈሳሽ መጠን የግለሰቡ ዓይን ከሚቋቋመው በላይ ተጠራቅሞ የዓይን ግፊት በእይታይ ነርቭ ላይ ጉዳት ሲያደርስ ነው።

### ለግላኮማ የሚያጋልጡ ነገሮች ምንድን ናቸው?

ምንም እንኳን ዘር፣ ፆታ፣ እድሜ፣ ሃይማኖት ሳይመርጥ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል የሚያጠቃ ቢሆንም ለዚህ ችግር ሊያጋልጡ የሚችሉ ዋና ዋና ነገሮች የሚከተሉት ናቸው። የእድሜ መጨመር (አርባ ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ለግላኮማ ተጋላጭነታቸውም እየጨመረ ይሄዳል፤ የጥቁር (የአፍሪካ) ዝርያ፣ከቤተሰብ ማለትም ከእናት፣ ከአባት ፣ከእህት፣ ከወንድም አንዱ በግላኮማ የተያዘ ከነበረ ሌላውም የቤተሰብ አባል በበሽታው የመያዝ እድሉ ከሌሎች ጋር ሲነጻጸር ከፍ ያለ ይሆናል፤አጠቃላይ የሰውነት ህመሞች ለምሳሌ የስኳር ፣ ደም ግፊት፣ የልብ ና ከፍ ያለ የራስ ምታት (ሚግሬይን) ያለባቸው ሰዎች ፤በመነጽር ሊስተካከል የሚችል የእይታ ችግር በቅርብ፣ በርቀት የማየት፤ በአደጋ ወይም በሌሎች ህመሞች ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ዓይን ከሆነ ፤ የዓይነ መስታወት ውፍረት መቀነስ ወይም ስስ ዓይነ መስታወት፤ ለረጅም ጊዜ ሳይቋረጡ የሚወሰዱ መድኃኒቶች ለትራኮማ አጋላጭ ተብለው በባለሙያዎች ይገለጻሉ።

### ግላኮማ መኖሩ የሚታወቀው እንዴት ነው?

አንድ ግለሰብ ግላኮማ እንዳለበት ሊያውቅ የሚችልበት ብቸኛው መንገድ ልምድ ባለው ዓይን ሀኪም ሙሉ የዓይን ምርመራ ተደርጎለት ሲረጋገጥ ብቻ ነው። በዚህም አንድ ሰው ግላኮማ እንዳለበት ወይም እንደሌለበት ለማወቅ የሚከተሉት መሠረታዊ ምርመራዎች ። የዓይን ግፊት መለካት፤የዓይነ መስታወት ውፍረት መለካት፤እይታን ነርቭን በልዩ መሣሪያ ማየትና ጉዳት ካለም የጉዳቱን መጠን መለካት፤ የእይታ አድማስን በልዩ መሣሪያ መለካት ሲሆኑ ከላይ የተጠቀሱት ምርመራዎች ከተደረጉ በኋላ ሀኪሙ አንድ ሰው ግላኮማ እንዳለበት ወይም እንደሌለበት፤ ካለም የጉዳቱ መጠን ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ገምግሞ የሚያስፈልገውን የህክምና አማራጭ ከህመምተኛው ጋር በመወያየትና በመምከር ውሳኔ ይሰጥበታል። በምርመራው ወቅት ግላኮማ የሌለባቸው ነግር ግን በግላኮማ የመያዝ እድላቸው ከፍተኛ ለሆኑ ሰዎች መደበኛ የሆነ ዓመታዊ የዓይን ምርመራ እንዲያደርጉ ምክር ይሰጣቸዋል።

### የግላኮማ ህክምና ምንድን ነው?

አንድ ግላኮማ ያለበት ሰው ሊያውቀውና አምኖ ሊቀበለው የሚገባው ነገር በግላኮማ ምክንያት የመጣ የእይታ መቀነስ በምንም አይነት የህክምና ዘዴ ወደ ነበረበት ሊመለስ እንደማይችል ነው። በመሆኑም የሚደረግለት ህክምናም የበለጠ ወይም ተጨማሪ ጉዳት እንዳይደርስ ለመከላከልና ያለውን እይታ ባለበት ጠብቆ ለማቆየት መሆኑን ጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል።

ለግላኮማ ህመም የሚደረጉ ዋና ዋና የህክምና አይነቶች በሦስት ይከፈላሉ ፤ የመድኃኒት ህክምና፣ የብርሃን ጨረር (ሌዘር) ህክምናና የዓይን ግፊት ቀዶ ህክምና ናቸው:: እነዚህ ህክምናዎች ዋና አላማቸውም የዓይን ግፊትን በመቀነስ ተጨማሪ ጉዳት እንዳይደርስ መከላከልና የጉዳቱ መጠን እንዲቀንስ ማድረግ ብቻ ነው::

### ግላኮማ የሌለበት ሰው ምን ሊያደርግ ይገባል ?

ጠቅለል ባለ መልኩ የሚከተሉትን መሠረታዊ ነጥቦች ልብ ማለት ከተቻለ ሰዎች እይታቸውን ለመጠበቅ፤ ግላኩማ ከተከሰተም ጉዳቱን ለመቀነስ ይችላሉ።

እድሜያቸው ከአርባ ዓመት በላይ ከሆነ፣ በቤተሰብ የግላኮማ ችግር ካለ ወይንም ያለበት ሰው ካለ፣ ሌሎች ለግላኮማ የሚያጋልጡ የጤና ችግሮች ካሉ ግላኮማ የሚያመጣውን ጉዳት መከላከል ስለሚቻል ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የዓይን ምርመራ ማድረግ በጣም ወሳኝ ነው፤ በሌላ በኩልም የግላኮማ ምርመራ የሚደረግባቸውንና በአቅራቢያ የሚገኙ የመንግሥትና የግል ጤና ተቋማት ማወቅ፤ ስለግላኮማ ያለዎትን እውቀትና ግንዛቤ በተለያዩ መንገዶች ማዳበርና እንዴት እይታዎን ሊጎዳ እንደሚችል መገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነው::

ከ40 ዓመት በኋላ የተለመደ ፣ የዓይን ግፊት የደም ግፊት ለግላኮማ የመጀመሪያ ተጋላጭነት የሚጨምር ጊዜ በመሆኑ እድሜው በዚህ ውስጥ ያለ ሰው በሙሉ በየጊዜው ወደጤና ተቋማት በመሄድ የአይን ግፊት መጠንን መለካት ችግሩም ካለ በቶሎ እርምጃ ለመውሰድ የሚያግዝ ብሎም እንደ እድል ሆኖ ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል በመሆኑ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል።

# ነፃ ሃሳብ



በ(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## «ላብ ደምን ያድናል»

### የሁለት ሙያዎች ወግ፤

በተቀራራቢ ዲሲፕሊንና ሥነ ሥርዓት ራሳቸውንና አባላቱን ሳይንገራገጩ በመምራት አክብሮት ከተጎናጸፉ የዓለማችን ዕድሜ ጠገብ ተቋማት መካከል ሁለቱ የሚሊቴሪና የፍትሕ ኢንስቲትዩሽን በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ።ሁለቱ ነባር ተቋማት የሰው ልጅ ራሱን በቡድን አደራጅቶ መኖር ከጀመረበት ጥንተ ዘመን ጀምሮ የነበሩና ያሉ ናቸው።ዛሬም ድረስ ሳይናወጡ እንደጸኑና እንደተከበሩ በሙሉ ሞገሳቸው የመሰንበታቸው ምሥጢርም በእጅጉ መደጋገፍ በመቻላቸው ነው፡፡

እነዚህ ሁለት ተቋማት የሚወደሱት የረጅም ዘመናት የዕድሜያቸው የሽበት ፀጋ ግድ ስለሚል ብቻ ሳይሆን እጅጉን በመቆራኘት ስለሚኖሩ ጭምር ነው።ይደጋገፋሉ ከማለት ይልቅ መሠረታዊ ባህርይ ይወራረሳሉ ማለቱ የተሻለ ገላጭ ነው።ከየትኛቹም የዓለማችን የሙያ ዘርፎች መካከል ከተቋም እስከ ግለሰብ በጥብቅ ሕግጋት፣ ሥነ ሥርዓትና ዲሲፕሊን የሚመራው የወታደርነት ሙያ ነው።

«ምንም አይደል» ይሉት አባባል በወታደራዊ ተቋም ውስጥ ቦታም ሆነ ከበሬታ የለውም።«አድርግ» ወይንም «አታድርግ» የአንድ ወታደር ክልኤቱ ትእዛዛት ናቸው።«ባላደርግስ?» ዓይነት መልስ ከወታደር አንደበት የራቀ ነው።ስለዚህም ነው ወታደራዊና የሕግ መርሆዎች ቁርኚታቸው ከመደጋገፍም ከፍ ብሎ የዝምድና ያህል ተጣምረዋል የሚባለው።

«ላብ ደምን ያድናል» የተለመደ የወታደራዊ ብሂል ብቻ ሳይሆን እንደ ሕግ የሚቆጠር የፀና መርህ ጭምር ነው።ወታደራዊ ሕግና ደንብ ሲመች የሚፈጽሙት ሳይመች የሚያመቻምቹት ሳይሆን ትዕዛዙ የእዝ ሰንሰለቱን ጠብቆ የሚተገበረው እንደወረደ ሳይሸራረፍ ነው።የአንድ ወታደር የጊዜ ሰሌዳ በሕግና በሥርዓት የሚተረጎም እንጂ ለይምሰል ወይንም ስለተባለ የሚነደፍ አይደለም።

እልህ አስጨራሹን ወታደራዊ ሥልጠናና ዲስፕሊን ለመግለጽ ሲፈለግም «ላብ ደምን ያድናል» መርህ በጥብቅ ሕግ በተግባር ይተረጎማል።እያላበውም ሆነ እያነባ በሥልጠናና በዲስፕሊን የሚመራ ወታደር በግዳጅ ቀጣናው ድልን መጎናጸፉ አይቀሬ ነው።ከግዳጅ በፊት ሥልጠናና ላብ በአግባቡ ተጣምረው ከተተገበሩ የሕይወትና የአካል መስዋዕትነትን የማስቀረት ወይንም የመቀነስ ዕድሉ ከፍ ያለ ነው፡፡

### ወታደር «ዋትቶ አደር»፤

ይህ የተዘወተረ አባባል አንድ ወታደር የአገሩ ሉዓላዊ ክብር እንዳይደፈርና ሕዝቡ በሰላም እንዲኖር የሚከፍለው አታካችና አድካሚ መዋተት የተገለጸበት ብሂል ነው።የወታደር ዋነኛው ትኩረቱና የግዳጁ ተልዕኮ አገሩን፣ ሕዝቡንና የብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማውን ክብር ማስጠበቅ ነው።የተቀረው የዕለት ኑሮው ሩጫ ሁለተኛ ወይንም ሦስተኛ ግዴታው ነው - ቤተሰቡ እንኳን ሳይቀር።ስለዚህም ነው የአገሩን ሉዓላዊነትና ክብር ከሁሉም ነገር ስለሚያስቀድም የወታደርነት ሙያ የተከበረና የተመሰገነ ነው የሚባለው።ታሪክም ሆነ ተሞክሯችን የሚመሰክረው ይህንን እውነታ ነው፡፡

የዚህ ጽሑፍ ዋነኛ ዓላማ የተከበረውን የወታደርነት ሙያና ግዳጅ ከ እስከ ከ ለመተንተነት ተፈልጎ ሳይሆን ለዛሬው ትኩረታችን እንደ ማሳያና መንደርደሪያነት ይጠቅም ስለመሰለን ነው።የአገሬ ዜጎች በሙሉ ወታደር

> **ከተፈጥሮ ጋር እርቅ ለመፍጠርና አረንጓዴ አሻራውን ለማሳረፍ ሕዝቡ ከአገሪቱ ጫፍ እስከ ጫፍ ተንቀሳቅሶ ታሪክ ለመሥራት መጨከኑ «ላብ እንደምን ከመከራ እንደሚታደግ» ጥሩ ማሳያ ነው**

መሆን ባንችልም እንኳን የወታደር ሞራሉና መንፈሱ ቢኖረን ኖሮ የዛሬዩቱ ኢትዮጵያ መልክ እንዲህ በማዲያት ባልወየበ ነበር የሚል ቁጭትን ለመግለጽ ጭምር ነው፡፡

በወታደራዊ ጥበብ ሳይንስ ውስጥም ሆነ በእያንዳንዱ የዕለት ተዕለት ወታደራዊ ግዳጅ ውስጥ አንዲት ደቂቃ በከንቱ አትባክንም።ከማለዳ ጀምሮ እስከ ተልዕኮ ማጠናቀቂያ ሰዓት ድረስ አንድ ወታደር የሚከውናቸው ተግባራት የታወቁ ናቸው።ከእንቅልፉ የሚነሳበት ሰዓት፣ መኝታ ክፍሉን የሚያሳምርበት፣ አለባበሱ፣ የማለዳ ስፖርቱና ቆጠራው (ፎሌው)፣ የምግብ ሰዓት፣ የግቢው ጽዳት፣ እንቅስቃሴውና የግዳጅ ተልዕኮ አፈጻጸሙ በሙሉ አንድም በኅብረት አለያም በግል ከሥርዓትና ከሕግ ውጪ ዝንፍ አይልም፡፡

በብሔራዊ የውትድርና ግዳጅ ውስጥ መሳተፍ ባህል በሆነባቸው አገራት ዜጎቻቸው በአብዛኛው የጤንነታቸው አቋም የተሻለ፣ አኗኗራቸውና ለሥራ የሚሰጡት ክብርና ትጋትም እንዲሁ የሚያስመሰግን እንደሆነ በበርካታ ጥናቶች ተረጋግጧል።አገሬ ይህን መሰሉን የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት ዜጎቿ እንዲያልፉበትና ሥርዓት እንዲሆን አጥብቃ ብትሠራ ከፍ ያለ ትሩፋት ይኖረዋል የሚል እምነት አለን፡፡

### ሌባ ባይሰርቅ፤ ዳኛም ባይገድ፤

«ላብ ደምን ያድናል» መርህ በተግባር ሊተረጎም የሚገባው ለወታደራዊ ግዳጅ ብቻ ሳይሆን ለበርካታ አገራዊ ጉዳዮቻችንም ጭምር ሊሆን ይገባል።ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ዜጎች፣ አንዳንድ የመንግሥት ተቋማት ባለሙያዎችና በኃላፊነት ወንበር ላይ የተመቀመጡትም ሳይቀሩ በሌብነት ተግባር ተሰማርተው የሚልከሰከሱት ላባቸውን ጠብ አድርገው፣ የተሰጣቸውን የኃላፊነት ወንበር አክብረውና ጊዜያቸውን በአግባቡ ተጠቅመው አገራቸውንና ሕዝባቸውን ከማገልገል ይልቅ «ለነፍሳቸው ሳስተው» በአቋራጭ ለመክበርና ሕይወታቸውን ለመለወጥ በመጎምዠታቸው ነው።

ለላባቸው ሳስተው ለሌብነት ጀግነው እጃቸውን አርዝመው በጥፋታቸው ሲጋለጡም «የሚያነቡት የደም እንባ» ለአነሳነው ዋና ጉዳይ ጥሩ ማሳያ ሊሆን ይችላል።ሰሞኑን በአዲስ አበባ ከተማ አንዳንድ ክፍለ ከተሞችና ወረዳዎች ውስጥ ሕዝቡን በሥራ ሰዓት የጊዜ ዝርፊያና በጉቦ ሲያሰቃዩ የተጋለጡት የመንግሥት ሹመኞች ከእስራቱ ባሻገር የቱንም ያህል «የደም ዋጋ» ቢከፍሉ የጎደፈውን ስማቸውን እንደማያነጹት የተረዱት አይመስልም።

እነርሱና የእነርሱ የሆኑ ቤተሰቦችም ሳይቀሩ «የዚያ የምንትሱ ሚስት/ባል፣ አባት/እናት» እየተባሉ የማኅበረሰቡ መጠቋቆሚያ እንደሚሆኑም ይጠፋቸዋል ተብሎ አይገመትም።ይህ መጠቋቆም የዕድሜ ልክ ውርስ ሆኖ እንደሚከተላቸውም የዘነጉት ይመስላል።ሕዝብን ለማገልገል ለተሾሙበት ኃላፊነት ላባቸውን ከመክፈል ይልቅ የሕዝቡን «ደም ለመምጠጥ» መትጋታቸው ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል እያደር ያዩታል፤ እኛም መጨረሻቸውን እንከታተላለን፡፡

አገር መርጣና ሕዝብ አክብሮ በሰጣቸው ሹመት «ላባቸውን ጠብ እያደረጉ» ለብዙኃን ጥቅም፣ እርካታና ውጤት ከመትጋት ይልቅ ቅዠታቸውና ህልማቸው ዘርፎና ገፎ ለመክበር ከሆነ በአንድ አጋጣሚ መጋለጣቸው እንደማይቀር ብዙዎች የዘነጉት ይመስላል።በገሃድ ተጋልጠው ሀፍረት መከናነባቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ፈጣሪ አምላክም የሚከፍላቸው መራራ ብድራት መኖሩንም ሊያስታውሱት ይገባል።

የሰረቁትን ሀብትም ሆነ ጊዜ ተደላድለውና እፎይ ብለው እንዳይበሉ ጤናቸው ሲያውካቸው፣ እንዳሻቸው እንዳይሆኑም ሕሊናቸው ሲያሳድዳቸው የሚኖሩ በርካታ ዜጎችን ቤታቸው ይቁጠረው ብሎ ማለፉ ይቀላል።«ላብና ንጽህና» ከጸጸት እንደሚጠብቅ፣ ከመሳቀቅም እንደሚታደግ፣ «ከደም እምባም እንደሚከልል» ደግሞ ደጋግሞ ለማሰብ ህሊናቸውን ስለደፈኑ ሊሰርቁ እጃቸውን ሲዘረጉ ይህ እውነታ አይታያቸውም።የሚያጭዱት ውጤት የከፋና የከረፋ እንደሚሆን ውስጣቸውን ቢያደምጡ ኖሮ ለስርቆሽ የተዘረጋውን እጃቸውን ወደ ፍም እሳት ለመክተት ባልተጣደፉ ነበር፡፡

### ትዕግስት ያደርሳል ከክብረት፤

ምልከታችንን ሰፋ አድርገን «ላብ ደምን ያድናል» የሚለውን መርህ ለሌላ ታላቅ ወቅታዊ አገራዊ ጉዳይ እንዋሰው።የኢትዮጵያ አገራዊ የምክክር ኮሚሽን ዋናውን ተልዕኮውን ለመጀመር ዝግጅቱን ማጠናቀቁ እየተገለጸልን ነው።ይህ ታላቅ ሕዝባዊ ተስፋ የተጣለበት ተልዕኮ ብዙ ተግዳሮትና የበረታ ፈተና ሊገጥመው እንደሚችል ይገመታል።

በጠብመንጃ ካልተዋጣልን፣ በሻምላ ካልተሞሻለቅን፣ በሰይፍ ካልተዋጣልን የሚል መርህ ያነገቡ የጥፋት ቡድኖች ሕዝብ ውስጥ መሽገውና ጫካ ውስጥ አድፍጠው ባገነኑበት በዚህ ወቅት በጠረጴዛ ዙሪያ ተሰባስበን እንመካከር ሲባል በእነርሱ ብሶ ሰበብ አስባብና መሰናክል እየፈጠሩ ነገሮችን ለማወሳሰብ እንደሚጥሩ መጠርጠሩ ቀቢጸ ተስፋኛ አያሰኝም፡፡

ቢሆንም ግን «ላብ ደምን ያድናል» ብለናልና ብዙ የሚያበሳጩ፣ አልፎም ተርፎ ልብ የሚሰብሩ ክስተቶች ቢስተዋሉም ሕዝቡ፣ የምክክር ኮሚሽኑ አባላትም ሆኑ «ትልቁ» መንግሥት በልብ ስፋትና በትእግስት ላብ እንደ ውሃ እየተንዠቀዠቀም ቢሆን ለቆሰለችው የአገራችን የሰላም ርግብ ሲባል «የደመኞችን» ዓላማ አክሽፎ መከራችንን ለማስቆም መጨከን የግድ ይላል።

ደም ከሚፈስ ላብ እንደ ውሃ ቢንቆረቆር ይበጃልና።ሕዝቡም ሆነ ባለድርሻ ነን የሚሉ አካላት ለዚህ ተስፋ ለተጣለበት የምክክር ኮሚሽን የተልዕኮ ፍሬያማነት የራሳቸውን ሚና ሊወጡ፤ በጎ አሻራቸውንም ለማተም ሊተጉ ይገባል፡፡

አገራዊ ጉዳያችንን ሰፋ እናድርገው።ድህነት ሕዝባችንንና አገራችንን እግር ተወርች ጠፍሮ ያሰረው በተፈጥሮ ሀብት ስላልተባረክን ሳይሆን ለሥራና ለጊዜ ፊት ነስተን ባይተዋር ስላደረግናቸው ነው።እንደ ወንዞቻችን በከንቱ ሲፈስ የኖረው የጊዜ ሀብታችን የሚታደስ ወይንም ተመልሶ ሊመጣ የማይችል መሆኑን እየዘነጋንና ላባችንን ጠብ ለማድረግ እየሰሰትን ድህነት ሞቆን ደርበነው መኖራችን ምስክሩ ሌላ ሳይሆን ኑሯችን ነው።

ለስንዴ ልመና አኩፋዳችንን ተሸክመን ለምጽዋት ስንዞር የኖርነው፣ በድርቅ በትር ክፉኛ ስንደበደብ ወደንና ፈቅደን ጀርባችንን ለግርፋቱ የሰጠነው ላባችንን ለማፍሰስ፣ ጊዜን አክብረን በአግባቡ ለመጠቀምና ሕይወታችንን መርህ አልባ በማድረግ ተጎሳቁለን መኖርን ተቀዳሚ ምርጫችን ስላደረግን ብቻ ነው፡፡

ከተፈጥሮ ጋር እርቅ ለመፍጠርና አረንጓዴ አሻራውን ለማሳረፍ ሕዝቡ ከአገሪቱ ጫፍ እስከ ጫፍ ተንቀሳቅሶ ታሪክ ለመሥራት መጨከኑ «ላብ እንደምን ከመከራ እንደሚታደግ» ጥሩ ማሳያ ነው። ልክ እንደ አረንጓዴ አሻራ ዘመቻችን ሁሉ የሥራ ባህላችንን ለመለወጥም ብሔራዊ ስትራቴጂ ተነድፎ ትንሽ ትልቁ «የላብ መዋጮውን» ለማበርከትና የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት ሊሠራበት ግድ ይሏል፡፡

ሳይሰሩ ለመብላትና ሳይደክሙ ለመክበር የሚቃዡ ዜጎችም ባንነው ከእንቅልፍ ሊቀሰቀሱ ጊዜው ግድ ይላል።በተለይም ለዘመን አመጣሹ የማኅበራዊ ሚዲያ ምርኮኛና እስረኛ የሆነው አብዛኛው ወጣት ከተሸመደመደበት የቅዠት ዓለም ነፃ እንዲወጣና አርነቱን እንዲያውጅ «ላብ ደምን ያድናል» የሚለው የትድግና ጥሪ በይፋ ሊቀርብለት ይገባል፡፡

«ልጅን ማሳደግ እንደ ዘመኑ ነው» ለሚል ፍልስፍና ተገዢ የሆኑ ወላጆችም ጊዜ እንዴት እንደሚዋጅና ላብ ደምን እንደምን እንደሚያድን በግልጽ ቋንቋ ለልጆቻቸው ሊነግሯቸውና በወላጅነት ሥልጣን በአግባቡ ሊያርቋቸው ይገባል።የትምህርት ሥርዓታችንም ቢሆን ለትውልዱ የከንቱነት መሹለኪያ ቀዳዳ ከፍቶ በምኞት ከሚያማልል ይልቅ ቢመርም ቢጎመዝዝም ከወታደራዊ መርሆዎች መካከል ጥቂቱን ተውሶ በመተግበር አደራውን ሊወጣ ጊዜው ዛሬ ነው፡፡

ላብ ከደም የሚታደገው በጦር ሜዳ ውሎ ብቻ አይደለም።በዕለት ተዕለት አኗኗራችን ውስጥም ሊተረጎም የግድ ነው።ጦርነት የአንድ ወቅት ክስተት ነው።ድህነት ተጣብቶ ያስገበረን ግን የቤታችን ማደጎ ሆኖ በጠላትነት ስለሰለጠነብን ነው።ድህነት የሚሸነፈው በክላሽንኮፍና በአዳፍኔ አይደለም።

ድህነትን ወልደን ያሳደግነው እኛው ስለሆንን አምክነን የምናስወግደው የላባችንን ጠብታ አስተባብረን «እምብየው!» በማለት በሥራና በፊጠራ ትጋት ስንዘምትበት ብቻ ነው።የተጠቃቀሱት የችግሮቻችን ዓይነቶች በርከት ይበሉ እንጂ መፍትሔው አንድ ነው፤ «ለላባችን የቅድሚያውን ክብር እንስጥ!» - ኑሯችንን የምንለውጠውና የምንለወጠው በሥራ ነው።የምናሸንፈውም ለትእግስትና ለመርህ እጅ በመስጠት ብቻ ነው።ሰላም ይሁን!

**ፖለቲካና ወቅታዊ**

# ተናጋሪው ዶሴ

# ክፋትን ያረገዘ ጓደኝነት ፍፃሜ...

**አስመረት ብሥራት**



ጓደኝነት ሲነሳ በጎ ሀሳቦች፣ መረዳዳት፣ መተሳሰብ፣ አብሮ መብላት መጠጣት በአዕምሮ ውስጥ ይመላለሱ። እንዲያውም አንዳንዴ ከዚያም በላይ ይሆናል። ጓደኝነት በተለይ የተቃራኒ ጾታ ከሆነ ደግሞ ሁለት ከመሆንም አልፎ አንድ አካል እስከመሆንም ይደረሳል። ጓደኛ ገበና ከታች ነውም ይባላል። የሰው ልጅ በጓደኝነት ደስታና ኀዘንን ሲሻገር፤ ለችግሮቹ መፍትሄ ሲሰጣጥ መመልከት የተለመደ ነው። ከአንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒቱ እንደሚባለው በመደጋገፍ ችግሮችን ለመሻገር ከጓደኝነት የበለጠ መፍትሄ የለም። ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ ከጓደኝነት ጋር ተያይዞ የሚያጋጥሙ ግጭቶች አይጠፉም። በቅናት፣ በምቀኝነት፣ በክህደት ወይም ደግሞ በሌላ ምክንያት ጸብ ውስጥ የሚገባበት ከዚያም አልፎ ሕይወት እስከመጠፋፋት የሚደርስበት አጋጣሚ በርካታ ነው።

የዛሬዎቹ ባለታሪኮቻችን በሥራ አጋጣሚ የተገናኙት ሁለት ጓደኛሞች ናቸው፡፡ ምሽታቸውን አብረው ማሳለፍ ከጀማመሩ በኋላ ወዳጅነታቸውን እያጠበቁ ይቀጥላሉ። በዚህ ወዳጅነት ውስጥ ችግሮችን ከመጋራት በላይ ደስታዎቻቸውንም አብረው መካፈል ልምዳቸው ሆነ። ከተወሰነ ጊዜ ወዲህ ግን አንዱ ጓደኛ ልብ ውስጥ የመበለጥ ስሜት፤ ቅናት የወለደው ክፋት ተፀነሰ። ይህ ክፋትን ያረገዘው ልብ ክፋትን ወደ መልካም ከመቀየር ይልቅ ቂምን አርግዞ ጊዜና ቦታ ይጠብቅ ጀመር።

‹‹እኔ የምሠራው ሥራ ውስጥ ሌሎች ገብተዋል›› በማለት ተቀናቃኙ የመሰሉትን በኅብረት ማደግ መፍትሄ አድርገው ሥራቸውን በጋራ የሚሠሩትን ጓደኞሞች በክፉ ዓይኑ መመልከት ጀመረ። ይሄን ልቡ ያረገዘውን ክፋትም ለጓደኛው ተነፈሰለት። ጓደኛውም የቆየ ልማድ ነበረውና የጓደኛውን ባላንጣዎች ለማጥፋት ተስማማ። እንግዲህ ለክፋት የተባበረው ጓደኝነት አዲስ አበባ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ ዜሮ አንድ ልዩ ቦታው ሀና ማርያም ቤተክርስቲያን አካባቢ ከሚገኝ ቤት ከምሽቱ ሦስት ሰዓት የሰው ነፍስ ለማጥፋት በቃ።

በዚህ ዕለት ከላይ በተጠቀሰው ስፍራ የተገደለ ሰው መኖሩ ለአዲስ አበባ ፖሊስ መረጃ ይደርሰዋል። ፖሊስ ጥቆማው ወደ ተሰማበት ቦታ በመሄድ ለምርመራው ያግዛሉ የተባሉ የቴክኒክና የታክቲክ ማስረጃዎችን ማሰባሰብ ይጀምራል።

ፖሊስ ሟችን የተለያዩ የሰውነት ክፍሎቹ ላይ በመወጋት የገደለውን ሰው ማንነት ለማወቅ ምርመራ ይጀምራል። የሰው መግደል ወንጀሉ ለምን ተፈፀመ? እንዴት ተፈፀመ? ወንጀል ፈፃሚዎቹስ ይሄንን ወንጀል ከፈፀሙ በኋላ ወዴት ሄዱ? በዚህ የወንጀል ድርጊት ውጤትስ ተጠቃሚው ማነው? ለሚሉ የተለያዩ ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት የምርመራ ክፍሉ በቡድን በመሆን ደፋ ቀና ይል ጀመር።

በዚህ ወንጀል ተጠቃሚ ይሆናል የተባለ ከሟች ጋር በቡና ገለባ ንግድ ይተዋወቁ ነበር የተባለ ተጠርጣሪ ጋር ሟች የተለያዩ ጊዜያት ያለመግባባት ውስጥ ገብተው እንደነበረና ስሙም አለልኝ ታደሰ የሚባል ሰው መሆኑን ለፖሊስ ጥቆማ ደረሰው።

ተከሳሹ የቡና ገለባ በሚያከፋፍልበት ወቅት ሳሪስ አካባቢ ከሚገኝ የግለሰብ ድርጅት ውስጥ ይወስድ የነበረና ሟችና የሟች ጓደኛም በተመሳሳይ ይሄ ድርጊት ከመፈፀሙ አስቀድሞ ከሦስት ወይም ከአራት ወራት በፊት ከዚሁ ድርጅት ውስጥ የቡና ገለባ በቀጥታ እየተረከቡ ለተጠቃሚ ያከፋፍሉ ነበር። ገዳይም በዚህ ድርጊት ቅናት ይዞት ‹‹ለምን የቡና ገለባውን ከእኔ አልተረከቡም›› በሚል ከሟችና ከሟች ጓደኛው ጋር ፀብ ውስጥ ገብተው ነበር።

ተጠርጣሪውም ከዚያ በኋላ በተደጋጋሚ ዛቻ ያደርስ የነበረ ሲሆን ሟችና የሟች ጓደኛ በተቀመጡበት መጥቶ ‹‹እናንተን ገድዬ ለሁለታችሁ ነፍስ ሰለሳ ሰላሳ ሺ ብር ብከፍል ነው፤ ይህንንም እከፍላለሁ›› በማለት በተደጋጋሚ ይዝት እንደነበር የሰሙ ሰዎች ለፖሊስ ይናገራሉ። ይህም ተጠርጣሪው በፖሊሶች በአይነ ቁረኛ እንዲታይ ያደርገዋል።

ሟች ጌትነት ከሞተ በኋላ ተጠርጣሪው አቶ አለልኝ ታደሰ ከአካባቢው መሰወሩንም ፖሊስ በመረጃው ማግኘት ችሏል። የተጠርጣሪው ማንነት ከተጣራና የሚኖርበት አካባቢ ከታወቀ በኋላ ምርመራው እየተጠናከረ ግለሰቡን ለማግኘት ፖሊሶች አሰሳቸውን ይጀምራሉ።

**ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ወይም በሕግ አግባብ መፍታት እየተቻለ በራስ መንገድ በስሜት በመነሳሳት ሕገ ወጥ ድርጊት መፈፀም ጉዳቱ የከፋ ነውና መጠንቀቅ ይገባል**

ይህ የወንጀል ድርጊት በተፈፀመ በአራተኛው ቀን ፖሊስ ተጠርጣሪውን ለመያዝ በሚያደርገው ሙከራ አምልጦ ወደ ጫካ ለመግባት ሲሞክር በኅብረተሰቡ ትብብር ይያዛል። ምንም እንኳን የመጀመሪያው ተጠርጣሪ አለልኝ ቢያዝም የምርመራ ቡድኑ ድርጊቱን የፈፀሙት ሁለት ሆነው እንደነበረ መረጃ ስላለው ሌላኛውን ተጠርጣሪ ለመያዝ በተያዘው ተጠርጣሪ ላይ ምርመራ ያደርጋል።

ተጠርጣሪው አለልኝ የወንጀል ድርጊት መፈፀሙን አምኖ የምርምራ አቅጣጫውን ለማሳት በማሰብ ‹‹ተስፋዬ የተባለ ከዚህ በፊት የማላውቀው ነገር ግን በሀና ማርያም አካባቢ በሥራ አጋጣሚ የማውቀው እና መጠጥ ቤት ውስጥ የተዋወቅኩትን በመገባበዝ ጓደኝነት የመሠረትን ነን። የእዚህ ሰውም መኖሪያ ቤት ሀና ማርያም አካባቢ ነው›› የሚል የተሳሳተ መረጃ ሰጠ፡፡

አንደኛ ተጠርጣሪ በቅናት በመነሳሳት የሟችን ነፍስ ማጥፋቱን ቢያምንም የግብረ አበሩን ማንነት በግልፅ ባለመናገሩ ፖሊስ ሌላኛውን ተጠርጣሪ ይዞ ለሕግ ለማቅረብ ዳግም ፍለጋውን አጠናክሮ ቀጠለ። በዚህም ተስፋዬ የሚባለው ሰው ማነው? ተስፋዬ ከሚባለው ሰውና አለልኝ የተባለ ሰው በጋራ ሰው ለመግደል ከቻሉ የጠበቀ ቁርኝት አላቸው ማለት ነው የሚሉ መላምቶችን በማስቀመጥ ፖሊስ ምርመራውን በስፋት እያካሄደ ነው።

ፖሊስ በቡድን ባደረገው አሰሳ ግን ተስፋዬ የተባለው ግለሰብን ማግኘት አልተቻለም። አንድም ሰው ተስፋዬን ስለማወቁ የሚናገር ጠፋ። ምንም ፍንጭ ባለመገኘቱ ከብዙ ድካም በኋላ ተስፋዬ የሚባለው ተጠርጣር ያልነበረ፤ የፈጠራ ሰው መሆኑን የምርመራ ቡድኑ ደረሰበት። አንደኛ ተጠርጣሪ አለልኝ ግን አሁንም ድረስ ግብረ አበሩን ለሕግ አሳልፎ የመስጠት ፍላጎት አልነበረውም።

ፖሊስ ይህንን ጉዳይ ለማጥራት በጥንቃቄ ምርመራውን ቀጠለ። በዚህም ከአለልኝ ታደሰ ጋር ሲወጣና ሲገባ የሚታየው ተስፋዬ ሳይሆን አበበ የሚባል ሰው መሆኑን ፖሊስ ደረሰበት። ይህ አበበ የተባለው ግለሰብም ከዚህ በፊት የሰው ነፍስ ማጥፋቱን ለፖሊሶች መረጃ ደረሰ።

መርማሪው እንደሚናገሩት አበበ ማነው? የሚለውን ጥያቄ የሚመለስ ምንም ነገር ማግኘት አልተቻለም ነበር። ስሙ ብቻ ደግሞ ተጠርጣሪውን ሊያስገኝ አልቻለም። እንደ ዕድል ሆኖ አንደኛ ተጠርጣሪ አለልኝና ይሄው ያልተገኘው ተጠርጣሪ አበበ አንድ ልደት ላይ የተነሱት ፎቶግራፍ በመርማሪዎች እጅ ገባ። ይህ ፎቶ እጃቸው ከገባ በኋላ ተጠርጣሪ አበበ መርኔ እዚያ አካባቢ ለምንና እንዴት እንደመጣ ፖሊሶች መረጃዎች መሰብሰብ ጀመሩ።

በምርመራውም አበበ መርኔ የመጣው ከደበረ ብርሃን አካባቢ መሆኑን ለማወቅ ተቻለ። ከዚህ ቀደም በደብረ ብርሃን የሰው ነፍስ በማጥፋት ወንጀል እስር ቤት እንደነበረ ታወቀ። ስምንት አመታትን በደብረ ብርሃን ወህኒ ቤት ከሳለፈ በኋላ በምህረት ተለቆ አሁን ወንጀሉ የተፈፀመበት ሀና ማርያም አካባቢ የቡና ገለባ የመጠቅጠቅ ሥራ ላይ ተሰማርቶ የነበረ መሆኑንና ወንጀሉ ከተፈፀመ በኋላ መሰወሩንም ፖሊሶች ባጠናቀሩት መረጃ ሊታወቅ ተቻለ።

ይህ አበበ የተባለው ተጠርጣሪ ከዚህ በፊትም በሰው መግደል ወንጀል አስራ ስምንት አመት ተፈርዶበት ስምንት አመታትን በደብረ ብርሃን ማረሚያ ቤት ካሳለፈ በኋላ በምህረት የተፈታ መሆኑን ያረጋገጠው የምርመራ ቡድን ይህ ተጠርጣሪ ይገኝበታል የተባለውን አካባቢ ማሰስ ይጀምራል።

ከብዙ ፍለጋ በኋላ ተከሳሹ በመስከረም ወር ላይ በደብረ ብርሃን ከተማ ሕገ ወጥ መሣሪያን ይዞ በደብረ ብርሃን ፖሊስ መያዙንና በጊዜ ቀጠሮ ላይ መሆኑን የምርመራ ቡደኑ መረጃ አገኘ። ፎቶግራፉ በምርመራ ቡድኑ እጅ ስለነበረ ያለበት ቦታ ሲለይ በማረሚያ ቤት መኖሩ ታወቀ። ፖሊስ የፍርድ ቤት ትእዛዝ በመያዝ ወደ ደብረ ብርሃን በመሄድ ተከሳሹ ያለበትን ሁኔታ ለይተው ይሄኛው የምርመራ ቡድን የያዘው ወንጀል ከባድ መሆኑን አስረድተው ከማረሚያ ቤቱ በመረከብ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ ተደረገ።

ተጠርጣሪ አበበ መርኔ በምርመራ ወቅት ከሟች ጌታቸው ጋር ትውውቅ እንዳልነበረው ነገር ግን በአካባቢው ያየው እንደነበር ይናገራል። እዚያ አካባቢ ሊያየው የቻለው በአንደኛ ተከሳሽ አለልኝ አማካይነት ነበር። ለአንደኛ ተከሳሽ ደግሞ ገለባ ሲጠቀጥቁና ግሮሰሪ ውስጥ ሲጠጡ የጠበቀ ወዳጅነት መስርተው ነበር። ጓደኝነታቸው እየጠበቀ ሲሄድም በእነ ጌትነት ደረሰብኝ ብሎ የሚያስበውን በደል አለልኝ ለአበበ ይነግረዋል።

መቼስ ልማድ አይለቅ ነውና አበበ ይሄን ሲሰማ ከዚህ ቀደም እንደለመደው ‹‹ተባብረን እናጥፋው›› በሚል ድጋፉን ይገልፅለታል። የወንጀል ድርጊቱንም ለጓደኛው ለአለልኝ ታደሰ ሲል ወንጀሉን መፈፀሙንም ለመርማሪዎቹ ይናገራል።

የምርመራ ውጤቱ ማጠናቀቂያ ላይ ሁለቱም ተከሳሾች የወንጀል ድርጊቱን እንዴት እንደፈፀሙት በማስረዳት የእምነት ክህደት ቃላቸውን ይሰጣሉ። ፖሊስ እነአለልኝ ታደሰ ድርጊቱን እንዴትና ለምን እንደፈፀሙ የሰጡትን ቃል በመያዝ የፎረንሲክና የሰው ማስረጃዎችን በማጠናቀር የምርመራ መዝገቡን ለአቃቤ ሕግ አስረከበ።

የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን የሰው መግደል ወንጀል ምርመራ መርማሪ ዋና ሳጅን መንግሥት ታደሰ እንደሚሉት በሥራ አጋጣሚም ሆነ በማህበራዊ ግንኙነት የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት አለዚያም ወደ ሕግ ማቅረብ ተገቢ ነው፡፡

ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ወይም በሕግ አግባብ መፍታት እየተቻለ በራስ መንገድ በስሜት በመነሳሳት ሕገ ወጥ ድርጊት መፈፀም ጉዳቱ የከፋ ነውና መጠንቀቅ ይገባል። ይህ ድርጊት በወንጀል አድራጊው በማኅበረሰቡና በአገር ላይ የሚፈጥረው ጫና ቀላል የሚባል አይደለምና ማንም ሰው በስሜት ጉዳት ከማድረሱ በፊት ቆም ብሎ ማሰብ ይገባዋል ይላሉ።

### ውሳኔ

አቃቤ ሕግ የመሠረተውን ክስ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ችሎት ነው። ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ማስረጃዎችና መረጃዎች በማየት ተጠርጣሪዎቹ በሠሩት የጭካኔ ወንጀል ጥፋተኛ ሆነው በመገኘታቸው ሁለቱም በሃያ አመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኖባቸው።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## የማህበራዊ ገፅ ተጠቃሚ እንጂ መጠቀሚያ አንሁን

ተገኝ ብሩ

ውሎና አዳራችን ስልካችን ላይ ሆኗል:: በጋራ ጉዳዮቻችንን ወንበር ስበን ፊት ለፊት መወያየት ትተናል:: ችግሮችን በተግባቦት ከመፍታት ይልቅ ጥራዝ ነጠቅ ሀሳቦቻችን ቴክኖሎጂ በፈጠረልን ሜዳ እንዳሻን በማንሸራሸር እየተቀባበልን መሰዳደብ ቀሎናል:: ማህበራዊ ግንኙነታችን በማህበራዊ ገፆች ምክንያት እጅጉን መላላቱን ልብ ብለነው ይሆን? እንጃ አይመስለኝም:: አብረውን ላሉ ወዳጆቻችን ትኩረት በመንሳት የቅርብ እሩቅ ሆነን ቀርበን ሳናዋያቸውና ሳንረዳቸው ስንቶችን አስቀይመናል፤የስንቶችንስ ስሜት ጎድተናል::

አባወራ ነው፤ በስራ የዛለ አካሉን እየጎተተ ይጓዛል:: ቤቱ ገብቶ አረፍ ማለት በፅኑ ፈልጓል:: ታክሲ ለማግኘት ብዙ ርቀት ተጉዞ ከዚያም ረጅም ሰልፍ ጠብቆ አመሻሽ ላይ ቤቱ ደረሰ:: ትንሽ አረፍ እንዳለ ረሀብ ቢጤ ተሰማውና ምግብ ፈለገ:: እዚያው ያረፈበት ሳሎን ውስጥ ከአንድ የቤቱ ጥግ ላይ ባለ ሶፋ ላይ ጋለል ብላ ስልክዋን የምትጎረጉረው ባለቤቱን ሲመለከት ከረሀቡ ይልቅ ውስጡ ቅሬታ ተሰማው:: እርሷ አንዴ ፌስ ቡክ ሌላ ጊዜ ቴሌግራም እየከፈተችና እየዘጋች እዚያው መንደር ላይ እዚህ እዚያ ትመላለሳለች:: አባወራው ቤት መግባቱን እንኳን ልብ ያለች አትመስልም::

እማወራዋ የቤት እመቤት ናት::ባል በስራ ደክሞት ነበርና በድካሙ መሀል የሁልጊዜ የባለቤቱን ተግባር ወደኋላ ተመልሶ ማየት ጀመረ:: ቤቱን ለማቅናት የሚለፋውን ያህል ትኩረት አትሰጠውም:: ጎጆውን ለማቆም የሚጥረውን ያህል ድጋፍ አታደርግለትም:: በዚህ ሁሌም ይከፋዋል:: እቤት በሚሆንበት ጊዜ እሱን ከማውራት ይልቅ ስልክዋ ላይ አብዝታ ታተኩራለች:: ከእርሱ ጋር ከመወያየት ይልቅ በጣቷ ስልኳ ላይ ፊደል እየተየበች የምታሳልፈው ጊዜ ይበልጥባታል:: ይሄም ያበሽቀዋል:: ለአንድ ሰዓት ያህል በትኩረት ሁኔታዋን ተከታተለ:: ዞር ብላም አላየችው::

**ምንያህል የሚጠቅመንን ትተን ከማይጠቅመን ነገር ጋር እንደተጣበቅን ማሳያም ነው**

እንደደከመውና እራት እንድታቀርብለት ሲነግራት የመለሰችው መልስ ግን ይበልጥ አበሳጭቶት ቱግ አለ::ርቦኛል የሚቀመስ ካለ ለሚለው የአባወራው መማፀኛው "ፍሪጅ ውስጥ አለልህ አሙቀህ ብላ እኔ በቃኝ::" ነበር መልሷ:: ይሄን ማለፍ አልቻለም:: ከዚያ ቀን በፊት ልክ ያልሆነ ተግባሯን እያነሳ ይወቅሳትና ይገስፃት ጀመር::

ይሄኔ ተንጋላ የነበረችው ባለቤቱ ቀና ብላ ከእሷ ብሶ ተቆጣች:: በስልኳ ምክንያት የሚነሳው ሀሳብ እንደሰለቻት፣ወሬ እንደማትወድና ጭቅጭቅም እንደማትፈልግ በቁጣ ጭምር ስሜትዋን መግለፅ ያዘች:: ስልኳን ሳታይ ደቂቃዎች መቆየት እደማትችልና አባወራው ይሄን ካልወደደ ሁሉም ሊቀር እንደሚችል መናገርን መረጠች:: ይሄኔ አባወራ ተቆጣ:: "በቃ ወደ ቤተሰቤ እሄዳለው" ስትለው የተጣሉት ውል ባለው ነገር ባለመሆኑ ሁኔታዋ ግራ አጋባው:: በጉዳዩ ‹‹እናውራበት›› ቢላትም በጀ አላለችም::

ጓዳ ገብታ ልብሷን መሰብሰብ ጀመረች:: በሻንጣም አንጠልጥላ ለመውጣት በር ላይ ስትደርስ ቆም ብላ አንድ ነገር አሰበች:: አባወራ ሁኔታዋን በመገረም ይከታተላል:: እሷ ግን እግሯን ወደፊት የማያራምዳት አንድ ምክንያት ትውስ አላት:: ልትሄድበት ያሰበችው የወላጆቿ ቤት አሁን እንደምትኖርበት ቤት ዋይ ፋይ የለም:: በዳታም ቀጥታ እንዳትጠቀም ያለውን የኔትወርክ ችግር ጠንቅቃ ታውቃለች:: ከባለቤቷ ይልቅ ነጋ ጠባ የምታወራቸው የማህበራዊ ገፅ ጓደኞቿን ማጣት አሳሰባት:: ላለመሄድ ወሰነች::

ይህ ማህበራዊ ገፆች ምንያህል በእያንዳንዱ ቤት እያሳረፉ የሚገኙትን አሉታዊ ተፅዕኖ የት እንደደረሰ የሚያሳይ እውነተኛ ገጠመኝ ነው:: ምንያህል የሚጠቅመንን ትተን ከማይጠቅመን ነገር ጋር እንደተጣበቅን ማሳያም ነው:: ይህን ያህል የቆምንበትን መሰረት ስተን አየር ላይ እያንሳፈፈን የሚገኝ መጥፎ ልማድ እንዳዳበርን ጠቋሚም ነው::

ዛሬ ላይ እንዲ ሆነ እንዲህ ተባለ እያሉ በማህበራዊ ገፆች አጀንዳ የሚያቀብሉን ስራችን ካሉ ሰዎች ሁሉ በልጠውብናል:: የማህበራዊ ገፅና ሚዲያ አጠቃቀማችን ከማህበራዊ ግንኙነት አርቆን ግለኛ አድርጎናል:: አጠገባችን ያለውን ጓደኛ ወይም ቤተሰብ ከማውራት ይልቅ ስልካችንን ከፍተን ውሎና አዳራችን ከማናውቀው ጋር ሆኗል:: ነገር በዓይን ይገባል እንዲሉ ፊት ለፊት ከመወያየት ይልቅ በዚህ ዘመን አመጣሽ መረብ ከተዋወቅነው ጋር ማውራት ቀሎናል::የሚወራው መልካም ሆኖ የምንወያይበት ርዕሰ ጉዳይ እኛን የሚለውጥ አገርን የሚጠቅም ቢሆን መልካም ነበር::

ስንቶቻችን ነን የማህበራዊ ገፅ አጠቃቀማችን ላይ ገደብ አበጅተን ስርዓት ባለውና እኛን በሚጠቅም መንገድ የምንገለገለው? ቴክኖሎጂውን ተገቢ ላልሆነ ነገር የምንጠቀመውስ?:: ቴክኖሎጂውን በተገቢው መንገድ ከተገለገልንበት ይጠቅመናል:: ተገቢ ባልሆነ መንገድ ስንገለገለው ግን አቋምና መስመር እንዳይኖረን ሲያደርገን አይተናል:: በጠንካራ መሰረት ላይ የፀና ማንነት እንዳንላበስ አድርጎናል:: በህይወት ውጣ ውረድ ውስጥ የራሳችን መስመር፣ መርህና ግብ ኖሮን ያንን ለማሳካት ከመጣር ይልቅ የሰው ህልም እየመነዘሩና እየተረጎሙ መኖርን አስለምዶናል::

ከሌሎች በጎ ነገር መውሰድ አንድ ነገር ነው:: ሁሌም የሌሎችን ሀሳብ ውስጣችን ሞልተን እኛን ሆነን የቆምንበትን ማንነነት በሌሎች ሃሳብ መነጠቅ ግን አይበጅንም:: ሰው በስብዕናው ይቆም ዘንድ የራሱን መሰረት ማፅናት፤ የግሉ መርህ ሊኖረው ግድ ይላል::ያ ማንነቱ የተዛነፈ ዕለት ከሰውነት ይወርዳል:: ከራሱ የጎደለም ህልውና አይኖረውም:: ቢኖርም ኑሮው ለሌላ ነው:: ቢንቀሳቀስም ሌሎች ባሰመሩለት መስመርና አቅጣጫ ብቻ ነው::ይህ ሰው ታዲያ እራሱ ሳይሆን ህልውናውን በገዛ ፍቃዱ አስረክቦ የሚንቀሳቀስ ፍጡር ነው::

ሁሉንም ነገር በልክ ካላደረግነው ከልክ በታች ያደርገናል:: ቴክኖሎጂውን እንጠቀምበት እንጂ አይጠቀምብን:: በርካቶች መጠቀሚያ የመሆን እንጂ ተጠቃሚ የመሆን ልማድ አላዳበርንም:: በእርግጥ ማህበራዊ ገፆችን በእጅጉ የሚጠቀሙበትና እራሳቸው የለወጡበት እንዳሉ ይታወቃል:: እድሉን ተጠቅመው እራሳቸውን በተለያየ መንገድ ወደሚፈልጉት በጎ ግብ ያደረሱ በርካቶች ናቸው::

በቴክኖሎጂው መልካምነት ላይ ብዙ ሊባል ይችላል:: እዚህ ምድር ላይ ለበጎ መጠቀም ከተቻለ ሁሉም ነገር መልካም ነው:: ዓለምን ካስተሳሰሩ መልካም ነገሮችም ውስጥ አንዱም ይህ ቴክኖሎጂ ነው:: ችግሩ በምን መልክ እንገለገልበት የሚለው ላይ ነው:: ሰዎችን በአስተሳሰብና ህይወት እንዲለውጥ፣ አኗኗራቸውን እንዲያቀል እንጠቀምበት::

# ዓለም አቀፍ

## የዩክሬንን እህል ለዓለም ገበያ ለማቅረብ ከሩሲያ ጋር ስምምነት መደረሱን ቱርክ አስታወቀች

ቱርክ በጥቁር ባሕር የዩክሬንን እህል ለዓለም ገበያ ለማቅረብ ከሩሲያ ጋር ስምምነት መደረሱን አስታወቀች።የተደረሰውን ስምምነት ተከትሎም በዛሬው እለት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ አንቶኒዮ ጉተሬዝ በተገኙበት በሩሲያ እና ዩክሬን ተወካዮች መካከል በኢስታንቡል የሰነድ የፊርማ ሥነ ስርአት እንደሚኖርም ተገልጿል።

የዩክሬን ውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤትም የሀገሪቱ የጥራጥሬ ምርት ከጥቁር ባሕር ተነስቶ ለዓለም ገበያ እንዲደርስ የሚያስችል የስምምነት ሰነድ በዛሬው እለት ሊፈረም እንደሚችል አረጋግጧል።የዩክሬን ፕሬዚዳንት ቮሎዲሚር ዜለንስኪም ዩክሬን "ከወደቦች መከፈት ጋር የተያያዙ" ዜናዎችን ትጠብቃለች ብለዋል።

ለሚፈረመው የስምምነት ሰነድ ቅርብ የሆኑ አንድ የዩክሬን የፓርላማ አባል ግን ከስምምነት ሰነዱ ጋር ተያይዞ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል በሚል ስጋታቸውን ገልጸዋል።በስምምነቱ መሰረት ጥራጥሬ የጫኑ የዩክሬን መርከቦች ያለምንም ገደብ እንዲንቀሳቀሱ ሲፈቀድላቸው ሩሲያም መርከቦቹ እህል ጭነው በሚጓዙበት ወቅት የተኩስ አቁም ታደርጋለች።

ከዩክሬን ባለፈም ሩሲያም የጥራጥሬ እና ማዳበሪያ ምርቶቿን በጥቁር ባሕር በኩል ለዓለም ገበያ የምታቀርብበትን መንገድ ማሳለጥም የስምምነቱ አካል መሆኑም ነው የተገለጸው።ቱርክም በተመድ ድጋፍ እየተደረገላት በአካባቢው የመሳሪያ ዝውውር እንዳይኖር በሚል ከሩሲያ በኩል የተነሳውን ስጋት ለመቅረፍ በመርከቦቹ ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ታደርጋለች ነው የተባለው።

የሩሲያ ዩክሬን ጦርነት ከተጀመረበት ካለፈው የካቲት ወር ጀምሮ የጥራጥሬ ምርት ለዓለም ገበያ እየቀረበ አይደለም።ለዚህ ደግሞ ዩክሬን ሩሲያ የጥቁር ባሕር




ወደቦችን ዘግታብኛለች በሚል ስትኮንን በአንጻሩ ሩሲያ ውንጀላውን ታስተባብላለች።

በአካባቢው ካለው የባሕር ትራንስፖርት መስተጓጎል ጋር በተያያዘም አሁን ላይ ወደ 20 ሚሊየን ቶን የሚጠጋ የጥራጥሬ ምርት በኦዴሳ ሲሎስ ተከማችቶ እንደሚገኝ ቢቢሲ መዘገቡን ኤፍቢሲ ጠቅሷል።

## የጃፓን ፓስፖርት የዓለማችን ጠንካራው ፓስፖርት መሆኑ ተጠቆመ

የጃፓናውያን ፓስፖርት የዓለማችን 'ጠንካራው' ፓስፖርት ተባለ።ሄንሊይ የተሰኘው ተቋም የዓለም አቀፉን የአየር ትራንስፖርት ማኅበር አሃዞችን ተጠቅሞ ባወጣው ደረጃ መሠረት የጃፓን ፓስፖርት የዓለማችን ጠንካራው ፓስፖርት ነው ብሏል።

የጃፓን ፓስፖርትን የያዙ ሰዎች ወደ 193 አገራትና ግዛቶች ያለ ቪዛ መጓዝ ይችላሉ፣ አልያም ቪዛ በመዳረሻቸው ያገኛሉ።ሄንሊይ የፓስፖርቶችን ጥንካሬ የሚለከው፤ ተጓዦች በያዙት ፓስፖርት ምክንያት ቪዛ ቀድሞ ሳያስፈልጋቸው ወደ ስንት አገራት መጓዝ ይችላሉ የሚለውን በማጤን ነው።

በሄንሊይ ሪፖርት ላይ ቀድሞ ቪዛ አለማስፈለግ ማለት፤ ወደ መዳረሻ ለመጓዝ ቪዛ አለመጠየቅ አልያም በመዳረሻ ቪዛ የማግኘት መብት ማለት ነው።ሄንሊይ የ2022 ሦስተኛው ሩብ ዓመት የፓስፖርት ደረጃዎችን ይፋ ያደረገው 199 ፓስፖርቶችን እና 227 መዳረሻዎችን ከመረመረ በኋላ መሆኑን አስታውቋል።በዚህም መሠረት ሲንጋፖር እና ደቡብ ኮሪያ በእኩል ነጥብ የዓለማችን ሁለተኛው ጠንካራ ፓስፖርት ደረጃን ይዘዋል። የእነዚህ አገር ዜጎች ቀድመው ቪዛ ማግኘት ሳይጠበቅባቸው ወደ 192 መዳረሻዎች መጓዝ ይችላሉ።

ጀርመን እና ስፔን በሦስተኛ ደረጃ ላይ የተቀመጡ ሲሆን ፊንላንድ፣ ጣሊያን እና ላክሰመበርግ 4ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጠዋል።ኦስትሪያ፣ ዴንማርክ፣ ኔዘርላንድስ እና ስዊድን ያለ ቪዛ ወደ 188 መዳረሻዎች በመጓዝ 5ኛ ደረጃ ላይ ናቸው።ዩናይትድ ኪንግደም፣ አሜሪካ እና አውስትራሊያ ወደ 187፣ 186 እና 185 መዳረሻዎች ቀድሞ ቪዛ ሳያስፈልጋቸው ለመጓዝ በመቻል እንደ ቅደም ተከተላቸው 6ኛ፣ 7ኛ እና 8ኛ ደረጃ ላይ ሲቀመጡ፤ ሃንጋሪ እና ሉትዌኒያ ደግሞ 9ኛ እና 10ኛ ደረጃን ይዘዋል።

የዓለም ባንክ እንደሚለው ከሆነ የአንድ አገርን የፓስፖርት ጥንካሬ ከሚወስኑ ዋነኛ ጉዳዮች መካከል አንዱ ዜጎች የሚያገኙ ገንዘብ መጠን ነው።ከፍተኛ የነፍስ ወከፍ ገቢ ያላቸው አገራት ከደሃ አገራት በተሻለ ወደ በርካታ አገራት ቪዛ ቀድሞ ማግኘት ሳይጠበቅባቸው መጓዝ ይችላሉ።




ይህ የሚሆነው ይላሉ የሄንለይ አጥኚ የሆኑት አመር ዛረፐሊ (ዶ/ር)፤ "ይህ የሚሆነው አገራት ከድሆች ይልቅ ለሃብታም አገራት ድንበሮቻቸውን ክፍት ስለሚያደርጉ ነው።"ከፍተኛ የነፍስ ወከፍ ገቢ ካላቸው አገራት የሚመጡ ተጓዦች በመዳረሻቸው በቱሪዝም፣ በንግድ እና በኢንቨስትመንት መልክ ብዙ ገንዘብ ፈሰስ ስለሚያደርጉ ለተቀባይ አገር ምጣኔ ሃብታዊ ዕድገት አዎንታዊ አስተዋጽኦን ያበረክታሉ ይላሉ አጥኚው።

ሄንሊይ እንደሚለው የአንድ የአገር ሁለንተናዊ ሰላም ከአገሪቱ የፓስፖርት ጥንካሬ ጋር በቀጥታ ይገናኛል።በአንድ አገር የሽብር ጥቃቶች እና ብሔርን መሰረት ያደረጉ ግጭቶች የበረከቱ ከሆነ፤ በተደራጁ ቡድኖች የሚፈጸሙ ወንጀሎች ካሉ የዚያች አገር ዜጎች ዓለም አቀፍ ጉዟቸው የተገደበ ይሆናል።

ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት የሌላቸው እና ከፍተኛ ተፈናቃይ ያለባቸው አገራት ዜጎችም በተመሳሳይ ቪዛ የሚጠየቁባቸው መዳረሻዎች ከፍተኛ እንዲሆኑ አድርጓል።ለማሳያም ምጣኔ ሃብታቸው የደቀቀባቸው፣ ማዕከላዊ መንግሥታቸው የተዳከመባቸው አልያም የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች የበዙባቸው እንደ የመን፣ ሶሪያ፣ ኢራቅ እና አፍጋኒስታን ያሉ አገራትን ፓስፖርት የያዙ ዜጎች በብዙ መዳረሻዎች ቪዛ እንደሚጠየቁ ቢቢሲ ዘግቧል።

# መጋቢ አዕምሮ

# ሀሳብ፤ በግራም በቀኝም!

በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ

በመርካቶ ተገኝቶ ሽመታ ለማድረግ የሚመላለሱ ሰዎች ከቀማኛ ራሳቸውን እየጠበቁ ግራ ቀኛቸውን እየገላመጡ የሚንቀሳቀሱ ናቸው። መርካቶ የብዙ ነገሮች መገኛ ቦታ እንደሆነችም ይነገራል። ከአፍሪካ ቀዳሚው የገበያ ቀጠና የተባለው መርካቶ በውስጡ የያዘው ታሪክ በልኩ የተነገረ እስካይመስል ድረስ ነው። በአመታት መካከል እጅግ አስገራሚ የሆኑ ክስተቶች በመርካቶ ውስጥ ተመዝግበው ይገኛሉ። ከመርካቶ ጓዳ አንዳንዶች የገባቸውን በፊልም፣ በግጥም እንዲሁም በተለያዩ መንገዶች ለማቅረብ ጥረት አድርገዋል። ስንቶቻቸው በሚገባ እንደገለጡት ግን እርግጠኛ መሆን አይቻልም።

በቦሌ መንገድ ላይ ዘናጭ መኪና ይዞ የሚነዳ የመርካቶ ነጋዴ መርካቶ ውስጥ ግን አለባበሱ በተቃራኒው ሆኖ አንድ ተራ ሰው መስሎ ሊታይ ይችላል። ምክንያቱም ቦታው መርካቶ ነውና ሰዎች ዝቅ ብለው ከፍ ለማለት የሚታትሩበት ስለሆነ። መርካቶ የብዙ ሃሳቦች እርስ በእርስ ፍጭት መድረክ አድርገን ልንወስደውም እንችላለን፤ በተግባርም ነው። ነጋዴው በታታሪነቱ ወይንም ግብር በማጭበርበሩ፤ ግለሰቡ ሠርቶ ለማደር በመወሰኑ ወይንም ቀማኛ በመሆን በመሰለፉ፤ የመንግሥት ሰዎች ንግድን ተቆጣጥሮ ለሕዝብ በመሥራት ወይንም ለሙስና እጃቸውን ሰጥተው የሙስና ገበያ በመሆናቸው፤ ወዘተ።

ከመርካቶ ገጠመኞች መካከል አንዱን እንደመነሻ ተመልክተን የግራ ቀኙን ነጥብ እናንሳ። አባት፣ ሚስትና ሁለት ልጆች በመርካቶ መካከል ዕቃ ተሸክመው ወደ አውቶቡስተራ ለመድረስ እያቀኑ ነው። አውቶቡስ ይዘው ወደ ሌላ አካባቢ ለመሄድ፤ አዲስ አበባን እንደ መሸጋገሪያ እያደረጉ። አባት ፍራሽ ተሸክሞ በሌላ እጁ አንዱን ልጅ ይዟል። እናትም ዕቃ ይዛ በሌላኛውን ልጅ ይዛለች። በዚህ መሃል ተወንጫፊ ሌባ የአባትን እጅ መትቶ ከእጁ ያለውን ሰዓት ቀምቶ እግሬ አውጪ ብሏል። አባትም ፍራሹን ከመሬት ላይ ጥሎ ሌባውን በማሳደድ መንገድ ውስጥ ነው። «ሌባ ሌባ ሌባ» በሚል ጩኸት አካባቢው በግርግር ውስጥ ነው። ሌባው በሚያውቀው የመርካቶ ጉራንጉር ውስጥ ገብቶ ተሰወረ። አባትም ሰዓቱን አስረክቦ ያለ ውጤት ተመለሰ። የሁለት ሀሳቦች ትንቅንቅ የሌብነት እና የራስን ሀብት የማስጠበቅ።

ሌሎች መሰል የመርካቶ ገጠመኞችን ብንሰማ የምናገኘው ታሪክ አስደማሚ ይሆናል። የስርቆት ድራማዎች በሚገባ ተቀርጸው የሚተወንባቸው ቦታ መርካቶ እስኪመስል ድረስ በመርካቶ ጀርባ ላይ መሰል ትእይንቶች ይገኛል። ትልቅ ልውውጥ፤ ገንዘብ ለብዙ ነገሮች ገንዘብ ሆኖ የሚቀርብበት ስፍራ፤ ግራ ቀኙ ሌባ መስሎ በነፃነት መመላለስን የሚገድብበት ቦታ፤ መርካቶ። በሰዎች ዘንድ ያለ የበዛን ሀሳብ የሚያሳይ የቁሳቁስ ብቻም ሳይሆን የሀሳብ አተገባበር ማሳያ ስፍራ። ሀሳብ ተጽንሶ፤ ሀሳብ የሚወለድበት። በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊነቱ የሚነበብበት ስፍራ።

በግራም በቀኝም ስላለው በሀሳብ መስመር አልፈን ከማየታችን በፊት አንድ የልቦለድ መጽሐፍ ማንበብ የሚወድ ወጣትን እናንሳ። ወጣቱ አንባቢነቱን ብቻም ሳይሆን ተቀያያሪ ባህሪውንም ያውቀዋል። ተቀያያሪ ባህሪው የሚመጣው ከሚያነበው መጽሐፍ የሆነ። ራሱንም «እንዳነበብኩት» እያለ ይጠራል። እንዳነበብኩት ዙሪያ ገባውን የሚያየው እንዳነበበው መጽሐፍ ነው። የስለላ መጽሐፍ ባነበበ ጊዜ አጠገቡ ያለው ሰው ሁሉ ሰላይ ይመስለዋል። የስነልቦና መጽሐፍ ካነበብ አጠገቡ ያለው ሰውን ድርጊት በስነልቦናው መጽሐፍ ዓይነት እያየ ይመለከታል። ከትንሽ ተነስቶ ቁጃር ስለሆነ ሰው ካነበበ የሚያየውን ነገር በሙሉ እንዴት ወደ ቁጃርነት እንደሚወስደው ይሆናል፤ በአጭሩ እንዳነበበው ነው።

በግራም በቀኝም የበረከተ ድምጽ ባለበት ዘመን ውስጥ ስንኖር ራሳችንን ልንጠይቅ የሚገባው ነገር ዛሬ እየኖንበት ያለው ኑሮ ትናንት በተዘራው ሀሳብ ምን ያህል ተጽእኖ ውስጥ መሆኑን ነው። ትናንት የተዘራው ዛሬ ላይ ሕይወታችን ነው፤ የዛሬው ደግሞ ነገ። ግራ ቀኝ! የከበረውን መለየት መቻልና በከበረው ውስጥ መሆኑ ያለውን ፋይዳ ስንረዳ ለከበረ ሀሳብ ቦታን ሰጥተን ሕይወታችንን እንቃኛለን።

### የከበረውን መለየት መቻል

በግራም በቀኝም ያለው የሀሳብ ውጤት ነው። ሀሳቡ

> **ያለ ሃሳብ ከመሠልጠን፣ ያለ ሥልጣኔ ማሰብ ይሻላል። ያለ ሃሳብ መሠልጠን ያለ ልክ የተሰፋን ልብስ መልበስ ነው። ሰውዬው እየወፈረ ይሄድና ልብሱን መቅደዱ አይቀርም። ልብሱ ለሰውዬው እንጂ ሰውዬው ለልብሱ ሊሰፋ አይችልምና**

የታሰበበት ይሁን ያልታሰበበት የዛሬውን መልክ በብዙ ወስኗል። መልካም ሃሳብ ወደ ተሻለ አቅጣጫ ሕይወትን ሲመራ ክፉ ሃሳብ ደግሞ በተቃራኒው። ዲያቆን ዳንኤል ክብረት በአንድ ወቅት ስለ ሀሳብ በጻፈው ጽሑፍ ውስጥ ሃሳብ ምን ያህል የከበረ ነገር መሆኑን ለማሳየት አንድ ታሪክን አቅርቦ ነበር።

ታሪኩ የሚከተለው ነው፤

አንድ ጊዜ አንድ የሮም የጦር መሪ ወደ አንድ የአይሁድ ከተማ ይገባል። የከተማዋን ሕዝብም ወደ አንድ የማጎርያ ሥፍራ ይሰበስባቸዋል። የከተማዋ ቤቶች አንድ ሳይቀሩ እንዲቃጠሉ ለወታደሮቹ ትእዛዝ ይሰጣል። በዚያ ጊዜ ሕዝቡ በቤቶቹ ውስጥ ያለውን ሀብት ለማውጣት ለመነ።የሮም ወታደሮች ግን አልፈቀዱም። የሕዝቡ ልመና እየበዛ ሲሄድ የወታደሮቹ አለቃ አንድ ነገርፈቀደ።

ሕዝቡ ሁሉ ተስማምቶ አንድ እጅግ የሚፈልጉትን ነገር ብቻ እንዲያወጡ። ሕዝቡ ተተራመሰ።አንዱ አንድ ሌላውም ሌላ ይላል። ከዚያ ሁሉ ሀብት መካከል እጅግ አስፈላጊ የሆነውን ነገር መርጦ ማውጣት አስቸጋሪ ሆነ። ማንንም የሚያስማማ ሀሳብ ማግኘትም አልተቻለም።

በመጨረሻ ሕዝቡ በአንድ ነገር ተስማሙ። ረቢው (የአይሁድ መምህር) በጉዳዩ ላይ እንዲወስን። ረቢው ወደ ከተማው ገቡ። ያቀኑትም ወደ ምኩራቡ ነበር። ሕዝቡ ሁሉ ምን ይዘው ሊወጡ እንደሚችሉ የየራሱን ግምት ይሰጥ ነበር። አንዳንዱ ደግሞ የሚሆነውን ለማየት በጉጉት ይጠብቅ ነበር።

ረቢው ወደ ሕዝቡ ሲመለሱ አንዳች የሚታይ ነገር አልያዙም። ወደ ወታደሮቹ አለቃ ሄደው አንዲት ያረጀች በብራና የተጻፈች መጽሐፍ መሳይ ነገር አሳዩት። የወታደሮቹ አለቃ ስቆ አሰናበታቸው። እናም ከተማዋ ተቃጠለች።

የከተማዋ ሕዝብ በጉዳዩ ላይ በጣም በመበሳጨቱ ረቢውን ሊገድላቸው ተነሣ። ስንት የወርቅ እና የብር ሀብት እያለ። ስንት በከበሩ ድንጋዮች ያጌጠ ሀብት እያለ አንዲት ያረጀች ብራና ይዘው በመምጣታቸው በምርጫችን ተሳስተናል አለ።

ወታደሮቹ ከተማዋን አቃጥለው ሲሄዱ የከተማዋ ሰዎች ሜዳ ላይ ፈስሰው ረቢውን ጠየቋቸው። ለምን? ሲሉ።

ረቢው እንዲህ አሉ። «አዎን በከተማዋ ለዓይን የሚያጓጓ ብዙ ሀብት አለ። ወርቅ አለ። ብር አለ። የከበሩ ድንጋዮችም አሉ። የሐር ልብሶች አሉ። ከተልባ እግር የተሠሩ ልብሶች አሉ። የጌጥ ዕቃዎች አሉ። ሁሉም አሉ። ይህ ግን ከሁሉ ይበልጣል።

“እንዴት?” አለ ሕዝቡ።

«እነዚያ ያለቁ ነገሮች ናቸው። አንድ ጊዜ ይሸጣሉ፤ ይበላሉ። ያልቃሉ። ለጊዜያዊ ችግር ይሆናሉ። እኛን ከረሃብ ያላቅቃሉ። ነገር ግን አያዘልቁንም። ሰው የሚበላ ብቻ አይደለም። የሚጠጣም ብቻ አይደለም። ሰው ማለት ሁለት ነገር ነው። መንፈስ እና ሥጋ። ሥጋ ማለት ምንድን ነው? ሥጋ ውሱን ነው።

በቦታ፣ በጊዜ እና በዐቅም ይወሰናል። መንፈስስ? መንፈስ ግን አይወሰንም። መንፈስን በአንድ እሥር ቤት ልትወስነው አትችልም። ወደ ላይ ወደ ምጥቀቱ፤ ወደ ታችም ወደ ጥልቀቱ ይወርዳል። መንፈስ አገር የለው። ይዋኛል። ይቀዝፋል። መንፈስን በጊዜ አትገድቡትም። ወደ ኋላ ወደ ትናንት፣ ወደ ፊት ወደ ነገ ይጓዛል። ሥጋን በአንድ ቅርጽ ብቻ ማኖር ይቻላል። በአንድ ሞላላ ቤት፤ በአንድ አራት ማዕዘን ቤት፤ በአንድ ጉድጓድ ማኖር ይቻላል። መንፈስን ግን በአንድ ቅርጽ ማኖር አይቻልም።

ለተወለደ ልጅ ስም ይወጣል እንጂ ለወጣ ስም እንዴት ልጅ ይወለዳል? ዳዊት የሚባል ስም አውጥቶ እንዴት እንደ ዳዊት ያለ ልጅ ለመውለድ ይቻላል? መንፈስን በቅርጽ መወሰን እንዲህ ነው። ማሰብ ያለብህ እንዲህ ያለ አስተሳሰብ ነው፤ አንተ የዚህ ወይንም የዚያ ቡድን አመለካከት አለህ፤ አንተ ይህንን ወይንም ያንን ብቻ ሁን ማለት አይቻልም። መንፈስ ነፃነትን ይፈልጋል። ዓይኑን ጨፍኖ ወደ ውስጥ፣ ዓይኑንም ገልጦ ወደ ውጭ መጓዝ ይሻል።

«እዚህ ውስጥ ወርቅ ወይንም ብር የለም። እዚህ ውስጥ ሀሳብ አለ። ሰውን ሰው የሚያደርግ ሃሳብ አለ። ሰው ለሕልውናው ዓላማ እንዲኖረው። የሚኖርበት ምክንያት እንዲኖረው፤ ሰው ከመብላት እና ከመጠጣት በላይ ማሰብ እንዲችል። ሰው ከመኖር በላይ ማሰብ እንዲችል። ሰው ከችግሮቹ በላይ መኖር እንዲችል። ለነገ ሲል ዛሬን፣ ለጭንቅላቱ ሲል ሆዱን፣ ለነፍሱ ሲል ሥጋውን፣ ለሌላው ሲል ራሱን መሠዋት እንዲችል የሚያበቃ ሃሳብ አለ።

«ይህ ሃሳብ ሲሞት ያን ጊዜ ከተማችን ፈጽማ ትጠፋለች። ይህ ሃሳብ ካልሞተ ግን ዘጠኝ ጊዜ ብትጠፋ እንኳን አሥር ጊዜ አብልጠን እንገነባታለን። ይህ ሃሳብ ከሞተ ሆዳችን አድጎ ጭንቅላታችን ይቀጭጫል። ይህ ሃሳብ ካልሞተ ግን ሆዳችን ቀጭጮ ጭንቅላታችን ያድጋል። ይህ ሃሳብ መቶ ሀገራችን ሀብታም ትሆን ይሆናል። ነገር ግን ሆዳሞች የሞሉባት ሀብታም ሀገር ትሆናለች። ሆዳሞች ደግሞ መጀመሪያ የሀገራቸውን ሀብት ይበላሉ። ቀጥለው ሕዝባቸውን ይበላሉ። በመጨረሻም እርስ በርሳቸው ይበላላሉ።

ያለ ሃሳብ ከመሠልጠን፣ ያለ ሥልጣኔ ማሰብ ይሻላል። ያለ ሃሳብ መሠልጠን ያለ ልክ የተሰፋን ልብስ መልበስ ነው። ሰውዬው እየወፈረ ይሄድና ልብሱን መቅደዱ አይቀርም። ልብሱ ለሰውዬው እንጂ ሰውዬው ለልብሱ ሊሰፋ አይችልምና። ያለ ሃሳብ መሠልጠን ሰውዬውን ለልብሱ እንደማዘጋጀት ያለ ነው። ሰውዬው ከልብሱ በላይ እንዳይሆን ወይ ታስርቡታላችሁ፣ ያለበለዚያም በወፈረ እና በረዘመ ቁጥር ትቀንሱታላችሁ፣ ያለበለዚያም ውፍረቱን እና እድገቱን ለመቀነስ ሌላ ቅጣት ትቀጡታላችሁ።

ሃሳብ የሌለበት ዕድገት እና ሥልጣኔ እንደዚህ ነው። ሰው ምንም ቢሆን ማሰቡን አይተውም። ያለ ሰው የሚኖር ሃሳብ፣ ያለ ሃሳብ የሚኖርም ሰው የለም። ስለዚህ ለኛ ሃሳብ ይበልጥብናል። ይህ መጽሐፍ ከኛ በፊት የነበሩ ሰዎች ያሰቡትን፤ በዘመናችን ያላችሁ ሰዎች ያሰባችሁትን ነገር ይዟል። ለሀገር ትልቁ ሀብቷ ሃሳቧ ነው። በሀገር ዋናዎቹ ሰዎች ቀድመው እና ልቀው ማሰብ የሚችሉ ዜጎቿ ናቸው። የበቁ አሳቢዎች የበቁ መሪ ዎችን መፍጠር ይችላሉ፤ የበቁ መሪዎች ግን የበቁ አሳቢዎችን መፍጠር አይችሉም።

ሃሳብ እና ሃሳቢ የሞተባት ሀገር ወይ ሞታለች፣ ወይ ለመሞት ተዘጋጅታለች። እናም ወዳጆቼ አትዘኑ። ሃሳባችሁን የወሰደባችሁ የለም። ማሰብ ከቻላችሁ ዓለም ሁሉ የእናንተ ናት። ከሀገር የሚበልጥ መቼም የለም። ሀገርንም ቢሆን እንኳን የሚፈጥራት ሀሳብ ነው። ያለ ሃሳብ በሀገር ከመኖር፣ ያለ ሀገር እያሰቡ መኖር ይበልጣል። ማሰብ ካልቻላችሁ ግን በጣታችሁ ያለው ቀለበት እንኳን የእናንተ አይደለም። ለዚህ ነው ይቺን መጽሐፍ የመረጥኳት።

እንዳትበሉ የሚከለክሏችሁ፣ እንዳትኖሩ የሚከለክሏችሁ፣ እንዳትሠሩ የሚከለክሏችሁ ብዙም



አይጎዱችሁም። እነርሱ እንስሳነታችሁን ነው የከለከሏችሁ። እንዳታስቡ የሚከልክሏችሁ ግን አደገኞች ናቸው። ምክንያቱም የከለከሏችሁ ሰውነታችሁን ነውና።»

በዚህ ታሪክ ውስጥ የምናገኘው ቁምነገር የሰው ልጅ የሰውነት ክብሩ የሚገኘው በሀሳብ ውስጥ መሆኑን ነው። ሀሳብ የከበረውን መለየት መቻል የከበረውን ምርት አድርጎ ለማስገባት ይረዳል። የሃሳብ መጥራቱም ለዚህ ነው የሚጠቅመው። ከቁስ ነገር ይልቅ ለጤናማ ሃሳብ ትኩረት መስጠት የቻሉ በሕይወታቸው ውስጥ የሚብላላውን ነገር ጥራት ይወስናሉ።

የሀሳብ ሕይወት የከበረ ሆኖ ሳለ ግን ሀሳብን ማሰብና ያሰቡትን መኖር ውስጥ የምንኖርበት ከባቢ የማይመች ሆኖ ሊገኝ ይችላል። ማሰብ የተፈቀደ መሆኑ አለመሆኑ ላይ እርግጠኝነት በሌለበት ሁኔታ ውስጥ እየኖርንም ያለን ይመስላል። ጥያቄውን አስቀድመን ጥቂት እንበል፤

### ማሰብ ይፈቀዳል?

የጥያቄው መልስ ከሁለት አቅጣጫ ሊሆን ይገባዋል። በአንድ አቅጣጫ አንድ ሰው በውስጡ የወደደውን ማሰብ ይችላል ወይ? ሲሆን ሌላው ግን ያሰበውን መተግበር ይፈቀድለታል ወይ? ወይንም እንዳሰበው መኖር ይፈቀድለታል ወይ? የሚል ነው።

አስተዳደጋችን ሃሳብን በማበረታታት ዘንድ ያለው መገለጫ የደበዘዘ ነው። ሃሳብን ከማበረታታት ማሳነስ በሰፊው እንደ ማህበረሰብ ይታይብናል። አዳዲስ ሃሳቦችን ሰዎች ለመተግበር ሲነሱም ዙሪያ ገባው በእሾህ የታጠረ ሆኖም ይጠብቃቸዋል። ተቋማት አዳዲስ ሃሳብ እንዳይወጣ አንቀው የሚጠብቁም ይመስላሉ። ማሰብ በሕግ ደረጃ የተከለከለ የሆነ ይመስል ለአዲስ ሃሳብ በመጣ ቁጥር የሚወረወረው ጦር ብዙም ነው።

ማሰብ ይፈቀዳል ወይ የሚለውን ጥያቄ አንባቢው እያሰላሰለ የሀሳብ መንገዳችን የቀና ይሆን ዘንድ የማሳረጊያ ሁለት ነጥቦች እናንሳ፤

**1. ትኩረት በመስጠት ማሰብ፤**

ትኩረት በመስጠት ማሰብ ማለት የበለጠ ትኩረት ሊሰጠው ስለሚገባ ነገር በቅድሚያ በትኩረት በማሰብ ስለሌሎችም ነገሮች አስከትሎ ማሰብ ማለት ነው። አንድ ግለሰብ በሕይወቱ ውስጥ ጉልህ ለሚላቸው ነገሮች የሚያደርገው ሃሳብ ነው። ጉልህ ጉዳዮች ተገቢውን ትኩረት ተሰጥቷቸው ሲታሰብባቸው የሕይወት አቅጣጫ ጤናማውን መስመር ይይዛል። ከጉልህ ጉዳዮች ቀዳሚው ለግለሰቡ ራሱ ግለሰቡ ነው። አንድ ግለሰብ እንደ ግለሰብነቱ ስለ ብዙ ነገሮች ሊያስብ ይችላል። ነገርግን ስለ ራሱ የሚያስበው ከሁሉም ሊቀድም ይገባዋል። ባልንጀራህን እንደ እራሱ ሊወድ የተነሳ ሰው ከባለንጀራው በፊት ስለራሱ ሊያስብ የተገባው ነው። ግለሰባዊ ጤናማነት ነውና ወደ ቤተሰብ፣ ወደ ሥራ ወደ ማህበራዊ ሕይወት የሚጋባው።

**2. የተግባር ሰው ሆኖ ማሰብ፤**

በጤናማ ሃሳብ ሊቃኝ የማይገባው ምንም ነገር የለም። ሁሉም ነገር በጤነኛ ሃሳብ የተቃኘ ሊሆን ይገባዋል። ጤነኛ ሃሳብን ወደ መተግበር መሄድ ደግሞ ሌላኛው ወሳኝ ነጥብ ነው። ሃሳብን ለመተግበር መነሳት የሚፈልገው ጊዜ፣ ገንዘብ እንዲሁም ሌሎች ሀብቶች አሉ። የተግባር ሰው ሆኖ ለመገኘት ሃሳብን መተግበር ግድ የሚልም ለዚሁ ነው።

መልካም ለሀሳብ ጊዜ የመስጠት ቀናት ከፊታችን ይምጡ!

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# የጉጂ ቡና አልሚና ላኪ ሶስተኛው ትውልድ

**ፍሬሕይወት አወቀ**




በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ከሚመረቱ ቡናዎች መካከል አንዱ የጉጂ ቡና ነው፤ ቡናው ባለው ልዩ ጣዕም በዓለም ገበያም በእጅጉ ይፈለጋል:: የጉጂ ቡና ከዚህ ቀደም በሲዳማ ቡና ስም ነበር ለግብይት የሚቀርበው:: አሁን በስሙ ወደ ገበያ እየቀረበ ይገኛል:: የታጠበውም ሆነ ያልታጠበው የጉጂ ቡና በልዩ ጣዕሙ የተነሳ ተፈላጊነቱ እየጨመረ መጥቷል:: በዓለም ገበያ ተወዳጅነትን እያተረፈ ሲሆን፣ የቡና አልሚዎችን ትኩረትን መሳብ መቻሉን መረጃዎች ያመለክታሉ::

በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በቡና ልማትና ግብይት በተለይም ቡናን ለውጭ ገበያ በማቅረብ የሚታወቁ በርካታ ቢሆኑም፣ ቡናን ከሚያለማ ቤተሰብ ተገኝተው በቡና ውስጥ ኖረው ቡናን እያለሙ ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ ግን ጥቂቶች ናቸው:: እነዚህ ሰዎች ለቡና ካላቸው ቅርበት የተነሳ ዘርፉ ምን እንደሚያስፈልገው ጠንቅቀው ከማወቅ ባለፈ ለውጤታማነቱ በብዙ ይተጋሉ:: የዝግጅት ክፍላችንም ቡና ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ባስገኘበት በዚህ አመት፣ ለሀገር ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ እየሆነ ካለው ቡና ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸውን እንግዳ በዛሬው የስኬት ገጹ ይዞ ቀርቧል::

ተወልደው ያደጉት በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ጉጂ ዞን ቡሌ ሆራ ቅሌንሶ ነው:: የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በዚሁ ትውልድ ቦታቸው፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ በሀዋሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከታትለዋል:: በግብርናና በንግድ ዘርፍ ከተሰማራ ቤተሰብ የተገኙት እኚህ እንግዳችን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ባጠናቀቁ ማግስት ያደጉበትን የቡና ልማትና የቡና ንግድ መልሰው ተቀላቀሉ:: የዛሬው የስኬት እንግዳችን አቶ አክሊሉ ካሳ ::

አቶ አክሊሉ የናርዶስ ቡና ላኪ እና ቤካ ኮፊ ፕሮሰስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት መስራችና ባለቤት ናቸው:: በጉጂ ዞን ቡሌ ሆራ አካባቢ ቡናን እንዲሁም እንሰትን በማልማት ቀዳሚ ከሆነ የዘር ሀረግ የተገኙት አቶ አክሊሉ፣ ከቡናው በተጨማሪም በሆቴል ዘርፍ ተሰማርተው በምዕራብ ጉጂ ዞን ቡሌሆራ ላይ ቡሌሆራ ሆቴልን ገንብተዋል:: በዚህም 100 ለሚደርሱ የአካባቢው ነዋሪዎች የሥራ ዕድል ፈጥረዋል::

የአቶ አክሊሉ አያት አቶ ጭሪሳ ሲሳ ቡናን ጨምሮ እንሰትን ወደ ጉጂ አካባቢ በማምጣት የመጀመሪያው ናቸው፤ በንጉሱ ዘመን በነበራቸው ሰፊ የእርሻ መሬት ላይ ቡናና እንሰትን በስፋት በማምረት ይታወቁ ነበር:: የቡና ምርቱንም ነጋዴዎች ኤኔትሬ በሚባል ገልባጭ መኪና ገዝተው ሲወስዱ ያስታውሳሉ፤ የቡና ልማትና ግብይትን ወላጅ አባታቸው ከአያታቸው፤ እርሳቸው ደግሞ ከወላጅ አባታቸው እየተቀባበሉ እዚህ ደርሷል::

በወቅቱ ቡናን ወደ አዲስ አበባ ገበያ አምጥተው የመሸጥ ዕድሉ ያልነበራቸው ወላጅ አባታቸው ቡና ሰብሳቢ በሚል የንግድ ፈቃድ በግላቸው የሚያለሙትን ቡና ጨምረው የአካባቢውን አርሶ አደሮች ቡና በመሰብሰብ ለነጋዴዎች ያቀርቡ ነበር:: የወላጅ አባታቸውን ዱካ በመከተል ከፍተኛ እገዛ እያደረጉ ያደጉት አቶ አክሊሉም፣ ከልጅነታቸው ጀምረው ከአርሶ አደርነትና ከነጋዴነት የትኛው አዋጭ እንደሆነ ሲያመዛዝኑ አድገዋል:: በመጨረሻም ንግዱ የበለጠ አዋጭ እንደሆነ በማመን የቡና አቅራቢ ፈቃድ በማውጣት ወደ ንግዱ ስራ በይፋ ገቡ::

በወቅቱ የቡና ፈቃድ ከነበራቸው ጥቂት ቡና ሰብሳቢዎችና ቡና ላኪዎች መካከል አንዱ ከነበሩት ወላጅ አባታቸው የተረከቡትን የቡና ንግድ ለማሳለጥ በ1984 ዓ.ም ልክ እንደ አባታቸው ሁሉ እርሳቸውም የቡና ሰብሳቢ ንግድ ፈቃድ አወጡ:: በወቅቱ የግላቸውን ሥራ ጨምረው ወላጅ አባታቸውንም ጭምር በማገዝ ሥራውን በሚገባ ተለማመዱ:: ለዘርፉ ካላቸው ቅርበት የተነሳ በጥራት ሠርተው ውጤታማ መሆን ሲችሉ ከሰብሳቢነት ወደ አቅራቢነት ተሸጋገሩ::

ወደ ቡና አቅራቢነት የተሸጋገሩት አቶ አክሊሉ፤ እሸት ቡና መፈልፈያ ማሽን በመትከል የተፈለፈለውን ቡና ወደ አዲስ አበባ በማምጣት ለላኪዎች ያስረክቡ ነበር:: በዚሁ ሥራ አዲስ አበባ ሲመላለሱ የሥራውን ስፋትና ጥልቀት እንዲሁም ውጤቱን በሚገባ መረዳት ቻሉ:: የተረዱትን ዕውነትም በተግባር ለማዋል ጊዜ አልፈጁም:: ቡናን ከማልማት ጀምረው ሰብሳቢና አቅራቢ ሆነው አዲስ አበባ በነበራቸው ምልልስ የወጪ ንግዱን በከፊል ተረዱ:: ‹‹ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል›› ነውና ብሂሉ ቡናን ወደ ውጭ ገበያ ለመላክ ፍላጎት አደረባቸው::

በ1994 ዓ.ም ብዙ ውጣውረዶችን አልፈው የላኪነት ንግድ ፈቃድ አወጡ:: ቡና ላኪ ለመሆን ብዙ ሂደቶች ያለፉ ሲሆን አዲስ አበባ ከተማ ላይ ቢሮ ከመከራየት ጀምሮ እንደ ኮምፒዩተር፣ ስልክና የመሳሰሉትን ግብዓቶች ማሟላት ከጉጂ ለመጡት ለአቶ አክሊሉ ቀላል ጉዳይ አልነበረም:: ይሁንና አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታዎች በሙሉ አሟልተው ከ1994 ዓ.ም ጀምረው ላለፉት 20 ዓመታት የጉጂ ቡናን ወደ ውጭ ገበያ በመላክ ለአገሪቱ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እያስገቡ ይገኛሉ::

አቶ አክሊሉ በላኪነት ብቻ 20 ዓመታትን አስቆጥረዋል፤ በቡና ልማቱና በአገር ውስጥ ንግዱ ግን ነብስ ካወቁ ጊዜ አንስቶ ኖረውበታል:: ሕይወታቸው በሙሉ ከቡና ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው በመሆኑም ዘርፉ ላይ ትኩረት አድርገው ይሠራሉ:: የቡና ሥራ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያስፈልገውና እንደ አይናችን ብሌን ልንንከባከበው የሚገባ ስስ ብልት ነው ሲሉም ገልጸው፣ ሥራው እርጋታን የሚፈልግ እንደሆነም ይናገራሉ::

የቡና ገበያ ዓለማቀፍ ገበያ እንደመሆኑ አንድ ጊዜ ሲወጣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ይወርዳል የሚሉት አቶ አክሊሉ፣ በከፍታውም ከፍ ማለት እንዳለ ሁሉ ሲወርድም አብሮ መውረድ የግድ ነውና ባሕሪውን ማወቅና በጥንቃቄ መጓዝ የግድ ነው ይላሉ:: ቡና እዩኝ እዩኝ የማይወድና እርጋታን የሚፈልግ ሥራ እንደሆነም ይገልጻሉ::

ከቤተሰባቸው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የቡና ልማትና ግብይት እየመሩ ያሉትና በዚህም ሶስተኛው ትውልድ ለመሆን የበቁት አቶ አክሊሉ፤ በጉጂ አካባቢ በ105 ሄክታር መሬት ላይ 200 ቋሚ ሠራተኞችን በማሰማራት ቡና እያለሙ ናቸው:: ቡና በሚደርስበት ጊዜ ደግሞ በቀን ከ400 እስከ 500 ለሚደርሱ ዜጎች ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ይፈጥራሉ:: ከዚህ በተጨማሪም በአካባቢው የሚገኙ አምስት ሺ አርሶ አደሮችን በማሰባሰብ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል እያደረጉ አርሶ አደሮቹ የሚያለሙትን ቡና ይረከባሉ:: አርሶ አደሮቹም በዕለቱ በዋለው የቡና ገበያ ዋጋና ባቀረቡት የቡና መጠን ልክ ተከፋይ ይሆናሉ::

አርሶ አደሮቹ የተሻለ ተከፋይ እንዲሆኑ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ የግድ መሆኑንም ጠቅሰው፣ ችግኝ ከማቅረብ ጀምሮ የተለያዩ እገዛዎችን ከናርዶስ ቡና ላኪ ድርጅት እንዲያገኙ አንደሚደረግም ነው የሚናገሩት:: ለአብነትም ችግኝ በማፍላት፣ በጉንደላ፣ በምርት አሰባሰብና በአፈር አጠባበቅ ዙሪያ አስፈላጊውን ሁሉ እገዛ በባለሙያዎች እንዲያገኙ ይደረጋል:: ይህም ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ ባለፈ ጥራቱ የተጠበቀና በተፈጥሮ ኦርጋኒክ የሆነውን የጉጂ ቡናን ለዓለም ገበያ ማቅረብ አስችሏቸዋል:: በዚህም ናርዶስ ቡና ላኪ ድርጅት የኦርጋኒክነት መለያን ጨምሮ የጥራት ደረጃቸውን የሚገልጹ የምስክር ወረቀቶችን ማግኘት ችሏል::

እሸት ቡናው እዛው ጉጂ በሚገኘው መፈልፈያ ጣቢያቸው ተፈልፍሎና ደርቆ አዲስ አበባ ይደርሳል:: አዲስ አበባ በሚገኘው መቀሸሪያና ማበጠሪያ ማዕከላቸው ደግሞ ቡናው አስፈላጊው ማጣራት ተደርጎለት ደረጃውን በጠበቀ መንገድ ተዘጋጅቶ ለውጭ ገበያ ይሰናዳል:: ይህ ሥራ በሚከናወንበት ናርዶስ ቡና ላኪ ድርጅት ውስጥ ደግሞ ከ80 በላይ ለሆኑ ሠራተኞች በቋሚነት የሥራ ዕድል ተፈጥሯል::

የዛሬ 20 ዓመት ቡና ወደ ውጭ መላክ ሲጀምሩ ቄራ አካባቢ ቢሮ ተከራይተው ይሰሩ እንደነበር የሚያስታውሱት አቶ አክሊሉ፣ በብዙ ልፋትና ጥረት፤ እርጋታና ትዕግስትን ገንዘብ በማድረግ ጭምር ቀስ በቀስ ዛሬ ላይ ደርሰዋል:: በአሁኑ ወቅት ግን በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ማሰልጠኛ አካባቢ 4ሺ 500 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ፋብሪካቸውን ገንብተው ቡናውን ለውጭ ገበያ ዝግጁ በማድረግ ይልካሉ:: ሥራውን ከዚህ በበለጠ አስፍቶ ለመሥራትም ማስፋፊያ ጠይቀው በዚሁ ቦታ 8000 ካሬ ሜትር ስፋት ያለውን ቦታን አግኝተዋል::

‹‹ቡና የአገሪቱ ትልቅ ሃብት እንደመሆኑ እንደ አይናችን ብሌን ልንንከባከበው ይገባል›› የሚሉት አቶ አክሊሉ፤ የቡናው ዘርፍ ካለፉት ዓመታት በተሻለ አሁን ባለቤት እያገኘ መሆኑንም ነው የተናገሩት:: በዘርፉ መሠራት ያለበት ሥራ አሁንም ገና ብዙ እንደሚቀረው አስገንዝበዋል:: ከሌሎች አገራት ጋር ሲወዳደር በልማቱም ይሁን በወጪ ንግዱ እንዲሁም ዋናው ምንጭ የሆነው አርሶ አደር ላይ ምንም እንዳልተሰራም ይጠቁማሉ:: በማስታወቂያውም ቢሆን እንዲሁ ብዙ ይቀረናል ይላሉ::

እሳቸው እንደሚሉት፤ እነዚህ ሁሉ ሥራዎች በሚገባ ባይሠሩም የኢትዮጵያ ቡና በአሁኑ ወቅት በራሱ ጊዜ ገፍቶ እየወጣ ነው:: በዘርፉ የሚታዩ ክፍተቶችን በመድፈን በተለይም ቡና አምራቹ ዘንድ ወርዶ መሥራት ከተቻለ የኢትዮጵያ ቡና ከዚህም በበለጠ ውጤታማ መሆን ይችላል::

ከቡና መዳረሻ ሀገሮች አኳያም ሲያብራሩ በአሁኑ ወቅት ቻይናን ጨምሮ ብዙ በርካታ የዓለም አገራት የኢትዮጵያን ቡና እንደሚፈልጉ ይገልጻሉ:: ስለዚህ ይህን ዕድል መጠቀም እንዲቻል ቡናን በመጠንና በተሻለ ጥራት ማምረት የግድ መሆኑን ያመለክታሉ::

የናርዶስ ቡና ላኪ ድርጅት የገበያ መዳረሻዎችን አስመልክወተው ሲገልጹም በመላው ዓለም ተደራሽ እንደሚሆን ነው የተናገሩት:: አውሮፓ፣ አሜሪካ፣ ኤዢያ በተለይም በአሁኑ ወቅት ቻይና የጉጂን ቡና ተመራጭ በማድረግ አንደኛ ገዢ እየሆነች መጥታለች:: ዘንድሮ ናርዶስ ቡና ላኪ ብቻውን ሶስት ሺ ቶን ቡና ለውጭ ገበያ በማቅረብ እቅዱን ማሳካት ችሏል ብለዋል::

አቶ አክሊሉ እንዳሉት፤ ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድም ሰፋፊ ማህበረሰብ አቀፍ ሥራዎችን ሰርተዋል:: በትውልድ አካባቢያቸው መንገድ፣ ድልድይ፣ ውሃ፣ ትምህርት ቤቶችን በስፋት ሠርተዋል፤ በቡሌ ሆራ ቅሌንሶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሚማሩ ሴት ተማሪዎች የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ ያቀርባሉ:: ቁሳቁሱ ቡና ገዢ ከሆኑት አገራት መካከል አንዷ ከሆነችው ኒዮርክ ጋር ስምምነት በማድረግ ለዓመት የሚበቃውን አንድ ጊዜ በማምጣት ያቀርባሉ::

የሴቶች ንጽህና መጠበቂያው መልሶ ጥቅም ላይ የሚውልና የሚታጠብ መሆኑን ጠቅሰው፣ በአሁኑ ወቅት ተማሪዎቹን በማሰልጠን ራሳቸው እንዲያመርቱት እየተደረገም ነው ብለዋል:: ለዚህም አስፈላጊውን የስፌት መኪኖች፣ የተለያዩ ጨርቆች፣ ክሮችና ሌሎች ቁሳቁስ በማሟላት ተማሪዎቹ ሠርተው መጠቀም እንዲችሉ አድርገዋል:: አቶ አክሊሉ በማንኛውም አገራዊ ጉዳዮች መንግሥት ለሚያደርገው ጥሪ ምላሽ እየሰጡ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ይህንኑ አጠናክረው እንደሚቀጥሉ አረጋግጠዋል::

እሳቸው እንዳሉት ናርዶስ ቡና ላኪ ድርጅት አሁን ለዓለም ገበያ እያቀረበ ካለው የቡና መጠን በላይ ለማቅረብና የጥራት ደረጃውንም ከፍ ለማድረግ ራዕይ ሰንቆ እየሠራ ነው:: ለተግባራዊነቱም ዋናው ሥራ የሚሠራው ታች አርሶ አደሩ ዘንድ መሆኑን በማመን አርሶ አደሩ ጋ ወርደን እንሠራለን ብለዋል:: መንግሥትን ጨምሮ በዘርፉ የተሰማሩ አካላት ከታች ከመነሻው አርሶ አደሩ ላይ ብዙ መሥራት እንዳለባቸውም ነው ያስገነዘቡት::

እናም በወጪ ንግድ ቀዳሚ ከሆነው ቡና አገሪቷ ማግኘት የሚገባትን ገቢ እንድታገኝ፣ የታመመው ኢኮኖሚ እንዲያገግም ብሎም ዘርፉ እያስመዘገበ ያለው ውጤት ይበልጥ እንዲሻሻል መንግሥትን ጨምሮ የዘርፉ ተዋናዮች በሙሉ የቤት ሥራቸውን እንዲወጡም ነው የጠየቁት:: አበቃን::

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የአዳማ - አዋሽ የፍጥነት መንገድ

**መላኩ ኤሮሴ**

ኢትዮጵያን በአራቱም አቅጣጫ ካሉ የጎረቤት አገራት መንገድን ጨምሮ በተለያዩ መስኮች ለማስተሳሰር ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ነው:: ኢትዮጵያን ከጅቡቲ፣ ከኬኒያ፣ ከሱዳን እና ከደቡብ ሱዳን ጋር ለማስተሳሰር በርካታ የመንገድ መሰረተ ልማት ስራዎች ተካሂደዋል፤ እየተካሄዱም ይገኛሉ:: ግንባታቸው እየተከናወኑ ከሚገኙ የትራንስፖርት መተላለፊያ ኮሪደሮች መካከል ከአዲስ አበባ እስከ ጂቡቲ የሚዘልቀው የትራንስፖርት ኮርደር አንዱ ነው::

የኢትዮጵያ - ጁቡቲ የትራንስፖርት መተላለፊያ ኮሪደር የሀገራችን ገቢ - ወጪ ንግድ ዋነኛው ማሳለጫ ኮሪደር ነው:: ከሀገሪቱ የወጪና ገቢ ንግድ 90 በመቶ የሚሆነው በዚህ ኮሪደር እንደሚተላለፍ መረጃዎች ያሳያሉ::ይህ መንገድ ከተገነባ በርካታ ዓመታትን ያስቆጠረ ነው::መንገዱ የኮሪደሩን አስፈላጊነት በሚመጥን መልኩ በዘመናዊ መንገድ የተገነባ አይደለም::

በዘመናዊ መንገድ የተገነባ ባለመሆኑ እና በመንገዱ በብዛት የሚመላለሱን የከባድ ተሽከርካሪዎችን ጫና ለመቋቋም ባለመቻሉ በተደጋጋሚ ጊዜያት ለጥገና ሲዳረግ ቆይቷል:: ይህንን ችግር ለመፍታት 84 ነጥብ 6 ኪሎ ሜትር የሚሸፍነው የአዲስ አዳማ የፍጥነት መንገድ በ10 ነጥብ ሶስት ቢሊየን ብር ተገንብቶ የዛሬ ስምንት ዓመት ገደማ ተመርቆ ለትራፊክ ክፍት ሆኗል:: የዚህ መንገድ መጠናቀቅ ለሀገሪቱ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ አስገኝቷል::

ሆኖም ከጂቡቲ አዲስ አበባ ድረስ ካለው ርቀት አንጻር የአዲስ አዳማ የፍጥነት መንገድ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም:: ከአዲስ አበባ እስከ አዳማ የነበረውን የፍጥነት መንገድ ከፍ በማድረግ የረጂሙ የኢትዮ - ጂቡቲ የትራንስፖርት ኮሪደር አካል የሆነ አዳማ - አዋሽ - ሜኢሶ - ድሬዳዋ ኮንታራት አንድ፤ አዳማ አዋሽ የፍጥነት መንገድ ግንባታ የዛሬ ዓመት ገደማ ተጀምሯል:: የአዳማ-አዋሽ ምዕራፍ አንድ 60 ኪሎ ሜትር የፍጥነት መንገድ ፕሮጀክት ግንባታን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የመሰረት ድንጋይ በማስቀመጥ በይፋ ማስጀመራቸው ይታወሳል።

የአዳማ አዋሽ ኮሪደር ለሀገራችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ወሳኝ ከሆኑ የመንገድ ኮሪደሮች መካከል አንዱ ቢሆንም፣ ነባሩ መንገድ የትራንስፖርት ፍሰቱን የሚመጥን እና ደረጃውን የጠበቀ ያልነበረ በመሆኑ ፣ በመንገዱ ተጠቃሚዎች እንዲሁም በንብረት እና በህይወት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሲያደርስ ቆይቷል::

የፍጥነት መንገዱን ከነባሩ መንገድ ጋር የሚያገናኙ ሶስት ማሳላጫዎች በአዳማ ፣ ኑራ ኤራ እና በወለንጪቲ ላይ የሚገነባለት ሲሆን፤የምዕራፍ አንድ አዳማ -አዋሽ ኮንትራት አንድ አዳማ-60 ኪ.ሜ የፍጥነት መንገድ 34 ሜትር ስፋት አለው ::

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሳምሶን ወንድሙ እንደሚሉት፤ እያንዳንዱ የተሽከርካሪ መጓጓዣ መስመር ሶስት ነጥብ ስድስት ሜትር ስፋትና ዘጠኝ ሜትር ሜዲያን (የመንገድ አካፋይ) ያካተተ ነው ::

የመንገድ አካፋዩ ከፍተኛ ስፋት ያለው ሲሆን አካፋዩ በዚህ ደረጃ እንዲሰፋ የተደረገው በተቃራኒ አቅጣጫ ያለን ተሽከርካሪ በመለየት አደጋን ለማስወገድ አልያም ለመቀነስ ነው ተብሏል:: የመንገዱ ትከሻ ስፋት ከአንድ ነጥብ አምስት ሜትር እስከ ሶስት ሜትር ነው:: አራት መኪኖችን በአንድ ጊዜ በግራና በቀኝ በኩል የማስተናገድ አቅምም አለው::

መንገዱ አጠቃላይ 90 ሜትር የወሰን ስፋት ያካተተ ነው:: ይህም በቀጣይ ለሚኖረው የማስፋፋት ስራ በቂ ቦታ እንዲኖር የሚያስችል ይሆናል::በተጨማሪም የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂን መሰረት በማድረግ ችግኞችን በመትከል አካባቢውን የማስዋብ ስራ ይሰራል::በፍጥነት መንገዱ ለመጠቀም የተቀመጠለት የፍጥነት ገደብ በሰዓት ከ100 እስከ 120 ኪ.ሜ ነው::

ከአዲስ አበባ እስከ አዳማ የተገነባው የፍጥነት መንገድ እስከ አዋሽ ከፍ ማለቱ ለሀገሪቱ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅምም ያስገኛል:: የመንገዱ መገንባት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ከፍተኛ ፋይዳ ያለው ስለመሆኑም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ግንባታውን ባስጀመሩበት ወቅትም አስታውቀው ነበር:: ይህ የፍጥነት መንገድ ተገንብቶ ሲጠናቀቅ ፣በአሁኑ ወቅት በመንገዱ




ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመቅረፍ ፣የትራንስፖርት ፍሰቱን የተሳለጠ በማድረግ እና በትራፊክ መስተጓጎል ሳቢያ ኢኮኖሚው ላይ የሚፈጥረውን ጫና በማቃለል የተሳለጠ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጥ ያስችላል ::

ከዚህ ባሻገርም የፍጥነት መንገድ ግንባታው በሚካሄድበት አካባቢ የሚኖረው ህዝብ ትስስር ይበልጥ እንዲጠናከር የሚያደርግ ነው:: በተለይም ግንባታው በሚከናወንበት አካባቢ የሚገኘውን የከረዩ ህዝብ ከሌሎች ወንድም ህዝቦች ጋር በማስተሳሰር ረገድ ከፍተኛ ፋይዳ ያለው ፕሮጀክት ነው::

በተጨማሪም፤ የፕሮጀክቱ ግንባታ የሚካሄድበት አዳማና ዙሪያው የትላልቅ ፣ መካከለኛና ቀላል ማኑፋክቸሪንግ፣የአግሮ ፕሮሰሲንግ ፋብሪካዎች እና የኢንዱስትሪዎች መገናኛ እንደመሆኑ እነዚህ ኢንዱስትሪዎች እና ፋብሪካዎች ኢትዮጵያ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ በመሸጋገር ከበለፀጉት ሀገራት ተርታ ትሰለፍ ዘንድ የፍጥነት መንገድ ፕሮጀክቱ ትልቅ አበርክቶ ይኖረዋል::

ፕሮጀክቱ የሀገሪቱን የንግድ እንቅስቃሴን ከማቀላጠፍ እና የአካባቢውን ማህበረሰብ ከማስተሳሰር ባሻገር ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያላት ግንኙነት ከመቼውም ጊዜ በተሻለ መልኩ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ትስስርን ለመፍጠር ትልቅ አስተዋጽኦ አለው::

የኢትዮጵያ ጂቡቲ የፍጥነት መንገድ አውን መሆን የአካባቢው ሀገራት ከዚህ በፊት ከነበረው በተሻለ መልኩ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ትስስራቸው እንዲሳለጥ ያደርጋል::በተለይም ኢትዮጵያ ከጎረቤት ጂቡቲ ጋር ያላት ዘመናትን ያስቆጠረው ግንኙነት ከመቼውም ጊዜ በተሻለ መልኩ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ትስስር ለመፍጠር ፋይዳው የጎላ ነው::

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር መረጃ እንደሚያመለክተው፤ መንገዱ የሚገነባው በስድስት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር ወጪ ሲሆን፣ በጀቱ የሚሸፈነው በአፍሪካ ልማት ባንክ እና በኢትዮጵያ መንግሥት ነው። ግንባታውንም ጂ. ኤም. ሲ. እና ኤል. አር. ቢ. ሲ. ኤል. የተሰኙ ዓለም አቀፍ ተቋራጮች በጥምረት እያከናወኑት ነው የሚገኙት።

በጂ.ኤም.ሲ. የአዳማ-አዋሽ የፍጥነት መንገድ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ ሱባረዲ ባሲረዲ እንደተናገሩት፤ ድርጅቱ መንገዱን በ4 ዓመት ተኩል ጊዜ ለማጠናቀቅ የሚያስችል በርካታ ስራዎች ከወዲሁ እያከናወነ ነው። በኮንትራት ስምምነቱ መሰረት የመንገድ ግንባታው ከተከናወነ በኋላም ለአምስት ዓመታት ተጨማሪ የጥገና ስራ የሚያከናውን ይሆናል::

የአስተዳደሩ የኮሙዩኒኬሽን ሀላፊ አቶ ሳምሶን ወንድሙ እንደገለጹት፤ የፍጥነት መንገዱ ግንባታ በመልካም ሁኔታ እየተካሄደ ይገኛል::ግንባታውን ከተያዘው ጊዜ አስቀድሞ በመጨረስ ለማስረከብ ለግንባታው የሚያስፈልጉትን ባለሙያዎችና መሳሪያዎች በማሟላት ሥራው ተጀምሯል። የካምፕ ግንባታ የስትራክቸር ስራዎች የዲዛይንና መሰል ተግባራትን በተቀመጠው እቅድ መሰረት ለማከናውን ተችሏል።

የፍጥነት መንገዱ ከእንስሳት እና ከሰዎች እንቅስቃሴ ነጻ ተደርጎ የሚገነባ በመሆኑ ለአሽከርካሪ ፍጹም ምቹ የማሽከርከር እድል እና ነጻነትን የሚሰጥ ከመሆኑም ባለፈ በአሁኑ መንገድ በተደጋጋሚ የንጹሃን ዜጎችን ህይወት እየቀጠፈ ያለውን እና የንብረት ውድመት እያስከተለ የመጣውን የትራፊክ አደጋ በመቀነስ ረገድ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል:: ይህም የሀገሪቱ ዋነኛው ችግር የሆነውን የትራፊክ አደጋ በመቀነስ በትራፊክ አደጋዎች ምክንያት የሚፈጠሩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግር ቀድሞ ለመከላከል የሚያስችል ነው::

አንደ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር መረጃ ፤ ፕሮጀክቱ ለበርካቶች የስራ እድልም ፈጥሯል:: እስካሁን ፕሮጀክቱ መሃንዲሶችን፣ኦፕሬተሮችን፣ሾፌሮችንና የጉልበት ሠራተኞችን ጨምሮ ከ 550 በላይ ለሆኑ ዜጎች የሥራ እድል ፈጥሯል።

የግንባታው ተቆጣጣሪ መሃንዲስ ኢንጂነር ራጁማ ቱር በበኩላቸው፤ የግንባታው ጥራት አስተማማኝ እንዲሆን በልዩ ትኩረት እየተሰራ ነው ማለታቸው የተጠቆመ ሲሆን፤ ለግንባታው ጥቅም ላይ የዋሉት መሳሪያዎች የመንገዱን ጥራት ለማረጋገጥ የሚረዱ መሆኑንም ይገልጻሉ፤ ግንባታውም በከፍተኛ ኃላፊነት እየተካሄደ መሆኑን መናገራቸው ተጠቁሟል::

ይሁን እንጂ የወሰን ማስከበር ችግሮች እና ለግንባታው የሚውል ሲሚንቶ በሚፈለገው መጠን አለመገኘት ግንባታው በሚፈለገው ፍጥነት ለማስኬድ ጫና እያሳደረ መሆኑን ነው አስተዳደሩ ያብራራው:: የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የወሰን ማስከበር ችግር ካለበት ውስጥ 18 ኪሎ ሜትር ቦታ ነጻ በማድረግ ማስረከብ የቻለ ሲሆን፣ ቀሪ ቦታዎችን ለግንባታው ነጻ ለማድረግ ከባለድርሻ አካላት ጋር እየሰራ መሆኑን የአስተዳደሩ ኮሙዩኒኬሽን ዘግቧል።

ፕሮጀክቱ ካለው ሀገራዊ ፋይዳ አኳያ ቀሪ ቦታዎቹን ነጻ በማድረግ ግንባታው በተያዘለት የጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቅ የሚመለከታቸው አካላት አፋጣኝ ርብርብ እንዲያደርጉም አስተዳደሩ ጠይቋል። በተለይም የክልሉ መንግስት እና የዞን አስተዳደር ችግሩን በአፋጣኝ ለመፍታት በትኩረት መስራት አለባቸው::ፕሮጀክቱ ለአካባቢው ማህበረሰብ ጭምር ያለውን ፋይዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት የኦሮሚያ ክልል መንግስት እና ህዝብ ከፌዴራል መንገዶች አስተዳደር ጋር በቅንጅት መስራት አለባቸው::

ከዚህ ቀደም በሀገራችን በአንዳንድ አካባቢዎች የፌዴራል መንግስት የሚያስገነባቸውን የመንገድ ፕሮጀክቶች ሌሎች አካላት እንደሚገነቡት ፕሮጀክት በመቁጠር ከፍተኛ ካሳ የመጠየቅ እና ካሳ ከተከፈለ በኋላ ንብረት አለማንሳት ችግሮች ለመንገዶች መጓተት መንስኤ ሲሆን ቆይቷል:: በእዚህ ፕሮጀክትም መሰል ችግሮች እንዳይፈጠሩ በትኩረት ሊሰራ ይገባል::

ለመንገዱ ግንባታ ሌላኛው ፈተና እየሆነ ያለው የሲሚንቶ እጥረት ነው::ለግንባታው የሚውል ሲሚንቶ በሚፈለገው መጠን አለመገኘት ሌላው ትልቅ ፈተና መሆኑን ተቋራጮቹ መጠቆማቸውን የአስተዳደሩ ኮሙዩኒኬሽን ሰሞኑን ዘግቧል:: ኢመአ አቅርቦቱ በሚሻሻልበት ሁኔታ ላይ ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኝ ከባለድርሻ አካላት ጋር እየሰራ መሆኑም ተጠቁሟል::

የሲሚንቶ እጥረት በመንግስት እና በግል ግንባታዎች ላይ እያስከተለ ያለውን ችግር ለመቅረፍ መንግስት በትኩረት እየሰራ መሆኑን በተደጋጋሚ ቢገልጽም፣ አሁንም አዳማ አዋሽ ኮንትራት አንድን የመሳሰሉ ፕሮጀክቶችን ጨምሮ ሌሎች ፕሮጀክቶች በሲሚኒቶ እጥረት ምክንያት ፈተና ላይ መሆናቸው መንግስት የሲሚንቶ ችግርን ለመቅረፍ ተጨማሪ እርምጃዎችን መውሰድ እንዳለበት አመላካች ነው::

የሲሚንቶ እጥረት ዋነኛው መንስኤ ህገወጥ ደላሎች መሆናቸውን በመግለጽ እነዚህን ህገ ወጥ ደላሎች ከገበያ ሰንሰለቱ ለማስወጣት እርምጃ መወሰዱን መንግስት በቅርቡ መግለጹ ይታወሳል:: ይህም ሆኖ ችግሩ አለመቀረፉ እየተነገረ ነው:: መንግስት አሁንም በጥናት ላይ ተመስርቶ ለእጥረቱ መንስኤ እየሆነ ያለውን ችግር ከስሩ ለመፍታት መስራት ይጠበቅበታል::

የአዳማ አዋሽ 60 ኪሎ ሜትር መንገድ ግንባታ ላይ እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን በመፍታት የዚህን ፕሮጀክት ግንባታ በማጠናቀቅ በቀጣይም ኢትዮጵያ ከአዲስ አበባ ተነስቶ ጅቡቲ ድንበር ደወሌ ድረስ የተዘረጋ የዘመናዊ መንገድ ባለቤት የሚያደርጋትን ከአዋሽ - ድሬዳዋ ያለውን ቀጣዩ የጅቡቲ ኮሪደር መንገድ በፍጥነት መንገድ ደረጃ ለመገንባት ርብርቡን ከወዲሁ መጀመር ያስፈልጋል::

# ርዕሰ አንቀፅ

## የለውጥ ኃይሉ ከፍ ባለ ማስተዋልና ጥበብ ሃገርን ማሻገር ችሏል!

የለውጥ ኃይሉ / መንግስት/ እንደ ሀገር ያጋጠመንን ችግር ከፍ ባለ ማስተዋልና ጥበብ ለማለፍ የሄደበት መንገድ ብዙዎች እንዳሰቡት ሳይሆን አነስተኛ ዋጋ ከፍለን እንድንሻገር አስችሎናል። በተለይም የተደራረቡ የውጪ ጫናዎችን አቅልለን ለመሄድ የፈጠረልን አቅም አሁን አሁን ውጤቱ በአደባባይ እየታየ ጭምር ነው።

በአንድ በኩል አሸባሪው ሕወሓት የህዝብን የለውጥ ጉዞ በመቀልበስ ወደ ቀደመው ሙት አገዛዝ ሀገርን ለመመለስ የሄደበት እብሪት ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን የቡድኑን የእብሪት አካሄድ ተጠቃሚ ያደርገናል ብለው ያሰቡ ታሪካዊ ጠላቶቻችንና የለውጡ መንገድ ያሰጋቸው ሀይሎች በሀገርና በለውጡ ሀይል ላይ ከፍ ያለ ጫና መፍጠራቸው ይታወሳል።

ጫናው በሀገር ውስጥ ታጣቂ ቡድኖችን ከመመልመልና ከማሰልጠን ጀምሮ የተደራጀ የሚዲያ ድጋፍን ጨምሮ ፤ መንግስትን/ የለውጥ ኃይሉን በማዕቀብ የማዳከም ስትራቴጂ ያካተተ እንደነበር የአደባባይ ሚስጥር ነው ። ይህንንም ታሳቢ ባደረገ መልኩ የተጣሉ ማዕቀቦችና የማዕቀብ ማስፈራሪያዎች እንደነበሩም ይታወሳል።

ዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙኃን /የሀገራት የመገናኛ ብዙኃን/ አንድ ዓይነት በሆነ ቅኝት በሃገሪቱና በለውጥ ሀይሉ ላይ በዘመቻ ደረጃ ሊገለጥ በሚችል መናበብ ዓለም አቀፉን ህብረተሰብ ስለ ኢትዮጵያ ትክክለኛውን መረጃ እንዳያገኝ ተንቀሳቅሰዋል። የስም ማጥፋት ዘመቻዎችን አካሄደዋል።

አለም አቀፍ ተቋማት ስለ ኢትዮጵያ ያላቸውን ዕይታ የሚያንሸዋርሩ መረጃዎችን በመልቀቅ በሀገሪቱ ላይ አላስፈላጊ ጫናዎች እንዲደረጉ አድርገዋል።በዚህም መላው ሕዝባችን በተቋማቱ ላይ የነበረውን እምነት መልሶ እንዲያጤነው የተገደደበት ሁኔታ ተፈጥሯል ።

አሸባሪው ሕወሓት በስልጣን ላይ በነበረባቸው ዓመታትም ሆነ ከስልጣን ከተወገደም በኋላ በዘረፈው የሕዝብ ሀብት የገዛቸው በየተቋማቱ የነበሩ ግለሰቦችና በየተቋማቱ የተሰገሰጉ የቡድኑ አባላት ፤በሃገሪቱ ላይ ከፍያሉ ጫናዎች እንዲደረጉ፤ ሀገረ መንግስቱ በራሱ አደጋ ላይ እንዲወድቅ የሚያደርጉ ሴራዎች በቅንጅት ተካሄደዋል።

ከጫናዎቹ ክብደትና ከሴራዎቹ ውስብስብነት አንጻር የለውጥ ኃይሉ ችግሩን የመፍታት አቅም በብዙዎች ጥያቄ ውስጥ ገብቶ ነበር፤ አንዳንዶችም በአደባባይ ሳይቀር ስጋታቸውን ሲገልጹ ተሰምቷል። ጓዛቸውን ጠቅልለው ለቀጣይ ውሳኔ ራሳቸውን ያዘጋጁም ጥቂቶች አልነበሩም ።

በተለይም አሸባሪው ሕወሓት በኢትዮጵያውያን ሀብትና ደም በምስራቅ አፍሪካ ፈጥሮት የነበረው የገዘፈ ማንነት በብዙዎች ዘንድ እንዲህ በቀላሉ ተፍረክርኮ የቃላት ክምር ይሆናል ብለው እንዲያስቡ እድል ሳይፈጥርላቸው ቀርቷል፤ እውነታው አደባባዮችን እስኪሞላና ተጨባጭ መሆኑ እስኪረጋገጥ መርገጫ አሳጥቷቸውም ነበር።

ይህን ሁሉ ሃገራዊ እውነታ በማስተዋልና በጥበብ የተጋፈጠው የለውጥ ኃይሉ፤ አንዳንድ ውሳኔዎቹ በሕዝብ ዘንድ ጥርጣሬ እየፈጠሩም ቢሆን ከፍ ባለ ቁርጠኝነት የሄደበት መንገድ አሁን ላይ ሃገርን በማስከንም ሆነ ለውጡን ከብዙ መንገጫገጭ በኋላ ወደ መንገዱ እንዲገባ እና ጉዞውን እንዲቀጥል የተሻለ ዕድል ፈጥሯል ።

በተለይም አለም አቀፉ ህብረተሰብ የፈጠረውን ጫና ሃገራዊ ከሆነው ተጨባጭ እውነታ ጋር በማስታረቅ የተጓዘበት እና እየተጓዘበት ያለው መንገድ አለም አቀፍ ጫናዎች ሊያደርሱት የሚችለውን ችግር ከማቅለል ባለፈ፤ትክክለኛ ሃገራዊ ገጽታውን ለዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ ለማሳየት የተሻለ አቅም መሆን ችሏል።

ለዚህ ደግሞ ዓለም አቀፍ ተቋማትም ሆኑ የሃገራት መንግስታት በሃገሪቱ ላይ ጫናዎችን ከማሳረፍ ወጥተው ፤ ሀገሪቱን በመደገፍ ሄደት ውስጥ በስፋት መሳተፍ የመጀመራቸው እውነታ ተጠቃሽ ነው። በየዕለቱ የምንሰማቸው የድጋፍ ዜናዎችም የዚሁ እውነታ ማሳያ ናቸው።

ከዚህም ባለፈ አሸባሪው ሕወሓት እንደቀደመው ወቅት ዓለምአቀፉን ኅብረተሰብ ለማወናበድ የሚያደርጋቸው የሚዲያ ዘመቻዎች ፍሬ አልባ እንዲሆኑ ከማስቻል ባለፈ ፤ ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ ስለ ቡድኑ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረው እያስቻለ ነው። ይህ ደግሞ አጠቃላይ የሆነውን ሃገራዊ ሰላም በማፍጠን የጀመርነውን ልማት አጠናክረን እንድንቀጥል በር ከፋች ትልቅ ስኬት ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## ‹‹ግርግር ለሌባ ይመቻል››

**ሜሎዲ ከኪስ ሜዳ**

አባቶቻችን ከፍ ያሉ እውቀቶችን የተሸከሙና ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገሩ ተረትና ምሳሌዎችን አስቀምጠውልን አልፈዋል ። እነዚህ ተረትና ምሳሌዎች ሀሳብን በቀላሉና በአጭር ከማስተላለፍ ባለፈ ከአንባቢ ጋር በቀላሉ ለመግባባት አቅም ያላቸው ናቸው ።

ይህንን ለማለት የተገደድኩት አሁን ላይ በየጓዳችን የምናንጎራጉርበት አለፍ ሲልም በየአደባባዩ የመንግስት ያለህ እያልን የምናለቅስበትን የዋጋ ንረት /በአለማዊና ሃገራዊ ጉዳይ/ ምክንያት በማድረግ ከአፋችን ላይያለችውን ለመመንተፍ ያሰፈሰፉ ቀማኞኞችን ነገር ሆድ ሆዴን ሲበላኝ መክረሙን ተከትሎ ነው ።

በተለይ ሆድ አደር ነጋዴዎች (ታማኞቹን ሳይጨምር) የመረቀዘው የኑሮ ቁስላችን ላይ እንጨት እየሰደዱበት ህመማችንንና የኑሮ ጣራችንን አብዝተውታል። ለዚህም ነው ‹‹ግርግር ለሌባ ይመቻል›› የሚለውን የአበው ቢሂል ጊዜውን የሚዋጅ ሆኖ ስላገኘሁት የጽሁፌ መንደርደሪያ ያደረኩት።

እናንተዬ ‹‹ነግ በእኔ›› የሚባል ነገር ቀረ አይደል!? ከጉሊት ቸርቻሪው ጀምሮ እስከ ጅምላ አካፋፋዩ ድረስ በሰበብ በአስባቡ የምስኪኑን ህዝብ ኪስ መቦጥቦጡ አላንስ ብሏቸው በአጥንት ሊያስቀሩት ከግራ ከቀኝ ወጥረው ይዘውታል። እንዲህ ምንተ-እፍረት የሌለው የአደባባይ ዘረፋ መጨረሻው ምን እንደኒሆን ማሰብ ቢከብድም የሚገርመው፤ ጉዳይ ግን አለምአቀፍ የኢኮኖሚ ቀውስ ተገን እያደረጉ ከእያንዳንዱ ዜጋ ጉሮሮ እየነጠቁ ኪሳቸውን እያደለቡ ያሉ ግለሰቦች መልሰው የሚኖሩት ከዚሁ ምስኪን ህዝብ መሃል መሆኑ የመዘንጋታቸው እውነታ ነው ።

በተለይ ሰሞኑን የነዳጅ ዋጋ ሊጨምር ነው የሚለው ወሬ እንደተሰማ ምርት በመደበቅ፤ ያለውንም ከጣሪያ በላይ ዋጋ በማናር ብዙዎችን በብዙ መልኩ አራቁተዋል። የብዙዎችንም ጓዳ ተፈታትነዋል ።የነዳጅ ዋጋ መጨመሩን ተከትሎም በአዋጅ ህዝቡን አራቁቱት የተባለ ይመስል በሳር በቅጠሉ ላይ ዋጋ በእጥፍ በመጨመር የነዋሪውን ፈተና አብዝተውታል።

በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ ከነዳጅ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ነገር ባይኖርም በተለይ ቀድሞ በገቡ ምርቶች ላይ ሳይቀር ዋጋ በመጨመር ቁጥሩ ቀላል የማይባለውን ለፍቶአደር ህይወት በከፍተኛ ሁንታ ተፈታትነውታል ።በዚም ለችግር እየተዳረጉ ያሉ ዜጎች ቁጥር ቀላል አይደለም ።

እስቲ ፈጣሪ ያሳያችሁ፤ ወቅቱ ክረምት ነው፤ መሬቱ ሁሉ በአረንጓዴ የሚሸፈንበት፤ እሸት ምርት በስፋት የምናገኝበት እረ እንዳውም ለወትሮው ጥጋብ በጥጋብ የምንሆንበት ጊዜ ነው። ዘንድሮ ግን “ሃባ” በቆሎ እንኳን 15 ብር የሚሸጥበትና እንደስጋው ሁሉ የበቆሎው ጥብስ ብርቅ እየሆነ ያለበት ሆኗል ።

ከሰሞኑ ወደ ቤቴ እያዘገምኩ ሳለሁ ከሰፈራችን በሚገኝ አንድ ዳቦ ቤት የሚወጣው የትኩስ ዳቦ ማዕዛ አወደኝና ለእኔም ሆነ ለልጆቼ ዳቦ ልገዛ ጎራ አልኩ። ለወትሮው አራት ብር ይሸጥ የነበረው የአንድ ዳቦ ዋጋ ሁለት ብር ታክሎበት ስድስት ብር መግባቱን አረዱኝና ባይሆን እኔ ይቅርብኝና ለልጆቼ ይገዙ ልጋባ ብዬ አምሮቴን ውጬና ራሴን አሳምኜ ገንዘቤ መግዛት የቻለውን ይገዙ ወደ ቤቴ ገባሁ።

ወገኖቼ የአንዱ ዳቦ ዋጋ በዚህ ደረጃ መቆለሉ አይደለም የሚገርመው፤ ዳቦው ራሱ ቆሌ የራቀው መሆኑ ነው፤ ከሁሉ በላይ ውሥጤን ያነደደኝ። ያ መልኩን አሳምሮና ማዕዛውን አውዶ ግዙኝ ግዙኝ የሚለው ዳቦ በማሻሻያና በእርሾ ያበጠ ፤ልክ እንደቅል ውስጡ ባዶ ነበር ለካ። እንዳንጠለጠልኩበት ፔስታል እየተንኮሻኮሸ ከልጆቼ አፍ ሳይደርስ ወለሉ ላይ ተጎዘጎዘ፤ በቃ ብሽቀቴን አትጠይቁኝ!፤ ብቻ ለእኔ የተረፈኝ የዳቦውን ቄጤማ መጥረግ ብቻ ነበር። መቼም ልክ እንደእኔ በእየለቱ የስግብግብ ነጋዴዎች እጅ ላይ የወደቃችሁ ብዙዎች እንደምትሆኑ አልጠራጠርም።

እናንተ ይሉኝታ ቢስ ነጋዴዎች ግን እስቲ ልጠይቃችሁ፤ እናንተ ገና ድክ ድክ ብላችሁ ንግዳችሁን ስትጀምሩ ከጎናችሁ ሆኖ የደገፋችሁን ህዝብ በዚህ ደረጃ ከሰውነት ተራ እዲወጣ መግፍፍ እንደምን አስቻላችሁ? እንዴትስ ዞራችሁ መግቢያችሁ፤ መደበቂያችሁና መቀበሪያችሁ ይህው ምስኪን ህዝብ መሆኑን ተዘነጋችሁ? ።

ዳሩ ልፊ ብሎኝ እንጂ እናንተ እንደሆነ የሰውን ሰውነት ከሸቀጥ ከመደባችሁት ቆይታችኋል። ህዝቡ ግን ዛሬም እየጮኸ ነው ፤ሰሚ እስኪያገኝም ይጮሀል ። ከዚህ ሁሉ ችግር ያወጡናል ብለን በጣታችን መርጠን የሾምናቸው እንደራሴዎቻችን ከወዴት አሉ? ይህ ሁሉ የህዝብ ጩኸት አልሰማ፤ እምባውም አልታይ ብሏቸው ይሆን።

ውድ አንባቢያን መርቃችሁና አጨብጭባችሁ የሾማችኋቸው እንደራሴዎቻችሁ የተሻለ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም አላረካ ብሏቸው ከነውረኛ ነጋዴዎች ጋር ተመሳጥረው ህዝቡን እየቦጠቦጡ መቀመቅም ሲወርዱ እየታዘብን ነው ። ለዚህ ደግሞ የሰሞንኛ ዜናዎቻችን ዋቢ ናቸው።

ግን ስር ከሰደደውና ከመረቀዘው ከዚህ ለህዝብ ያለመታመን /የሌብነት አባዜ መቼ ነው የምንወጣው ፤አብሮን ለሚኖረውና እጣ ፈንታ ለተጋራነው ህዝብ የምናስበው ከገባንበት እራስ ወዳድነትና ስግብግብነት መንገድስ ወጥተን ሀላፊነት በሚሰማው መንገድ የምንጓዘውስ መቼ ነው?።

ችግሩ ካለበት አሁነኛ ደረጃ አንፃር አሁን ላይ ያየነው ህጋዊ ርምጃ ቤት የሞላውን ቆሻሻ በስንጥር የማጽዳት ያህል እንደሆነ ይሰማኛል፤ጅመሩ እንደ ጅምር የሚበረታታና የሚመሰገን ቢሆንም ።

የዛሬውን ትዝብቴን “ከማክተሜ” በፊት ነውረኞቹ ነጋዴዎችም ሆነ ያበላጀውን እጅ የነከሱት ሹመኞች ሊረሱት የማይገባው ጉዳይ እሽኮኮ ብሎ ከስልጣንና ከሃብት ማማ ያወጣቸው ህዝብ አንድ ቀን የብሶት አርጮሜውን አንስቶ ከፍ ያለ ዋጋ ሊያስከፍላቸው እንደሚችል መርሳት እንደሌለባቸው በማሳሰብ ነው።

ያካባቱት ስምና ዝና በአንድ ጀምበር እንደሸክላ ወደ አመድነት ሊቀየር እንደሚችል ከትናት ታሪኮቻችን ሊማሩ ይገባል። እናንተ ምስኪን የእኔ አይነቶችም ብትሆኑ እለት ቁስላችሁን እየነካካ ከሚያመረቅዝ ሃሜት ተላቃችሁ የመጠየቅ፤ የማጋለጥና ለፍርድ የማቅረብ መብታችሁን ተጠቀሙበት ብዬ ልመክራችሁ እወዳለሁ።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

# በሠርግ ዋዜማ የመጣው ዱብዕዳ

**እፀገነት አክሊሉ**

ወልዶ መሳም ዘርቶ መቃም የሰው ልጆች ሁሉ ምኞት ነው። በተለይ ሦስት ጉልቻ መስርቶ ጎጆ ቀልሶ ኑሮዬ ላለ ሰው ይህ ምኞት ተገቢም አስፈላጊም ነው። ወልዶ መሳምም ይሁን ዘርቶ መቃም ብሎም ሦስት ጉልቻ መስርቶ ጎጆ መቀለስ ሁሉም እንደየሁኔታቸው የሚጠይቁት ሂደት ደግሞ አለ።

ዘርቶ ለመቃም ሞፈርና ቀንበር አዋህዶ በሬን ከበሬ አዳብሎ አርሶ መዝራትን ዘርቶ ማረምን ፍሬ ሲደርስ አጭዶና ወቅቶ ፍሬን ከገለባ ለይቶ በጎተራ ማስቀመጥን ይጠይቃል።

ሦስት ጉልቻ ለመመሥረትም በቅድሚያ አይን ያረፈባትን ልቡ የከጀላትን ኮረዳ ማግባባቱና መጠየቁ የሚቀድም ነው። ከዚህ በኋላም ሁለቱ ተፈላላጊዎች መስማማት ብሎም ጉዳዩን ወደቤተሰብ ወስዶ ፍቃድን መጠየቅ ተጨማሪው ሂደት ነው። ይህ ሁሉ ከታለፈ በኋላ ደግሞ ለሠርግ የሚሆነውን ነገር ማዘገጃጀቱ ሌላ ጊዜና ገንዘብ ብሎም ጉልበት የሚጠይቅ ይሆናል።

እገሊት እኮ ልጇን ልትድር ነው ከተባለም የቅርቡም የሩቁም ዘመድ አዝማድ ጎረቤት ጓደኛ ተሰብስቦ የሚከውነው ነገር የሚያዋጣው ግብዓት ብሎም ሃሳብ ብዙ ነው።

ወደ ድግስ ሥራው ከተገባም በኋላ ደግሞ እንደ ባህልና ወጋችን ጌሾ ወቀጣው፣ እንጨት ፈለጣው፣ በርበሬ ቅንጠሳው ብቻ ጣጣው ብዙ ነው። እንዲህ ያለው ሂደት ደግሞ ለቤተሰቡም ሆነ ለቤተዘመድ የሚሰጠው ክብርና ሞገስ ትልቅ ነው። እገሊት እኮ ክብሯን የጠበቀችዋን ልጇን ዳረች ይባልላታል።

ይህ ሁኔታ ደግሞ በጎረቤት አልፎም በዘመድ አዝማድ ዘንድ ምሳሌም ሆኖ እስከመነሳት የሚደርስ ግርማ ሞገስ አለው። በተለይም በቤታቸው ውስጥ አስቸጋሪ ልጆች ያሏቸው ወላጆች ምን ጊዜም ቢሆን አላየሽም የእገሊትን ልጅ ክብሯን ጠብቃ ተድራ ኮርታ ስታኮራቸው እየተባለ ይነገራል።



ፎቶ እፀገነት አክሊሉ

ወይዘሪት ዳንሴ ቱፋ

እንዲህ ሽር ጉድ ተብሎ ወራቶች ተወስደው የተዘጋጀው የሠርግ ድግስ ደግሞ ዘመድ አዝማድ በተሰበሰበበት ወዳጅ ዘመድ እየበላ እየጠጣ በሚጫወትበት በመጨፈር ሂደት ብዙ አዝናኝ ነገሮች ይፈጠራሉ።

አንዳንድ ነገሮች በተለይም በሠርግ ወቅት የሚፈጠሩ ክስተቶች አዝናኝ ስለሚሆኑ የማይረሱበት አጋጣሚም ብዙ ነው። ነገር ግን በዚህ ተቃራኒው አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የሚፈጠሩ አሳዛኝ ነገሮች ሙሽሮቹንም ሆነ የሙሽሮቹን ቤተሰቦች ሰቀቀን ውስጥ ከተው ያልፉሉ። አንዳንድ ጊዜ ሙሽሪት ቁጭ ብላ እየጠበቀች ባልዬው ሊቀር ይችላል፤ ይህ በራሱ ከሙሽራዋ ባሻገር በቤተሰቡ ብሎም በታዳሚው ላይ የሚፈጥረው ሃፍረትና ድንጋጤ በቀላሉ የሚታይ አይሆንም።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከሙሽሮቹ ቤተሰብ መካከል በዋዜማው አልያም በዕለቱ በአይቀሬው ሞት ተጠርተው የሚያልፉም አይጠፉም ይህም የሚያሳርፈው ጠባሳ ቀላል አይደለም።

ይህንን ሁሉ መንደርደሪያ ያደረግነውም አንድ በጣም አሳዛኝና ልብ ሰባሪ የሆነ ክስተት ስላጋጠመን ነው። የዛሬዋ ባለታሪካችን ዳንሴ ቱፋ ትባላለች ውልደትና እድገቷ ሞጆ ከተማ ነው ወላጆቿ በጥሩ ሁኔታ ነው ያሳደጓት። ዳንሴ ዕድሜዋ ለትምህርት ሲደርስም እንደ እኩዮቿ ተምራ ስደስተኛ ክፍል ደርሳለች። በአካባቢው እንዳሉት እንደማንኛዋም ሴት ደግሞ ዕድሜዋ ለሦስት ጉልቻ ሲደርስ እንደ አገሩ ባህልና ወግ ልትዳር ጎጆ ቀልሳ ሙሉ ሴት ልትሆን በትዳሯ መካከልም ወልዳ ልትስም ተዘጋጀች።

ለትዳር የተዘጋጀው ሰውም ምንም እንኳን እሷ በቅጡ ቀርባ ያወቀችው ባይሆንም አባቷና አባቱ በፈጸሙት ስምምነት መሠረት የተዘጋጀ ነው። ይህ ሰውም የታጨችለትን እጮኛውን በአገር ባህልና ወግ መሠረት ሊያገባ ለቤተሰቦቿ ሽማግሌ ልኮ የሚያስፈልገውን ጥሎሽ ጥሎ አስጠየቀ፤ ቤተሰቡም እንዲህ ባለው ክብር ልጃቸውን ለመዳር መታሰባቸው እጅግ አስደስቷቸው ለመጡት ሽማግሌዎች ልጃችንን ለልጃችሁ ትሁን ብለው ፍቃዳቸውን ሰጡ።

ቤተሰብ በዚህ ክብር ተሰምቶት ሳያበቃ ተከብራ ያስከበረቻቸውን ልጃቸውን እንዴት ባለው መልኩ ደግሰው እንደሚድሯት የትኞቹን ዘመዶቻቸውን ወገኖቻቸውንና ጓደኛ ጎረቤቶቻቸውን በጠቅላላው ወዳጆቻቸውን ጠርተው እንደሚያበሉ የደስታቸው ተካፋይ እንደሚያደርጉ አሰቡ።

ይህንንም እያሰቡ በቤታቸው አቅማቸው የፈቀደውን ሁሉ የድግስ ሥራ ተያያዙት ፤ በቅርብም በሩቅም ያለ ስለጉዳዩ የሰማ ወዳጅ ዘመድም ሁሉ የሚችለውን አቅሙ የፈቀደውን በዓይነትም በጉልበትም አስተዋጽኦ አደረገ ለማድረግም ተዘጋጀ፤ ያ በጉጉት ሲጠበቅ የነበረው የልጃቸው የሠርግ ቀንም ቀስ ቀስ እያለ አፋፍ ላይ ደረሰ። ዳንሴ ሦስት ጉልቻ ልትመሰርት ከእናት አባቷ ቤት በክብር ተድራ ልትወጣ አንድ ሳምንት ብቻ ቀራት። እነሱም ቢሆኑ ከሞላ ጎደል ዝግጅታቸውን ስላጠናቀቁ የቀኑን መድረስ በጉጉት ጠበቁት እንጂ አልፈሩም።

እሷም የረጅሙን የዕድሜ ዘመን አጋሯን ወደፊት የምትወልዳቸው ልጆች አባትን ባሏን ለማየት እንደናፈቀች ቀን ትቆጥራለች። ነገር ግን ዳንሴ እነዚህ ሁሉ እቅድ ሃሳቦቿን እንደጉም የሚያተን ብሎም ሕይወቷን ባላሰበችው ሁኔታ የሚያመሰቃቅል ጉድ ገጠማት። በዚህም ሰማይ ተደፋባት እንደዛ የተለፋበት ወግ ማዕረግ ሊታይበት የተናፈቀው ነገር ሁሉ ውሃ በላው። ዳንሴ ቱፋም በማታውቀው ምክንያት ለሠርጓ አንድ ሳምንት ሲቀራት መላ አካላቷ መታዘዝ አቃተው ጉልበት ከዳት ከተኛችበት ተነስታ መጸዳጃ ቤት እንኳን መሄድ አቃታት።

በዚህ ሁኔታዋ ደግሞ ቤተሰብ በሙሉ ተደናገጠ የትዳር አጋሯም ክው ብሎ ቀረ። ምን ሆና ነው ? የሚለው ጥያቄ የሁሉም ሆነ ነገር ግን መልሱን ሊሰጥ የተቻለው አንድም የቤተሰብ አባል አልተገኘም። ዳንሴ ቱፋ የደረሰባትን ነገር አሁንም ድረስ ማመን አልቻለችም፤ ስትናገርም እጅግ በጣም ሆድ ይብሳታል መላ አካላቷ ተሳስሮ ከተቀመጠችበት ወንበር ላይ የሚያነሷት ብቸኛዋ እናቷ ወይዘሮ ራዴ ጫካ ናቸው።

ወይዘሮ ራዴም የልጃቸው ሁኔታ ያሳዝናቸዋል የ27 ዓመቷ ዳንሴ እንደዚህ ሆና እያታለሁ እኔ እጅ ላይ ወድቃ ትቀራለች ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር ይላሉ። ወይዘሮ ራዴ ከምንም በላይ ደግሞ አንገታቸውን ያስደፋቸው ነገር ለራዴ ተብሎ የመጣውና የተቀበሉት ጥሎሽ ነው። «የልጄን ጥሎሽ በልቼ አፈርኩ» ይላሉ።

ላለፉት ስምንት ዓመታትም እናት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ልጃቸውን እየተሸከሙ ብዙ ፈተናዎችን አይተዋል፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ የሚያማቸው ነገር የልጃቸው ችግር ይህ ነው የሚላቸው ሀኪም ማጣታቸው መፍትሔውን የሚያመላክታቸው መቸገራቸው ነው።

እናት ከምንም በላይ የሚያሳስባቸው ነገር ዕድሜያቸው መግፋቱ ነው። ዕድሜያቸው መግፋቱ ደግሞ ልጃቸውን ለማገላበጥ አቅም አጣለሁ ብለው ሳይሆን ለማን ጥያት አልፋለሁ የሚለው ነገር ነው የሚያሳስባቸው። ዳንሴም ብትሆን ሁል ጊዜ የምትላቸው አንቺን ካጣሁ እኔ ምን እሆናለሁ ነው።

እናት ዛሬ ላይ ትንሽ አመም ሲያደርጋቸው ራሱ በከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ ይገባሉ፤ ልጄን ለማን ልተዋት ነው በሚል ጭንቀት። ዛሬ ላይ እናትና ልጅ የሚረዳቸውም የሚያግዛቸውም የለም ለጋብቻ ያጫት እጮኛዋም ችግሩን አልተካፈለም፤ እንዲያውም ይላሉ እናት ራዴ የልጁ አባት ከእኔ ጋር ለፍቷል ውጤት ባያመጣም ይላሉ።



ወይዘሮ ራዴ ጫካ

ይህች የ27 ዓመት ኮረዳ ልትዳር ባልም ለቤተሰቧ 12 ከብት፣ እንዲሁም ሌሎች ባህልና ወጉ የሚፈቅደው ሁሉ መጥቶላታል ይህንንም እናትና አባቷ ተቀብለዋል፤ ዛሬ ላይም እናት ከልጃቸው መሰናከል ባሻገር እንቅልፍ እየነሳቸው ያለው ነገር ይህ የበሉት የልጃቸው የሠርግ ጥሎሽ ነው። እኔ ብሞት ይህንን ዕዳ ማነው የሚያወጣው? የሚለውም እንቅልፍ አሳጥቷቸዋል።

ዛሬ ላይ ተነስተው የጥሎሹን ገንዘብ አይመልሱ አቅም የላቸውም ልጃቸውን ድረው በባህል በወጉ አለማቸውን አያዩ ነገር ልጃቸው እንኳን ለባል ለራሷም መሆን ተስኗት እጅና እግሯን በአግባቡ ማዘዝ አቅቷታል፤ ይህንን እያነሱ ደጋግ ኢትዮጵያውያን ይድረሱልኝ ይላሉ።

«እኔ ዕድሜዬን ጨርሻለሁ የሌት ተቀን ጭንቀቴ ለልጄ ነው፤ ልጄ እኔ ከሞትኩባት የምትቀመጥበትም የላት የሚያስታውሳትም አታገኝ» ይላሉ።


ዳንሴ እንባ እያነቃት ትናገራለች «የምወደውን ሰው ለማግባት በጣም ፍላጎት ነበረኝ ነገር ግን ለሠርጌ አንድ ሳምንት ሲቀረኝ ታመምኩ፤ በዚህ ምክንያት ደግሞ አባቴ እንዴት ያመማት ልጅ ለባል እሰጣለሁ ብሎ እምቢ አለ፤ ከዳነች የእናንተው ናት ብሎ እኔን ወደማሳከም ሄደ፤ እኔ ግን አልዳንኩም። አሁን ላይ ባለቤቴም ሌላ ሚስት አገባ» ትላለች።

ወደ ሕክምና ሄዳ መጀመሪያ የኩላሊት ጠጠር አለብሽ እንደተባለች የምትናገረው ዳንሴ በብዛት ውሃ በመጠጣት ጠጠሩ ሊወጣ እንደሚችል እንደተነገራት ትገልጻለች። ከሦስት ጊዜ በላይም ራጅ መነሳቷን በመግለጽ አሁን ላይ በሆዷ ውስጥ ተቀምጦ አላስተኛ አላስቀምጥ የሚላትን ሕመሟን በሕክምና መፍትሔ እንዳገኘችለት ትናገራለች። ሆኖም እንደ ልቧ መራመድ በእጇቿ ይዛ ውሃ መጠጣት ልብሷን ለብቻዋ መልበስና መጸዳዳት እንደማትችል ትገልጻለች።

አሁን ላይ ይላሉ እናት ጎረቤት ሄጄ ቡና መጠጣት ይጨንቀኛል፤ ዘመድ ቤት አልሄድም እነሱም አይመጡም ፤ ለቅሶ አልደርስም ፤ ብቻ እሷን አምኖ ቤት ውስጥ ጥሎ መሄድ ያስጨንቀኛል ፈጣሪ ረድቶኝ ልጄ የሚያግዛት ነገር ብታገኝ ይላሉ እንባ በተሞላበት ድምጽ።

በመሆኑም እናትና ልጅ በዚህ መሰል የኑሮ ውጣ ውረድ ውስጥ ነው ያሉት ዛሬ ላይ የሚያግዛቸው ይፈልጋሉ፤ ደጋግ ኢትዮጵያውያን አለንላችሁ በሏቸው።

# ስፖርት



# አረንጓዴው ጎርፍ በዛሬ ሌሊቱ ፍልሚያ ሊደገም ይችላል

ቦጋለ አበበ

18ኛው የኦሪገን የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ነገ ፍጻሜ ከማግኘቱ አስቀድሞ ዛሬ ሌሊት 10:25 ላይ አንድ አጓጊ ፉክክር ይጠበቃል። ይህ ፉክክር የሴቶች 5ሺ ሜትር ነው። በዚህ ውድድር አዲስ የዓለም ቻምፒዮን ብቅ እንደሚልም ብዙዎች ግምታቸውን አስቀምጠዋል። የርቀቱ አዲስ የዓለም ቻምፒዮን የመሆን ዕድሉም ከኢትዮጵያውያን ሦስት ኮከብ አትሌቶች የዘለለ እንደማይሆን ተገምቷል።

ያለፉትን ሁለት ቻምፒዮናዎች በርቀቱ ወርቅ ያጠለቀችው ኬንያዊቷ አትሌት ሄለን ኦቢሪ ኦሪገን ላይ በ10ሺ ሜትር ላይ ትኩረት ለማድረግ በመምረጧ በ5ሺ ሜትር አትሳተፍም። በኢትዮጵያም በኩል የርቀቱ የቀድሞ ቻምፒዮን አልማዝ አያና ኦሪገን አትገኝም። የርቀቱ የዓለምና የኦሊምፒክ ቻምፒዮን የሆነችው ትውልደ ኢትዮጵያዊቷ የኔዘርላንድስ አትሌት ሲፈን ሃሰንም በ10ሺ ሜትር ያሳየችው ደካማ አቋም ዘንድሮ ትኩረት ውስጥ እንዳትገባ አድርጓታል። ይህም በዚህ የውድድር አመት በርቀቱ ነጥረው የወጡ ወጣት አትሌቶች ወደ ቻምፒዮንነት ክብር እንዲመጡ ገፊ ምክንያት ተደርጎ ተወስዷል።

በውድድር አመቱ ድንቅ አቋምና ፈጣን ሰዓቶችን ያስመዘገቡት ደግሞ ሦስት እንቁና የወቅቱ የርቀቱ ኮከብ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ናቸው። ከሳምንት በፊት በ10ሺ ሜትር ወርቅ ያጠለቀችው ለተሰንበት ግደይ፣ ከቀናት በፊት በ1500 ሜትር በብር ሜዳሊያ ያጌጠችው ጉዳፍ ጸጋይ፣ ትኩስ ጉልበት ይዛ የዛሬውን የፍጻሜ ውድድር የምትጠባበቀው ዳዊት ስዩም የዓለም ትኩረት ናቸው። ሦስቱም አትሌቶች ማጣሪያውን በድንቅ ብቃት አልፈው ለዛሬው ፍጻሜ ቀርበዋል።

በዚህ የውድድር አመት በ5ሺ ሜትር ዩጂን ዳይመንድሊግ ላይ እጅጋየሁ ታዬን ተከትላ ሁለተኛ ሆና ያጠናቀቀችው የርቀቱ ባለክብረወሰን ለተሰንበት፣ ከወር




**ዳዊት ስዩም፣ጉዳፍ ጸጋይና ለተሰንበት ግደይ በዛሬ ሌሊቱ ፍልሚያ አረንጓዴውን ጎርፍ የመድገም ዕድል አላቸው፣**

በፊትም በኦስሎ ዳይመንድሊግ ዛሬ አብረዋት የሚፋለሙት የአገሯን ልጆች ዳዊት ስዩምና ጉዳፍ ጸጋይን ተከትላ ሦስተኛ ሆና ማጠናቀቋ ይታወሳል። ይህ ሲታይ ለተሰንበት ከሦስቱ ኢትዮጵያውያን አንጻር አነስ ያለ ስኬት ነው። ይሁን እንጂ የዛሬው ውድድር ዳይመንድሊግ አይደለም። ለተሰንበትም ከአመት በፊት የምናውቃት አትሌት አይደለችም። የቻምፒዮኖቹን ዓለም ከሳምንት በፊት ተቀላቅላ በትልልቅ ውድድሮች እንዴት ማሸነፍ እንደምትችል በቂ ልምድ አካብታለች። የርቀቱ ባለክብረወሰን መሆኗም መዘንጋት የለበትም። ይህም በቻምፒዮናው ጥምር ወርቅ የማጥለቅ ህልሟን እውን ለማድረግ ትክክለኛው ቀን ዛሬ እንደሆነ ማሳያ ነው።

በ1500 ሜትር ከቀናት በፊት ብር ያጠለቀችው ጉዳፍ ጸጋይ ቶኪዮ ኦሊምፒክ ላይ በ5ሺ ሜትር የነሐስ ሜዳሊያ አሸንፋለች። የቤልግሬዱ የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና ወርቅ ያጠለቀችው ጉዳፍ ከቤት ውጪ ቻምፒዮናዎች የወርቅ ሜዳሊያ ህልሟና ጥረቷ የሚሳካበት ትክክለኛው ቀን ዛሬ የሚሆንበት ዕድል ጠባብ አይደለም። ጉዳፍን በዚህ ርቀት ከለተሰንበት የሚለያት አንድ ነገር አለ። ጉዳፍ በርቀቱ እንደለተሰንበት ልምድ ያላት አትሌት ስትሆን የ1500 ሜትር ተወዳዳሪ መሆኗ የተሻለ ተጠቃሚ ያደርጋታል ተብሎ ይታመናል። በብዙ አጋጣሚዎች ለመታዘብ እንደተቻለው የ1500 ሜትር ተወዳዳሪዎች ወደ 5ሺ ሜትር ሲመጡ በአጨራረስ ብቃት ከሌሎች በተለየ የተሻሉ ናቸው።

ከጉዳፍ ጋር በተመሳሳይ ሌላኛዋ ድንቅ አትሌት ዳዊት ስዩም መነሻዋ 1500 ሜትር ቢሆንም በዚህ አመት ወደ 5ሺ ሜትር መጥታ ስኬታማ መሆኗን አስመስክራለች። ዳዊት ባለፈው የኦስሎ ዳይመንድሊግ ለተሰንበትንና ጉዳፍን በድንቅ የአጨራረስ ብቃት ማሸነፏ እዚህ ጋር ሲታወስ ዛሬ የርቀቱ አዲስ ቻምፒዮን ልትሆን እንደምትችል ፍንጭ ይሰጣል።

እነዚህ ሦስት ድንቅ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ወረቀት ላይ ብቻ ሳይሆን በተግባር የርቀቱ የወቅቱ ፈርጦች ናቸው። ውድድሩ ላይ አንዳች ነገር ካልተፈጠረም ወርቁ ከነዚህ እንስቶች እጅ የሚወጣበት ዕድል ዝቅተኛ ነው። እንዲያውም ሦስቱም ሜዳሊያዎች በነዚህ ከዋክብቶች እጅ አስቀድመው ወድቀዋል ቢባል ማጋነን አይሆንም። ይህም ኢትዮጵያን በዚህ ቻምፒዮና ወደ ላቀ ስኬት ከማሸጋገሩ ባሻገር የአረንጓዴውን ጎርፍ ታሪክ እንዲደግሙ ሊያደርጋቸው ይችላል። እነዚህ አትሌቶች ሦስቱንም ሜዳሊያ ከጠቀለሉም በዓለም ቻምፒዮና የርቀቱ ታሪክ ለሦስተኛ ጊዜ የሚመዘገብ ይሆናል። በዓለም ቻምፒዮና የሴቶች 5ሺ ሜትር ታሪክ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ከዚህ ቀደም በሁለት አጋጣሚ አረንጓዴውን ጎርፍ አሳይተዋል። እኤአ 2005 ሄልሲንኪ ላይ ጥሩነሽ ዲባባ፣ መሠረት ደፋር፣ እጅጋየሁ ዲባባና መሰለች መልካሙ ከአንድ እስከ አራት ተከታትለው የገቡበት ትልቅ ታሪክ አይዘነጋም። እኤአ በ2015 የቤጂንግ ቻምፒዮናም አልማዝ አያና፣ሰንበሬ ተፈሪና ገንዘቤ ዲባባ ከአንድ እስከ ሦስት ተከታትለው በመግባት ተመሳሳይ ታሪክ ተጋርተዋል። ዘንድሮስ? የዛሬ ሌሊቱ ፍልሚያ መልስ ይኖረዋል።

## ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረቱ ስም ወ/ሮ ማወርዲ ጀማል ሳሊ   የሰሌዳ ቁጥር 2-02997 ኦሮ ሊብሬ ቁጥር G0040648 ከላይ የተጠቀሰው ተሽከርካሪ ባለንብረት ሊብሬ G0040648 ጠፋብኝ ብለው በ13/06/2010 ዓ.ም. አመልክተዋል፡ ፡በዚሁ መሠረት የባለቤትነት ሊብሬ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ትራንስፖርት ባለሥልጣን**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ሂሩት ኋይሌ ተድላ የሰሌዳ ቁጥር አአ 01-01-18708 የተሽከርካሪው አይነት አነስተኛ አውቶቡስ (ከ12 ያነሰ መቀመጫ) የሻንሲ ቁጥር JT1VLH61V00103747 ሞዴል LH61LV-QRBFW የሞተር ቁጥር 2L-1570230 የሊብሬ ቁጥር 317262 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 11/11/2014 አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤትማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአዲስ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም እሱባለው ልየው ደስታ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-B14921 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር JAAKP34H7M7P02651 ሞዴል NPR6SN የሞተር ቁጥር 4HG1 0EH067 የሊብሬ ቁጥር 285655 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 12/11/2014 አመልክተዋል፡፡የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የጉለሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

አመልካች ወ/ሮ አሰገደች ደበሌ በንቲ ተጠሪ አቶ ዮናስ ሐይሉ ደበላ ከሰኔ ወር 2009 ዓ.ም ጀምሮ ጠፍተዋል፡ ስለሆነም ተጠሪ ሆኑ ሌላ ግለሰብ ስለተጠሪ ያሉበትን የሚያውቅ ካለ ለ 20/11/2014 ለሆነው ቀነ ቀጠሮ በ3፡02 ሰዓት በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉለሌ ክ/ከተማ ምድብ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጉለሌ ምድብ ችሎት**

የባለንብረት ስም ሄኖክ ታደሰ አስታጥቄ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-A93404 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር SCP10- 035509 ሞዴል TA-SCP10-AHPNK-T የሞተር ቁጥር1SZ-0891767 የሊብሬ ቁጥር 502401 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝብለው 12/11/2014 አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የጉለሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ብሪ ሀይሉ ተስፋሁን የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-02953 የተሽከርካሪው አይነት ተሳቢ የሻንሲ ቁጥር CT0245.99 ሞዴል 36H/ET/3/7.5 የሞተር ቁጥር Trailer የሊብሬ ቁጥር 0254226 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 12/11/2014 አመልክተዋል። የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአራዳ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## አማራ ክልል

**ለእሸቱ /ማሙሽ/ዘውዱ ይገዙ ባሉበት ፣**

በከሣሽ የሰሜን ሸዋ ዞን ዓ/ሕግ እና በተከሳሽ አየን ኃይልዬ አሻግሬ በተከሰሰበት ከባድ ሰው መግደል ወንጀል ክስ ክርክር ጉዳይ መከሰስዎን አውቀው ለሐምሌ 27 ቀን 2014 ዓ/ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰ/ሸ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት 2ኛ ወንጀል ችሎት ቀርበው እንዲከራከሩ ባይቀርቡ ግን በሌሉበት ክሱ ተሰምቶ በመዝገቡ ላይ ውሣኔ የሚሰጥ መሆኑን ፍ/ቤቱ አዟል፡

**የሰ/ሸ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት**

በከሳሽ፡-የሰ/ወሎ ዞን ዐ/ህግ እና በተከሳሽ አቶ ጌታቸው አባተ መካከል ሥላለው የትራፊክ ደንብ መጣስና በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል ክስ ክርክር ጉዳይ እርስዎ መከሰስዎን አውቀው ለሐምሌ22 ቀን 2014 ዓ/ም ለሆነው የቀጠሮ ቀን ወልዲያ ከተማ ለሚያስችለው የሰ/ወሎ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት የወንጀል ችሎት እንድቀርቡ፤ባይቀርቡ ግን በሌሉበት ጉዳዩታይቶ የሚወሰን መሆኑን ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የሰ/ወሎ ከፍ/ፍ/ቤት**

ንብረትነቱ ደረሱ ሙሉጌታ ሰሌዳ ቁጥር ኮድ 1-29434 አማ ተሽከርካሪ ሊብሬ የጠፋባቸው መሆኑን በመግለፅ ሊብሬ እንዲሰጣቸው በቀን 8/11/ 2014 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቀውናል፡፡ ስለሆነም ይህን ሊብሬ ወድቆ ያገኘ ወይን በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃውን ካላቀረበ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሊብሬ የምንሰጥ መሆኑ እንገልፃለን፡፡

**በአብክመ መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ የሰ/ሸዋ ዞን መ/ትራ መምሪያ የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ቡድን**

በከሳሽ፡-የሰ/ወሎ ዞን ዐ/ህግ እና በተከሳሾች አቶ አቢዩት አባቡ ባዩህ 2. አቶ ደረበ እባቡ መካከል ሥላለው ተራ ሰው መግደል ወንጀል ክስ ክርክር ጉዳይ መከሰስዎን አውቀው ለሐምሌ 29 ቀን 2014 ዓ/ም ለሆነው የቀጠሮ ቀን ወልዲያ ከተማ ለሚያስችለው የሰ/ወሎ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት የወንጀል ችሎት እንድቀርቡ፤ ባይቀርቡ ግን በሌሉበት ጉዳዩ ታይቶ የሚወሰን መሆኑን ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የሰ/ወሎ ከፍ/ፍ/ቤት**

በከሳሽ ደ/ብረሃን ዩኒቨርሲቲ እና በተከሳሾች 1. አቶ ኤፍሬም ጉዑሽ ኪዳኑ 2. አቶ ፍስሀ ጽጋብ ፈንታ መካከል ስላለው የትምህርት ውል መሰረት ባለመወጣት ክስ ክርክር ጉዳይ፤ መከሰስዎን አውቀው ለሀምሌ 26 ቀን 2014 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡40ሰዓት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡
ሳትቀርቡ ብትቀሩ ግን ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ በመዝገቡ ላይ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን ፍ/ቤቱ ያሳውቃል :

**የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደ/ብረሃን**